የቤተ፡ ክርስቲያን፡ መዝሙራት።

በስዊድን፡ ሚስዮናት፡ የታተሙ፡ በ፲፱፻፷፯ኛ።

B. Zimmerman

Lack a line - 32 123
Lack of age - 34 237
Majestic sweetness (tune) 38 893
Come to the Savior 44 1165
The great Physician 48 89
The gate ajar for me 59 372
Happy day 64 866
To you oh Jesus 78
[illegible] - 177
Jesus loves me - 199 - 1155 95
He came down from heaven - 201
Christmas song 134.
I take the name of Jesus 95. 91
What a Friend

አ ን ቀ ጽ ።

ስለ፡ እግዚአብሔርና፡ ስለ፡ ቃሉ፡	፭፡— ፲፭፡
ስለየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስለተፈጸመው፡ መድኃኒት፡	፲፮፡— ፴፯፡
የእግዚአብሔርን፡ ጸጋ፡ ስለመቀበል፡	፴፰፡— ፵፮፡
ስለ፡ ምዕመን፡ ሂሰታ፡	፵፰፡— ፶፱፡
ስለ፡ ምዕመን፡ አካሔድ፡	፷፫፡— ፯፯፡
የጸሎትና፡ የምስጋና፡ መዝሙራት፡	፯፯፡—፹፱፡
ስለ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ በጭላት፡	፹፰፡— ፺፰፡
ስለ፡ ክርስቶስ፡ መመለስና፡ ስለ፡ ፍርድ፡	፺፰፡—፻፳፰፡
ስለ፡ ሞትና፡ ስለ፡ ዘላለም፡ ብፅዕና፡	፻፳፱፡—፻፵፱፡
ስለ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሠራ፡	፻፶ ፡—፻፶፰፡
የሕፃናት፡ መዝሙራት፡	፻፶፱፡—፻፹፩፡
የጥዋትና፡ የማታ፡ መዝሙራት፡	፻፹፫፡—፻፹፯፡

ስለ፡ እግዚአብሔርና፡ ስለ፡ ቃሉ።

፩፡

S. T. 472.

፩፡ አምላችን፡ አምላካችን፡ ነው።
እርሱም፡ እኛ፡ ጠራችን።
በመከራችን፡ እርሱ፡ ነው፡
ጽኑ፡ መጠጊያችን።
ያለም፡ ገዢ፡ ወርድዋል፤
ቀኣጣውም፡ በዝትዋል።
በተንኰልና፡ ኃይል፡
ይጣጣርብናል።
እኛ፡ ግን፡ አንፈራውም።

፪፡ ኃይላችንስ፡ ባልበቃን፡
ዶሎ፡ በጠፋን፡ ነበር፤
ግን፡ ያ፡ ረድኤት፡ እስካለን፡
በምንም፡ አንሸበር።
የሱስ፡ ነው፡ የረዳ፡ ስም።
ሰው፡ ነው፡ አምላክም።
የድል፡ ልብስ፡ ለብሰዋል፤

ዙፋኑም፡ ጸንትዋል፡
በኃይሉ፡ ለዘላለም።

፫ ዓለም፡ በጨለማ፡ ሥልጣን፡
ቢገዛም፡ ተስፋ፡ አለን።
በአምላክ፡ ኃይልና፡ ብርሃን፡
ሰርክ፡ እናሸንፋለን።
ያለም፡ ገዢ፡ ወደቀ፡
ኃይሉም፡ አለቀ።
እርሱ፡ በአንዳችም፡
ሊጐዳን፡ አይችልም።
ከጌታ፡ ቃል፡ ይሸሻል።

፬ የአምላክ፡ ቃል፡ አይፋለስም፡
ተስፋውም፡ ዘወትር፡ አለን።
ለአምላክ፡ ስንጋደልም፡
በእርሱ፡ ደስ፡ ይበለን።
ሁሉም፡ ቢጠፋብኑ፡
ቃሉ፡ ሳለን፡
ያምላክ፡ ፈቃድ፡ ይሁን።
እኛ፡ ግን፡ መንግሥቱን፡
ለርስት፡ እንወርሰለን።

ረዐቲን።

፪

S. T. 489; Stud. miss. 54.

፩ የአምላክ፡ ቃል፡
ያሸንፋል፡
የጨለማውን፡ ሥፍራ፡
ሰላም፡ ላጡ፡
ለወደቁ፡
ይሰጣል፡ ጽኑ፡ ተስፋ።

፪ በትእዛዙ፡
ሰባክቹ፡
ወጡ፡ በመላ፡ ዓለም።
ክፉ፡ ቅናት፡
ሰይፍ፡ ወይስ፡ እሳት፡
ወንጌሉን፡ አያስቀርም።

፫ ለጨካኞች፡
ላመጸኞች፡
ጽድቅን፡ ይሰብክሉ።
በጨለማ፡
እንዲበራ፡
ብርሃኑን፡ ያቆማሉ።

፬፡ በዓለሙ፡
ይዘራሉ፡
አምላክ፡ ዘሩን፡ ያለማል።
በምሕረት፡ ቀን፡
አንድ፡ ነፍስ፡ ቢድን፡
አምላክን ደስ፡ ያሰኛል።

፭፡ ልዑል፡ ንጉሥ፡
በኛ፡ ንገሥ፡
ግዛትህንም፡ አስፋ።
ድል፡ ያንተ ነው፡
በዓለሙ።
ላንተ፡ ይሁን፡ ምስጋና።

O. E.

፫፡

S. T. 484.

፩፡ ቅዱስ፡ ቃሉን፡ የሚሰሙ፡
አምላክን፡ የሚወዱ፡
ታዘው፡ ለቅዱስ፡ ፍቃዱ፡
ለጌታ፡ የሚለፉ፡
በመንፈሱ የሚመሩ፡
በወ ነት፡ ብዙዓን፡ ሆኑ።

መንግሥቱንም፡ ሊወርሱ።

፪፡ እምነታቸው፡ ድል፡ ሊነሣ፡
ጠብ፡ ውከት፡ በሚገዛ።
ፍቅራቸው፡ ደምቆ፡ ሊነድድ፡
ፍቅር፡ በዓለም፡ ሲበርድ።
የተስፋቸውም፡ መሠረት፡
ጸንቶአል፡ እንደ፡ አለት፡
በሞት፡ ውኖ፡ በሕይወት።

፫፡ ድመቅ፡ ጩራ፡ ከአብ፡ ግርማ፡
ይውረድ፡ በምድር፡ ዙርያ፡
ተንኧርግን፡ ሊያፈራ፡
ቸርነት፡ ሰላም፡ ደስታ
በግርማ፡ የምታገሰ፡
ይህች፡ ምድር፡ ትውን፡ ለኛ፡
ሰማያዊ፡ መግቢያ።

O. E.

፬፡

S. T. 550.

፩፡ ገስግሱ፡ ሲያልፍ፡ ቀናችን፡
በምላክ፡ ቃል፡ ሰርክ፡ እንጽና።
እርሱ፡ ነው፡ የሚበራልን፡

በዚህ፡ ዓለም፡ ጨለማ።
ክጥንት፡ ዘመን፡ ጀምሮ፡
ኃይልን፡ ደስታን፡ ሰጥቶ፡
በሰማይ፡ በሚያገ፡
በዚህ፡ ቃል፡ ሰርክ፡ እንመራ።

፪፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ስንዋተት፡
እንደ፡ ጥንቱ፡ ቅዱሳን፡
ቅዱስ፡ ቃሉን፡ ለማዳመጥ፡
እንሰብሰብ፡ ሲጠራን።
አባት፡ ከልጆች፡ ጋራ፡
ያቅርብለት፡ ምስጋና።
በየውሃቱ፡ እንዲያየን፡
ዘትር፡ ተግቶን፡ እንለምን።

፫፡ ባርከን፡ ጠብቀን፡
ጸጋን፡ ሞገስን፡ ስጠን።
ዘትር፡ በምክርህ፡ ምራን፡
በመንገድ፡ ብርሃን፡ ሁንን።
መልስልን፡ ፈትህን፡
ሰላምህን፡ አካፍለን፡
ሥሉስ፡ አምላክ፡ ስለ፡ ፍቅሩ፡
ይመስገን፡ በዓለም፡ ሁሉ።

O. E.

፭፡

S. T. 439.

፩፡ ብርሃን፡ በሌት፡ እንደሚዘልቅ፡
የጌታ፡ ቃል፡ ይሰፋል።
የዓለም፡ ዘመንም፡ ሊያልቅ፡
ዙፋኑ፡ ይረጋጋል።
ስሙን፡ በእምነት ሲጠሩ፡
ለመስቀሉ፡ ይሰግዳሉ፡
የምድር፡ ሕዝቦች፡ ሁሉ።

፪፡ ሕፃናት፡ ያቀርቡለታል፡
በሞት፡ ጽላም፡ ብርሃን፡ ነው።
በጭንቅም፡ ለርሱ፡ ይጮኻል፡
በደስታ፡ ቀን፡ የረሳው።
በመከራ፡ በሐዘንም፡
ኃይል፡ አጥቶ፡ ለሚደክም፡
ሌላ፡ ረድኤት፡ አይገኝም።

፫፡ በሞት፡ በሕይወት፡ የሱስ፡ ሁን፡
ወትሮ፡ ባጠገባችን።
ላክልን፡ ቅዱስ፡ መንፈሱን፡
በቆሰለ፡ ልባችን።
ኃይልን፡ ስጠን፡ በድካም፡

ሞትም፡ ሲደርስን፡ በሰላም፡
አድነን፡ ከዚህ፡ ዓለም።

ፈሪሂን።

፯፡

S. T. 671.

ኢሳ፡ ፶፰፡ ፲።

፩፡ አለት፡ ቢፈርስም፡ ተራራ፡ ቢወድቅም፡
እምነቴ፡ እስከ፡ ዘላለሙ፡ ነው።
የኪዳኔም፡ ጸጋ፡ ከአንቺ፡ አይርቅም፡
እንዲህ፡ የሚልሽ፡ መድኃኒትሽ፡ ነው።

፪፡ አ፡ ጌታ፡ የሱስ፡ ያን፡ ቃል፡ እንዳልረሳ፡
ተስፋህንም፡ እንድታመን፡ እርዳኝ።
ከመቃብሬም፡ ከእንቅልፌ፡ ስነሣ፡
ያ፡ ክቡር፡ ቃልህ፡ በቤትህ፡ ያግባኝ።

አኖ፡ ሌኖ።

፰፡

S. T. 303.

፩፡ አ፡ የሱስ፡ ቃልህ፡ ጸንቶዋል፡
መንግሥትህም፡ አይፈርስም።
ጠላትህ፡ ይወረውራል፡
ወዳምባህ፡ ግን፡ አይደርስም።

እስከ፡ ዘላለም፡ እንዳይወድቅ፡
አንተ፡ በእውነትና፡ ጽድቅ፡
ዙፋንህን፡ አጸናህ።

፪፡ ለኛ፡ ግን፡ ቆሎ፡ የሚያልቅ፡
የጠፋም፡ ይመስለናል።
መሠረቱም፡ እንደሚወድቅ፡
መስሎን፡ ደንግጥ፡ ይለናል።
ይህ፡ ግን፡ ኃይልህ፡ ባይሰማን፡ ነው፡
መንግሥትህ፡ የማይጠፋ፡ ነው፡
ቃልህም፡ ይረጋጋል።

፫፡ ግን፡ ጌታ፡ ሆይ፡ ያንተ፡ ሥልጣን፡
ከዚህ፡ ዓለም፡ አይደለም።
ከምድር፡ ሁሉ፡ ክቡራን፡
የሚሰግድልህ፡ የለም።
የክርስቲያኖችህ፡ ድካም፡
ሲታይ፡ የመንግሥትህ፡ ሰላም፡
ለዓለም፡ ሰው፡ አይታይም።

፬፡ ተመስገን፡ ርኅሩኅ፡ መድኃኔ፡
ለኔ፡ ተገለጠልኝ።
የመንግሥትህ፡ ወራሽ፡ ሁኜ፡
ብፅዕናህ፡ ደረሰልኝ።

ከአንተም፡ ዘንድ፡ ምስጋናሀን፡
ስዘምር፡ ታላቅ፡ ጸጋህን፡
ዘላለሙ፡ ላመስግን።

ረስቲን።

፲፬፡

S. T. 440.

፩፡ አንተ፡ እውነተኛ፡ አምላክ፡
የሚያውቅህ፡ ብፁዕ፡ ሆነ።
ልጅህ፡ እርሱም፡ ፍጹም፡ አምላክ፡
ከንተ፡ ጋር፡ አስታረቀን።
የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሆይ፡ ሆንህልን፡
መንገድ፡ እውነትም፡ ሕይወትም።
ለመድኃኒት፡ የሚሆነን፡
ሌላ፡ ስም፡ ግን፡ አልተሰጠም።

ረስቲን።

፲፭፡

S. T. 441.

፩፡ ቅዱስ፡ ሥላሴ፡ ምስጢር፡ ነው።
በአብ፡ ተፈጥረናል።
ወልድም፡ አዳነ፡ ሁሉን፡ ሰው።

መንፈስ፡ ይቀድስናል።
አብን፡ ወልድን፡ መንፈስንም፡
እናምልክ፡ እናመስግንም፡
ከሁን፡ እስከ፡ ዘላለም።

ረስቲን።

፲፡

S. T. 477.

፩፡ እናምናለን፡ በአባት፡
ያቆመ፡ ምድርን፡ ሰማያት።
ጥጋችን፡ ነው፡
ርኅሩኅ፡ የዋህ፡ ለሰው።
ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ነው፡ አምላክ፡ ጸባኦት።

፪፡ ሊያድነን፡ ከሞት፡ ጥፋት፡
ክርስቶስ፡ መጣልን፡ ከአባት።
እኛን፡ ፈታ፡
ሆነልን፡ ቸር፡ ጌታ።
ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ነው፡ አምላክ፡ ጸባኦት።

፫፡ መንፈሱ፡ ጸጋን፡ ያድላል፡
ይቀድሰናል፡ ባምላክ፡ ቃል።
ለነፍስ፡ ሕይወት፡

ይሰጣል፡ በእምነት።
ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ነው፡ አምላክ፡ ጸባኦት።

N. N.

፲፩፡

S. T. 303.

፩፡ ከአምላካችን፡ ማን፡ ይበልጥ፤
እንደርሱስ፡ ማን፡ ይሆናል፤
ከሃሊ፡ ኃይሉንም፡ ሲገልጥ፡
እንዴት፡ በጣም፡ ይገርማል።
በስድስት፡ ቀን፡ በኃይሉ፡ ቃል፡
ምድራችንን፡ አቁምዋል፡
በርስዋም፡ ያለውን፡ ሁሉ፡

፪፡ አምላክ፡ የፈጠረውም፡ ሁሉ፡
ግሩምና፡ መልካም፡ ነበር።
እባቡ፡ ግን፡ በተንኰሉ፡
አጠፋው፡ ሁሉን፡ ነገር።
በአባታችን፡ ኃጢአት፡
ውርሳችን፡ ሁንዋል፡ ጥፋት፡
በሁሉም፡ ፍርድ፡ ተጫነ።

፫፡ ግን፡ አምላክ፡ ሰው፡ ሆኖልናል።

በሕይወቱም፡ በሞቱም፡
መድኃኒት፡ ተገኝቶልናል፡
ከፍርዱ፡ ከጥፋቱም።
ፍዳችንን፡ ተቀበለ፡
ዕዳችንንም፡ ከፈለ፡
ተፈጸመ፡ ሲል፡ ሞተም።

፬፡ ይህንም፡ የሚያምነው፡
በልቡም፡ የሚቀበል፡
ይታጠባል፡ ከበሽታው፡
በቅዱስ፡ ደሙ፡ ጠበል።
ከክርስቶስ፡ ጋራ፡ ድንዋል፤
ለነፍሱም፡ ሕይወት፡ ያገኛል፡
ከወንድሙ፡ ከየሱስ።

፭፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስም፡
አገኘን፡ ደህንነት።
ለሥሉስ፡ አምላካችንም፡
ምስጋና፡ ይሁንለት።
ከሞትና፡ ከሰይጣን፡ ኃይል፡
በየሱስ፡ ፍጹም፡ ድነናል።
መድኃኒት፡ ሆይ፡ ተመስገን።

ረሰቲን።

፲፪፡

S. T. 535.

፩፡ አምላክ፡ የፈለገው፡ ከንተ፡
በግልጥ፡ ተነግርዋል።
ሲገሥፅ፡ ሲመክር፡ ላንተ፡
ዋቅም፡ ይሆንሃል።

፪፡ በገርንት፡ በትሕትና፡
በእምላክ፡ ቃል፡ እመን።
ተግተህ፡ በቀና፡ ሕሊና፡
ፈቃዱንም፡ ፈጽም።

፫፡ በክርስቶስ፡ ሁሉ፡ ይቀናል፡
በኃይሉ፡ ነህ፡ ሥልጡን።
መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ይረድሃል፡
ያሳይሃል፡ ፍቅሩን።

፬፡ በቃሉ፡ የሚያምኑ፡
ለጽድቅ፡ አላቸው፡ ኃይል፡
በምድር፡ በሰማይ፡ በርሱ፡
ሰላም፡ ብፁዕ፡ ዕድል።

፭፡ በአንተ፡ ነው፡ የአብ ሥምረት፡
የዓለም፡ ተስፋ፡ ነህ።

ትላንት፡ ዛሬ፡ ሳትለወጥ፡
ግና፡ ትኖራለህ።

O. E.

፲፫፡

S. T. 439.

፩፡ ልዑል፡ አምላክ፡ ለወገኑ፡
ብዙ፡ ስጥወታ፡ ሰጠ።
ፍቅሩንም፡ የሚያወሩ፡
መላእክትን፡ ለኛ፡ ላክ።
ለሰርክ፡ ለሚከባክበን፡
ልዑል፡ አምላክ፡ እናመስግን፡
መላእክትን፡ ለላከልን።

፪፡ በእግዚአብሔር፡ ልጆች፡
ዙርያ፡ ይሰፍራሉ።
ሊያስጥሉ፡ ከጠላቶች፡
ቤታቸውን፡ ይከባሉ።
በምላክ፡ ትእዛዝ፡ ቀንና፡ ሌት፡
ሊጠብቁን፡ በጎች፡ መላእክት፡
ለአምላክ፡ ብንከተት።

፫፡ መንገድን፡ ይጠርጉልናል፡
እግር፡ እንዳይሰናክል።

ጋሬጣን፡ ያስነሡልናል፤
በቃሉ፡ ስንከተል።
ዕድሜ፡ ቢያለማግገን፡
ይሸከሙናል፤ ደስ፡ ብሎን፡
አምላክን፡ እናመስግን።

ሉንሂል። — O. E.

ፕፀ፡

S. T. 437.

፩፡ ለአምላካችን፡ በሰማይ፡
ይገባዋል፡ ምስጋና፡
ስለ፡ ጸጋው፡ በሰው፡ ላይ፡
የሰጠው፡ ለብዕዕና።
በምድር፡ ደስታና፡ ሰላም፡
ሲሰጥ፡ ይገባናል፡ በጣም፡
ፈቃዱን፡ ልንፈጽም።

፪፡ አ፡ አባት፡ ስላንተ፡ ምሕረት፡
እናመሰግናለን።
አንተ፡ በታላቅ፡ ቸርነት፡
ጸጋን፡ አወረድህልን።
ሥሉጥ፡ እጅህ፡ ሁሉን፡ ይይዛል፡

ስውር፡ ኃጢአት፡ ይታይሃል፤
ጽኝነትህ፡ ይቀናል።

፫፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ የልዑል፡ ልጅ፡
ልታድነን፡ የመጣህ፡
ከፍርድና፡ ከሰይጣን፡ እጅ፡
በሞት፡ እኛን፡ የዋጀህ፡
በትልቅ፡ ምሕረትህ፡ መጠን፡
ከመቅሠፍት፡ ሞት፡ ልታድነን፡
በአንተ፡ ስንማጠን።

፬፡ በመንፈስህ፡ ልባችንን፡
በቃልህ፡ አጸናና።
ላንተ፡ ምስጋና፡ መቅደስህን፡
ወደ፡ ነፍሳችን፡ ሥራ።
በመከራችን፡ ደግፈን፡
አድስ፡ ለጽድቅ፡ ልባችንን፡
እምነትን፡ ጨምርልን።

ሉንሂል።

ፕፈ፡

S. T. 663; 438.

፩፡ ወደ፡ መቅደስ፡ ተራሮች፡
ሽቅብ፡ አያለሁ።

ረድኤት፡ ከጌታ፡ አለች።
በፍቅሩ፡ አመንሁ።
ረድኤቱ፡ ትመጣለች፡
ሁሉን፡ ከፈጠረ።
ጸሎቴ፡ ትሰማለች፡
ሁሉን፡ ከሚራራ።

፪፡ እግሬንም፡ ለመናወጥ፡
አምላኬ፡ አይሰጥም።
ጠባቂዬ፡ በእርግጥ፡
ከዶ፡ አይደክምም።
እርሱ፡ ጸጋውን፡ ሰጠኝ፡
ከኃጢአት፡ ለማዳን።
ዘወትር፡ ሊቆምልኝ፡
እስክደርስ፡ ወደ፡ ላይ።

፫፡ አምላክ፡ ነፍሴን፡ ከክፋ፡
ወትሮ፡ ይጠብቃል።
የደረሰብኝ፡ ሁሉ፡
ጥቅም፡ ይሆነኛል።
ይባርክል፡ መግቢቴን፡
ድምድሙን፡ ያቀናል።

በአምላክ፡ ለሚማጠን፡
ለግሱ፡ ይመርቃል።

ሉኒያል።

በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስለ፡ ተፈጸመው፡ መዳን።

፲፯፡

S. T. 53.

፩፡ ተስፋ፡ የሰጠኝ፡ ሕይወትም፡
አንድ፡ ስም፡ ተገለጠ።
ከምድር፡ ከሰማያትም፡
ያ፡ ድንቅ፡ ስም፡ በለጠ።

፪፡ ያ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ ነው፡ አምባዬ፡
እርዴም፡ በጭንቀቴ።
በሐዘንም፡ ነው፡ ደስታዬ፡
በችግርም፡ ሀብቴ።

፫፡ ያ፡ ስም፡ ስላንድ፡ ርኅሩኅ፡ ወዳጅ፡
ይተርክልኛል።
ወዳጄም፡ የሰማይን፡ ደጅ፡
ለኔ፡ ከፍቶልኛል።

፬፡ አባቴም፡ እንዲቀበለኝ፡
ያ፡ ስም፡ ያስታውቃል።

አንድ፡ ብፁዕ፡ ወደብ፡ እንዲገኝ፡
ያ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ ይላል።

፭፡ ስለሚረዳኝ፡ ምሕረት፡
ያ፡ ስም፡ ይናገራል።
ስጨነቅ፡ ኃይልና፡ ረድኤት፡
ወትሮ፡ ይሰጠኛል።

፮፡ እንደኔም፡ የተፈተነ፡
የሚራራልኝም፡
መድኅን፡ እንደተሰጠን፡
ይተርካል፡ ያ፡ ስም።

፯፡ ያ፡ ብፁዕ፡ ስምም፡ የሱስ፡ ነው፡
እርሱ፡ ነው፡ ተስፋዬ።
እረፍቴና፡ ሰላሜ፡ ነው፡
በርሱም፡ ነው፡ ደስታዬ።

፰፡ ምድራዊ፡ አፍ፡ ያን፡ ቅዱስ፡ ስም፡
ሊያመሰግነው፡
አይበቃም፡ እንጂ፡ ባርያም፡
የብፁዓን፡ መዝሙር፡ ነው።

፱፡ ግን፡ ከዚህ፡ ምድር፡ በረሐ፡
ስሔድ፡ ወዳገሬ፡

ያ፡ ስም፡ ነው፡ ለኔ፡ ፍሥሐ፡
ያ፡ ስም፡ ነው፡ መዝሙሬ።

፲፡ አንድ፡ ቀንም፡ ወደ፡ አገሬ፡
የሱስ፡ ሲያደርሰኝ፡
አዲሱን፡ መዝሙር፡ ዘምሬ፡
ያን፡ ስም፡ ልወድስ፡ ነኝ።

ረስቲን።

፲፩፡

S. T. 449.

፩፡ የየሱስ፡ ስም፡ ያጸናናል፡
በመከራም፡ ይረዳናል።
በየሱስ፡ ጸጋ፡ አለን፡
የአብ፡ ሥምረትን፡ ሰጠን።

፪፡ አ፡ ያምላክ፡ ልጅ፡ አ፡ ረጃችን፡
በምሕረትህ፡ ይቅር፡ በለን።
ሰው፡ ነህ፡ በእውነት፡ አምላክም።
እይ፡ ጭንቃችንን፡ እርዳንም።

፫፡ ጽድቅ፡ ሁሉ፡ ከንተ፡ ብቻ፡ ነው፡
ሰላምም፡ ዕርቅም፡ ካንተ፡ ነው።
በቅዱስ፡ ስምህ፡ ያመነ፡
እርሱ፡ ከሁሉ፡ ፍርድ፡ ዳነ።

፬፥ ምስጋና፡ ስለ፡ ጥምቀትህ፡
ስለ፡ ቁርባንም፡ እንስጥህ።
በዚህ፡ ሕይወት፡ ሰላም፡ ስጠን፡
ወደ፡ ሰማይም፡ ሰብስበን።

ረስቲን።

፲፰፡

S. T. 557; Ahnf. 15.

፩፥ ጸውልን፡ እንዳበባ፡
ሲቀር፡ የዓለም፡ ተስፋ፡
ውኃ፡ ፈልቆ፡ በበረሐ፡
ለተጸማ፡
ነፍሱን፡ የሚያረክ።

፪፥ ክርስቶስ፡ ፍቅሩን፡ እያሳየን፡
የሕይወት፡ ምንጭ፡ ሆነልን።
በደሙ፡ የሚያድነን፡
ለነፍሳችን፡
ሀብቱን፡ አቀረበልን።

፫፥ በዓለም፡ እርሱ፡ ነው፡ ብቻ፡
ከጭንቀት፡ የሚረዳ።
ሊሰዋ፡ ለኃጥአን፡ ይቅርታ፡

ምሉ፡ ጸጋ፡
ኑዛዜ፡ ለሚገባ።

፬፥ ከየሱስ፡ ነው፡ ብርሃን፡ እውነት፡
ሆነልን፡ መንገድ፡ ሕይወት።
የፈለገው፡ ያገኘዋል፡
ይሰጠዋል፡
ለለመነው፡ በእምነት።

፭፥ በመላ፡ ዕድሜያችን፡ ቀን፡
እጆቹን፡ ዘረጋልን።
ገና፡ እኛን፡ ይታገሣል፡
ይጠረናል፡
እምነትን፡ አጸናልን።

፮፥ በጎ፡ አረኛ፡ ሁንዋል፡
የጐደለን፡ ይመላል።
በወንጌል፡ በቅዱስ፡ አራት፡
ሰጠን፡ ብዕአት።
ርኅሩኅ፡ ሁኖ፡ ይኖራል፡

፯፥ ከኩነኔ፡ ሊያድነን፡
ስንት፡ ውለታ፡ ዋለልን።
ድል፡ ይሰጣል፡ በጦርነት፡

በቸርነት፡
ሆነልን፡ ጤና፡ ሕይወት።

፫፡ እንደ፡ አባት፡ አሳድረን፡
ጸጋህን፡ አቅርብልን።
ሰላምን፡ ስጥ፡ ለችግር፡ ነፍስ፡
ለኛ፡ ለግስ፡
ይህ፡ ጉዞ፡ እስኪጨረስ።

፬፡ በሚደርስብን፡ መከራ፡
ሆንህልን፡ ረድኤት፡ ተስፋ።
በጭንቅ፡ በሞት፡ አሳልፈህ፡
በመንግሥትህ፡
ብዕዕናን፡ ትሰጣለህ።

O. E.

፲፱፡

S. T. 439.

፩፡ ደስ፡ እንዲለን፡ ይገባናል፡
ባገኘነው፡ ድንቅ፡ ነገር።
አምላክ፡ አሁን፡ ይምረናል፡
ፍርዳችን፡ ሞት፡ የነበር።
ሊምረን፡ እንደወደደ፡

የሚለን፡ ቃሉን፡ ሰደደ።
ይህም፡ ደስታችን፡ ሆነ።

፪፡ የሰይጣን፡ ባርያ፡ ነበርሁኝ፡
መዳኔም፡ አልተቻለም።
በኃጢአቴ፡ ታሠርሁኝ፡
ልጠፋ፡ ለዘላለም።
ወደ፡ ሲያል፡ እሳት፡ ልወርድ፡
በገዛ፡ ሕሊናዬ፡ ፍርድ፡
እንደሚገባኝ፡ ሆነ።

፫፡ ተስፋ፡ ስቆርጥም፡ ከጥፋት፡
መዳን፡ ስላልታየልኝ፡
አምላክ፡ በምሕረቱ፡ ብዛት፡
በአባት፡ ፍቅር፡ አየኝ።
በኃጢአቴ፡ ከርፍቼ፡
ሳለሁ፡ ተሰጠኝ፡ ያባቴ፡
ቸርነትና፡ ፍቅር።

፬፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ተናገረ፡
እራራላቸዋለሁ።
እኒያን፡ ምስኪን፡ እሥሮች፡
ለልጄ፡ እሰጣለሁ።
በደሙ፡ ከዘላለም፡ ሞት፡

ሊያድናቸው፡ አዘዝሁት፡
ሊሆንላቸውም፡ ሕይወት።

፫፡ አባቱም፡ እንደፈቀደ፡
ወልድ፡ ታዘዘ፡ በፍቅሩ።
ከሰውም፡ ሥጋ፡ ተዋሐደ፡
ሲደበቅበት፡ ክብሩ።
ሕግ፡ በኔ፡ እንደፈረደ፡
ሊሞት፡ በመስቀል፡ ወረደ፡
ከሞቴም፡ ሊያወጣኝ።

፬፡ ከግፉ፡ ፍርዴም፡ እንድድን፡
ሕይወቱን፡ ለወጠልኝ፡
የከበረም፡ የየሱስ፡ ደም፡
በመስቀል፡ ፈሰሰልኝ።
ሲሞት፡ አወጣኝ፡ ከፍርዴ፡
ሆነልኝም፡ አማላጄ፡
በበቱም፡ ፈት፡ ቆመልኝ።

፭፡ ከዚህም፡ ዓለም፡ መከራ፡
ወዳጠቱ፡ ወጣልኝ።
ለጭንቀቴም፡ የሚራራ፡
ጸራቅሊጦስ፡ መጣልኝ።
ለንስሐ፡ ይጠራኛል፡

በእውነትም፡ ይመራኛል፡
በልቤም፡ አደረልኝ።

፮፡ በአምላኬን፡ ምሕረት፡
ምሉ፡ መዳን፡ አገኘን።
ከሰጠኑ፡ ይህን፡ ረድኤት፡
በአምላክ፡ ተስፋ፡ አለን።
እኛን፡ በርኅራኄ፡ ምሮ፡
የሰይጣንንም፡ ኃይል፡ ሽሮ፡
በክርስቶስ፡ ሞት፡ አዳነን።

ረሰቲነ።

፯፡

S. T. 480.

፩፡ በጸጋው፡ እግዚአብሔር፡
የጠፋውን፡ ሰው፡ አዳነ።
ልጁንም፡ ወደዚች፡ ምድር፡
ላከ፡ ሊያድነኑ።
ዓለም፡ በኃጢአት፡ ብዛት፡
ሰጥሞ፡ ጠፍቶ፡ ነበር።
ጽድቅና፡ ሕይወት፡
የአምላክ፡ ልጅ፡ ባይሞት፡
ባልተገኘልን፡ ነበር።

፪፡ ወልድም፡ በዓለም፡ ላይ፡ ሊፈርድ፡
አልመጣም፡ ወደ፡ እኛ፡
የፍርድ፡ መዓት፡ ግን፡ እንዲበርድ፡
ተሠዋ፡ ያለም፡ ዳኛ።
ጠፍቶ፡ የነበር፡ ብዕዕናም፡
ከአብ፡ በወልድ፡ ተሰጠን፡
ተመለስልን።
በርሱም፡ የሚያምን፡
ይድናል፡ ለዘላለም።

፫፡ በክርስቶስ፡ ግን፡ ያላመነ፡
አሁን፡ ተፈረደበት።
በራሱ፡ እርሱ፡ ኰነነ፡
ጥፋቱም፡ አይቀርለት።
የረገጠ፡ የወልድን፡ ደም፡
ብዕዕናን፡ አያገኝም።
የአምላክ፡ በግም፡
ያስፈርድበታል፡
ሰማይንም፡ ይነሣል።

፬፡ ጌታችን፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሆይ፡
ነፍስህን፡ ለወጥህልን።
በሞት፡ ጽላ፡ እንዳንቆይ፡

በመስቀል፡ ላይ፡ ሞትህልን።
አ፡ አምላክ፡ ጸጋህ፡ በዝትዋል።
አ፡ ያምላክ፡ ልጅ፡ ተመስገን።
በምድር፡ ሳለን፡
ምስጋናህ፡ አንሥዋል፡
በዚያ፡ ግን፡ ይደምቃል።

ረሱቲን።

፯፡

S. T. 439; 442.

፩፡ አምላክ፡ በምሕረቱ፡ ብዛት፡
ለሕይወት፡ መረጠኑ።
በልጁም፡ ደም፡ ከኃጢአት፡
በጸጋው፡ አጠበኑ።
ትምክሕታችን፡ ቀርትዋል፡
ዕዳችንም፡ ከብዶብናል፡
ጸጋን፡ መለመን፡ ግድ፡ ነው።

፪፡ የአምላክ፡ ትእዛዝ፡ ቅዱስ፡ ነው፡
መታዘዝ፡ ግን፡ አቃተን።
ከበለሱ፡ የለቀመው፡
ሁላችንን፡ አሳተን።
ከአዳም፡ የሚወለድም፡

ያምላክን፡ ሕግ፡ ፈቃዱንም፡
ሊፈጽም፡ አቅም፡ አጣ።

፫፡ ሕግ፡ ሁሉ፡ እስኪፈጸም፡ ግን፡
ከፍርዱ፡ አንድንም።
ጽድቅ፡ ካላገኘን፡ በፍርድ፡ ቀን፡
አምላክ፡ ይቅር፡ አይለንም።
ተመስገን፡ ጌታ፡ ልጅህን፡
ከዚህ፡ ጥፋት፡ ሊያድነን፡
በምሕረትህ፡ ላክህልን።

፬፡ ያለምን፡ ሁሉ፡ ኃጢአት፡
ሊሸከም፡ የመጣልን፡
የአምላክ፡ ልጅ፡ በትሩፋት፡
አሪትን፡ ፈጸመልን።
እርሱንም፡ በተቀበለው፡
ያ፡ መድኀኒ፡ የፈጸመው፡
የአምላክ፡ ሕግ፡ አይፈርድም።

፭፡ የአቅማችንን፡ ድክም፡
ተረድተን፡ በመድኀኒ፡
በፈጸመልንም፡ ሕማም፡
በደሙም፡ ኃይል፡ ስናምን፡
ጽድቁ፡ ይቈጠርልናል፡

በምላክም፡ ፊት፡ ያጸድቀናል፡
ልጆቹም፡ ያደርገናል።

፮፡ ልጆች፡ ከሆነ፡ መንፈስም፡
ልባችንን፡ ይገዛል።
ዛፍ፡ መልክም፡ ከተደረገም፡
መልካሙን፡ ፍሬ፡ ያፈራል።
እምነት፡ ቢኖረን፡ ፍቅርም፡
አይቀርም፡ ባልንጀራውንም፡
ምዕመኑ፡ ይወዳል።

፯፡ አምላክ፡ እንዲህ፡ እኛን፡ ኃጥአን፡
በምሕረቱ፡ አዳነ።
ጸጋውንም፡ ለምዕመናን፡
ሊሰጥ፡ ፈቃዱ፡ ሆነ።
በእኛ፡ ጕድለት፡ ብቻ፡ ነው።
ጽድቃችን፡ ሁሉ፡ የሱስ፡ ነው።
እርሱንም፡ እናመስግን።

ረሰቲን።

፸፱፡

S. T. 443.

፩፡ መድኀኒት፡ ተገኘልን፡
ከአብ፡ ተልከዋል።

ወልድም፡ እኛን፡ ሊያድን፡
ወዳለም፡ መጥትዋል።
በኃጢአት፡ ለሞቱ፡
በጨለማም፡ ለኖሩ፡
መዳንን፡ ሰጥትዋል።

፪፡ ሰው፡ ሁኖ፡ እርሱ፡ መጣ፤
የጸጋ፡ ዘመንም፡
ለምድር፡ ልጆች፡ ወጣ፡
ሰላም፡ ተሰጠንም።
የሞትም፡ ኃይል፡ ተሻረ፡
የጠፋውም፡ ልጅ፡ ተማረ፡
ሰማይ፡ ተከፈተም።

፫፡ አ፡ ክርስቶስ፡ በቸርነት፡
ብርሃንህን፡ ስጠን።
ከዓለምም፡ ከንቱነት፡
በፍቅርህ፡ አድነን።
በእምነት፡ እንድናይህ፡
ስጠን፡ ስለ፡ ሥቃይህ፡
የጽድቅህን፡ ሕይወት።

፬፡ ከአባትህ፡ ተሰጠህ፡
በሁሉ፡ ላይ፡ ሥልጣን።

አንተም፡ በደምህ፡ ዋጀህ፡
የሕዝብህን፡ መዳን።
ሰማይን፡ ታወርሳለህ፡
ብዕዕናም፡ ትሰጣለህ፡
በመንግሥትህ፡ ብርሃን።

፭፡ ከአብ፡ ያገኘኸውንም፡
ማዳን፡ ፈቃድህ፡ ነው።
የጠፋውን፡ መንጋህንም፡
ለሕይወት፡ መረጥኸው።
አ፡ የሱስ፡ ለኔም፡ ራራ፡
እኔንም፡ ከንተ፡ ጋራ፡
በመንግሥትህ፡ አኑር።

ረሱቲን።

ሽቺ፡

S. T. 439; 442.

፩፡ ለዓለም፡ ሕይወት፡ ልትዋጅ፡
ሥጋችንን፡ የለበስህ፡
ተስፋችንን፡ ልታዘጋጅ፡
አ፡ የሱስ፡ ሞትን፡ ቀመስህ።
ያላንተ፡ ግን፡ በጠፋነ፡

ሲያል፡ ተከፈተብኝ፡
ሞትም፡ ርስታችን፡ ነበር።

፪፡ አንተም፡ ስታይ፡ የኛን፡ ጉዳት፡
በፍቅር፡ ራራህልን፡
ልታድነንም፡ ከጥፋት፡
ወዳለም፡ ወረድህልን።
ከአንተ፡ ሞትና፡ ሕማም፡
የእግዚአብሔር፡ ሰላም፡
አ፡ የሱስ፡ ተገኘልን።

፫፡ በትሩፋትህ፡ አምነን፡
ወዳምላክ፡ ስንመጣ፡
ምሉ፡ ይቅርታ፡ ሰጠኸን፡
በሕግ፡ እንዳንቀጣ።
እኛም፡ ይህን፡ ተቀብለን፡
በቅዱስ፡ ቃልህ፡ ታምነን፡
ከሞት፡ እንድናለን።

፬፡ ጥር፡ ወንድማችን፡ አንተ፡ ነህ፡
እንዴት፡ አክብረኸናል።
ዘላለም፡ ከኛ፡ ጋራ፡ ነህ፡
ሁሉንም፡ ሰጥተኸናል።
የዓለም፡ ስድብና፡ ጥል፡

ከቶ፡ ሊጎዳን፡ እንዳይችል፡
አምባችን፡ ያምላክ፡ ልጅ፡ ነው።

፭፡ ግሩም፡ ጸጋህን፡ የሰጠኸን፡
መድኃኒት፡ ሆይ፡ ተወደስ።
ከአንተ፡ ጋራ፡ ልጆች፡ ነን፡
አ፡ ጌታ፡ የሱስ፡ ክርስቶስ።
አምላክን፡ እናመስግንም፡
እርሱ፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡
ቸር፡ አባታችን፡ ሆነ።

ረስቲን።

ኛይ፡

S. T. 82; 280.

፩፡ አዳም፡ በውድቀቱ፡ ያወረደብን፡
ሁሉ፡ በሴት፡ ዘር፡ ተፈውስዋል።
ክርስቶስ፡ በመስቀሉም፡ ላይ፡ ሲሞትልን፡
ኃጢአታችንን፡ አርቅዋል።
በእንጨት፡ ላይ፡
የሞት፡ ሥቃይ፡
ቅዱሱ፡ ስለ፡ ኃጥአን፡ ቀምስዋል።

፪፡ ደሜን፡ ሥጋዬንም፡ እንኩ፡ ውሰዱ።
ይህ፡ ነው፡ የኃጢአታችሁ፡ ሥርየት፡

አለና፣ ወደ፣ ሕማም፣ በመሔዱ፣
አወረደልን፣ የአብን፣ ሥምረት።
ግሩም፣ ጭንቁንም፣
መስቀሉንም፣
ተሸክሞልን፣ ቀጀልን፣ ሥርየት።

፫፡ አበሳህም፣ እንደ፣ ቅርምዝ፣ ቢሆንም፣
በቅዱስ፣ ደሙ፣ መጥራት፣ ይችላል።
የሱስ፣ በመስቀል፣ ከሞተ፣ መዳንም፣
ጽድቅም፣ ብዕዕናም፣ ተሰጥቶናል።
የርሱን፣ ሥቃይ፣
በምነት፣ ብታይ፣
ከሞት፣ ከመቅሠፍትም፣ ያድንሃል።

፬፡ ግን፣ የመድኃኒቱን፣ ደም፣ የሚንቁ፣
ፍርድን፣ ሳይፈሩ፣ የጸጋን፣ ብዛት፣
ችላ፣ እያሉ፣ ከየሱስ፣ ሲርቁ፣
ምን፣ ያድናቸው፣ ይሆን፣ ከጥፋት፣
የናቁትን፣
ቸር፣ መድኅንን፣
ግርማውን፣ ሲለብስ፣ ያዩታል፣ በፍርሃት።

፭፡ አ፣ ጌታ፣ የሱስ፣ በቅዱስ፣ ሕማምህ፣
ኃጢአተኞችን፣ አድነሃል።

ለመንፈሳችን፣ እረፍት፣ በድካምህ፣
እንድትሰጠን፣ ተጨንቀሃል።
ሁላችንን፣
ልታድነን፣
በቅዱስ፣ መስቀልህ፣ ገዝተኸናል።

፯፡ አንተ፣ በጎልጎታ፣ ላይ፣ የሞትህልን፣
አ፣ የሱስ፣ ክርስቶስ፣ ለማመን፣ እርዳን።
የሠራህልንንም፣ ግለጥልን፣
እኛም፣ በመስቀልህ፣ ኃይል፣ እንዳን።
መስቀልህም፣
ለዘላለም፣
ተስፋና፣ ሕይወት፣ ሊሰጠን፣ ይብቃን።

ረሰቲን።

፸፩፣

S. T. 437; Ahnf. 41.

፩፡ ወንጌል፣ የሚለውን፣ ሰምቼ፣
ደስታዬ፣ ምሉ፣ ነው።
ከአምላክ፣ ርስት፣ ተቀብዬ፣
ምስጋናዬን፣ ልስጠው።
የአምላክ፣ ልጅ፣ ተዛምዶናል፣

መድኃኒታችን፡ ሁንዋል፡
ደስታዬም፡ ምሉ፡ ነው።

፪፡ እሁን፡ የምድሩ፡ ሕማም፡
በጣም፡ ቢበዛኝም፡
የልቤ፡ ኃይል፡ የነፍስ፡ ሰላም፡
ሁሉም፡ ቢጠፉኝም፡
ግን፡ አምላክ፡ በሰማይ፡ ዙፋን፡
ሲሰጥ፡ ለወንድሜ፡ ሥልጣን፡
መዳኔ፡ እርግጥ፡ ነው።

፫፡ ይህ፡ የዘላለም፡ ምክር፡ ነው፡
የጸጋ፡ ምሥጢርም፡
የአምላክ፡ ልጅ፡ ቤዛችን፡ ነው፡
ያፈሰል፡ ደሙንም።
አ፡ ግሩም፡ የሆነ፡ ዘመዴ፡
ሲሞት፡ ጠፋልኝ፡ ዕዳዬ፡
ደስታዬም፡ ምሉ፡ ነው።

፬፡ የአዳም፡ ርስት፡ በባሕርዩ፡
ስወርስው፡ ታሠርሁ።
በክርስቶስ፡ ግን፡ በመድኀኔ፡
አርነት፡ ወጣሁ።
የአምላክ፡ ልጅ፡ ሰው፡ ሁኖልኝ፡

ነፍሱን፡ ሲሰጥ፡ ሊያድነኝ፡
ደስታዬ፡ ምሉ፡ ነው።

፭፡ እንዲህ፡ ከሆነ፡ ማመንን፡
ልተው፡ አልደፍርም።
የሰጠውም፡ መሥዋዕትን፡
ልንቀው፡ አልችልም።
ጥፋቴ፡ ቢበዛብኝም፡
ይበልጣል፡ ግን፡ የበጉ፡ ደም፡
ደስታዬም፡ ምሉ፡ ነው።

ረስቲን።

፺፩፡

S. T. 141.

፩፡ የምስራችን፡
ሰምተሀ፡ አመን።
የሱስ፡ ፈጽሞ፡ አዳነን።
ሰውን፡ ሊያድን፡ በምሕረት፡
ነው፡ የጥንቱ፡ የአብ፡ ሥምረት።
ወልድም፡ ዋጀልን፡ ስርየት።

፪፡ የምስራችን፡
ሰምተሀ፡ አመን።
የሱስ፡ ፈጽሞ፡ አዳነን።

ብቻውን፡ ሁኖ፡ ድል፡ ነሥትዋል።
የእባብን፡ ራስ፡ ረግጥዋል።
ሰማይን፡ ከፍቶልናል።

፫፡ የምስራችን፡
ሰምተህ፡ አመን።
የሱስ፡ ፈጽሞ፡ አዳነን።
ሕግ፡ ሊሠራ፡ የማይችለውን፡
በንተም፡ ውስጥ፡ የሚነቅፈውን፡
የሱስ፡ ተሸክሞታል።

፬፡ የምስራችን፡
ሰምተህ፡ አመን።
የሱስ፡ ፈጽሞ፡ አዳነን።
ኃጢአትህ፡ ከብዶብሃል፡
መርገምም፡ ተጭኖብሃል፡
የሱስ፡ ግን፡ አድኖሃል።

፭፡ የምስራችን፡
ሰምተህ፡ አመን።
የሱስ፡ ፈጽሞ፡ አዳነን።
ርኩስ፡ ኃጢአተኛ፡ ነህ።
የሱስ፡ ግን፡ ስለወደደህ፡
ክምላክ፡ ጋር፡ አስታረቀህ።

፮፡ ተቀብለህ፡
ደስ፡ ይበልህ፡
የሱስ፡ ሁሉ፡ ሲሆንልህ።
ሁሉን፡ የሚያስፈልገው፡
በመድኃኒቱ፡ ያገኘው፡
ጻድቅም፡ ቅዱስም፡ ነው።

፯፡ ተቀብለህ፡
ደስ፡ ይበልህ፡
የሱስ፡ ሁሉ፡ ሲሆንልህ።
ስትጨነቅ፡ ይጦርሃል፡
በይታይልህም፡ ቀርቦልሃል፡
በጄም፡ ይሸከምሃል።

፰፡ ተቀብለህ፡
ደስ፡ ይበልህ፡
የሱስ፡ ሁሉ፡ ሲሆንልህ።
እንግድነትና፡ ድካም፡
አርቆልህ፡ ያሳርፍሃል፡
በሰማያዊ፡ ሰላም።

፸፯፡

S. T. 559. AhnF. 15.

፩፡ ፈርዖን፡ የእሥራኤል፡ ጠላት፡
በባሕር፡ እንደቀረ፡
እንዲሁም፡ ያለም፡ ኃጢአት፡
— እ፡ ተአምራት፡ —
በክርስቶስ፡ ደም፡ ተሻረ።

፪፡ በባሕር፡ የተጣለ፡ ፍም፡
ትሎ፡ እንደሚጠፋ፡
ጠፋልን፡ መከራችንም፡
ተቀበረም፡
ከእንግዲህ፡ አይገኝም።

፫፡ ተፈጸመና፡ ዓለሙ፡
ከከባድ፡ ዕዳው፡ ዳነ።
ቢጠጋም፡ ወደ፡ መስቀሉ፡
በእምነቱ፡
ዕለቱን፡ ብፀዕ፡ ሆነ።

፬፡ ምዕመንም፡ የምስራቱን፡
ይቀበላል፡ ተደንቆ።
ሌላም፡ ይሰማል፡ ነገሩን፡

ግን፡ ምሥጢሩን፡
አያውቅም፡ ቃሉን፡ አውቆ።

፭፡ ግን፡ ስለም፡ አንዱ፡ እኔ፡ ነኝ፡
ስለኔም፡ የሱስ፡ ሞተ።
በጽድቁም፡ ስለሸፈነኝ፡
አጸደቀኝ፡
ከኃጢአቴ፡ ሁሉ።

፮፡ የሰይጣን፡ ፍትወት፡ በልቤ፡
እስከማይቻል፡ ቢሆንም፡
ሰላም፡ ላግኝ፡ ከችግሬ፡
በመድኀኔ፡
ከሞት፡ ፍርሃት፡ ልዳንም።

ረስቲን።

፸፰፡

S. T. 422.

፩፡ መድኃኒት፡ ተገኘልን፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ደም።
ከአምላክ፡ ጋራም፡ ዕርቅ፡ ተደረገልን።
ለምንስ፡ እንጨነቅ፡ አገኘኑ፡ ሰላም፡
የጥል፡ ግድግዳም፡ ፍጹም፡ ፈረሰልን።
አዙንስ፡ ቀኑ፡ ነጋ፡ ሌሊትም፡ አልፍዋል።

ኃላም፡ በጽድቁ፡ አንተን፡ የሚፈልግ፡
ምሀረትህ፡ የሚገባው፡ ሊሆን፡ ተዳክሞ፡
በራሱ፡ አቅም፡ ተስፋ፡ የሚያደርግ፡
ያ፡ ሥስኪን፡ ሰው፡ ይስታል፡ ጽድቅንም፡ አ
|ጥቶ፡
ምሕረትህንም፡ ያጣል፡ ወዳንተም፡ መጥቶ፡
በጽድቅህ፡ ጽድቁን፡ ሊያገኝ፡ አይቻለውም።

፫፡ ኃጥአንን፡ ሁሉ፡ እንጅ፡ ጻድቃንን፡ ለመ
|ጥራት፡
መድኃኒታችን፡ ወደዚህ፡ አልመጣም።
የታመመው፡ ሰይድንም፡ መድኃኒት፡ ለመ
|ሻት፡
ደቀርብ፡ በሐኪም፡ ከቶ፡ አልተቀጣም።
እኔም፡ አ፡የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወዳንተ፡ መጥቼ፡
የፈለግሁትን፡ ሁሉ፡ በከንቱ፡ አግኝቼ፡
በደስታ፡ ቅዱስ፡ ስምህን፡ ላመስግን።

፮፡ ዓለምም፡ ሰይመሠረት፡ በምረሐትህ፡ ፈቃድ፡
ልጅህ፡ ልሆን፡ በየሱስ፡ መርጠኸኛል።
ሥምረትህም፡ አ፡ አምላክ፡ አሁን፡ እንዴት፡
|ይከድ፡
በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሁሉን፡ ሰጥተኸኛል።

ተማረክ፡ ኃይለኛው፡ ምርኮኛውም፡ ይፈታል።
በክርስቶስ፡ መስቀል፡ አምላክ፡ ታረቀን።

፪፡ አምላክ፡ ከታረቀኝም፡ በየሱስ፡ ልጁ፡ ነኝ።
ልጅነት፡ ተዋጀልኝ፡ በሕማሙ።
አ፡ አምላኬ፡ በክርስቶስ፡ ከጥንት፡ ከወደድ
|ኸኝ፡
የመንግሥትህ፡ ወራሽ፡ ነኝ፡ ስለስሙ።
በባርያ፡ መንፈስ፡ ተይዤ፡ ለጽድቅ፡ የማስንሁ፡
የጸጋህን፡ ስጦታ፡ ልገዛው፡ ያሰብሁ፡
እኔ፡ በየሱስ፡ ብቻ፡ ልጅህ፡ ሆንሁ።

፫፡ ምንደኞች፡ ሁነን፡ ሠርተን፡ ደመወዝን፡
|ብናገኝ፡
ልጅነት፡ አኗኝም፡ በሥራችን።
መድኃኒት፡ ሆይ፡ በጽድቅህ፡ አንተ፡ ከጸደ
|ቅኸኝ፡
አሮጌ፡ ጨርቅ፡ አያርክስ፡ አዲስ፡ ልብሴን።
እኔ፡ ሁለንትናዬ፡ ፍጹም፡ የረከስሁ፡
በአንተ፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ፍጹም፡ ተቀደስሁ።
የራሴን፡ ጽድቅ፡ ከጉድፍ፡ ልቀጠረው።

፬፡ ፈተ፡ ኃጢአቱን፡ ነቅሎ፡ ጽድቁንም፡ ፈ
|ጽሞ፡

የምክርህን፡ ምሥጢር፡ በቃልህ፡ ገለጥኸው።
የሰው፡ መዳን፡ አ፡ አምላክ፡ በጸጋ፡ ብቻ፡ ነው።
እኔም፡ በጸጋህ፡ ብቻ፡ እመካለሁ።

ረስቲን።

፸፱፡

S. T. 196.

፩፡ መድኃኒቴን፡ ብቻ፡ ተስፋ፡ ሲያደርገው፡
በየሱስ፡ የሚያምን፡ በእርግጥ፡ ብፁዕ፡ ነው።

፪፡ ድካም፡ ጕስቍልናም፡ ቢያስደነግጠው፡
በወንጌል፡ የተሰጠ፡ መጽናናቱ፡ ይብቃው።

፫፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ክርስቶስ፡ በግልጥ፡ ይታ-
ሌላ፡ ጊዜ፡ ግን፡ ፍጹም፡ ይሠወርብናል | የናል፡

፬፡ ግን፡ በሕሊናችን፡ እንዲህ፡ ሲለወጥም፡
ከየሱስ፡ የተሰጠን፡ ሰላም፡ አይናወጥም።

፭፡ በየሱስ፡ መሞት፡ አምላክ፡ እንደታረቀን፡
መጽናናት፡ ሊሆንልን፡ ወንጌሉ፡ ነገረን።

፮፡ በደሙ፡ መድኃኒትም፡ ተገኝቶልናል፡
ይህንም፡ ላለም፡ ሁሉ፡ መግለጥ፡ ያስመኝናል።

፯፡ ዘወትር፡ የአምላክ፡ ውዳጅ፡ ከመሆን፡
የበለጠ፡ ብዕዕና፡ ወዴት፡ ይገኝ፡ ይሆን፡

፰፡ እስከንተያይህ፡ በጭንቀት፡ ስንኖር፡
አ፡ የሱስ፡ ይህ፡ ሰላምህ፡ ልባችንን፡ ይጠር።

ረስቲን።

፹፡

S. T. 616.

፩፡ ኃጢአተኞችን፡ እንዲያድን፡
መድኃኒታችን፡ ተልከዋል።
ያን፡ ጥልቅ፡ የአምላክ፡ ምሥጢር፡ ለማመን፡
ያን፡ ቃል፡ መቀበል፡ ይገባናል።

፪፡ አሁን፡ በዓለም፡ ወንጌል፡ ይሰፋል።
መስፋቱን፡ ማን፡ ይከለክላል፡
ያ፡ ሰማያዊ፡ እሳት፡ ይነዳል፡
በርሃን፡ በሌሊት፡ ይሰጠናል።

፫፡ በየሱስ፡ ኃይል፡ ዕውራን፡ ያያሉ፡
የዲዳ፡ አፍም፡ ይናገራል»
በደስታ፡ ሽበትም፡ ይዘላሉ፡
ከሞት፡ አልዓዛር፡ ይመለሳል።

፬፡ በዚህ፡ የወደቀውን፡ ደረቅ፡ ጉልጥምት፡
አ፡ ጌታ፡ የሱስ፡ ተመልከተው።
የሕይወት፡ መንፈስ፡ የሞተውን፡ አዋንት።
ሥጋን፡ ድማትንም፡ ያልብሰው።

፭፡ ሰማይን፡ ቀደህ፡ በወረድህልን።
አለት፡ ይሰበር፡ ደንጋይ፡ ይቅለጥ።
በበረሐ፡ መናን፡ አውርድልን፡
የመስቀልህንም፡ ኃይል፡ ግለጥ።

፮፡ በእግርህ፡ ታች፡ አሕዛብ፡ ይስገዱ።
የአልጋህ፡ ግርማ፡ በዚህ፡ ይምላ።
ከጸጋ፡ ምንጭ፡ ሕይወትን፡ ይውሰዱ።
ስምህ፡ ይቀደስ። ሃሌሉያ።

አኖ፡ ሌኖ።

፴፩፡

S. T. 41.

፩፡ የሱስ፡ ለዓለም፡ ሲል፡ ሙትዋል።
አምላክ፡ ስጠኝ፡ ቅዱስ፡ ማስተዋል።
እንድድንበት፡ ከኩነኔ፡
አርሱ፡ በመስቀል፡ ሞተ፡ ለኔ።

፪፡ እንዴት፡ ይገርማል፡ ታላቅ፡ ፍቅሩ።

ማንም፡ አይወደኝ፡ እንደ፡ አርሱ።
አርሱ፡ ከዳንኝ፡ በመሞቱ፡
ሕይወቴን፡ ልስጠው፡ ለክብረቱ።

፫፡ አምላኬ፡ ሆይ፡ ልጅህ፡ አድርገኝ።
ከሰይጣን፡ ወጽመድ፡ ሁሉ፡ ፍታኝ።
አንተን፡ ልከተል፡ አስተምረኝ፡
ላንተም፡ ልሆን፡ በፍቅርህ፡ አርዳኝ።

፯ስቲን።

፴፪፡

S. T. 633.

፩፡ የተሰቀለው፡ መድኅን፡ ለነፍስህ፡ ቢታይ፡
ይሆንልሃል፡ ምሉ፡ መዳን።
ና፡ ተመልከት፡ ሲሣቀይ፡ በመስቀሉ፡ ላይ፡
ሲሸርም፡ የሞትን፡ ሥልጣን።
እይ፡ እይና፡ ዳን።
የተሰቀለውን፡ መድኅን፡ በእምነት፡ ብታይ፡
ይሆንልሃል፡ ምሉ፡ መዳን።

፪፡ ብትጦም፡ ብትጸልይም፡ እንበህ፡ ሲፈስ፡
ያ፡ አይበቃም፡ ለነፍስህ፡ መዳን።
የመድኃኒቱ፡ ደም፡ ግን፡ በመስቀል፡ ሲፈስ፡

ተፈጸመ፡ የኛ፡ መዳን።
እይ፡ እይና፡ . . . . ።

፫፡ ኃጢአትህ፡ በላይህ፡ የቀረ፡ ቢሆን፡
የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ለምን፡ ተቀሠፈ፡
የተቀደሰ፡ ደሙም፡ ባይከፍል፡ ዕዳህን፡
ከንቱስ፡ ለምን፡ ጐረፈ፡
እይ፡ እይና፡ . . . . ።

፬፡ ትሩፋቱን፡ ተቀበል፡ በስሙም፡ እመን፡
የመድኃኒቱን፡ ደም፡ አትናቅ።
በተሠዋ፡ ጊዜ፡ በተሰቀለም፡ ቀን፡
ከሞት፡ እንዳዳነህ፡ እወቅ።
እይ፡ እይና፡ . . . . ።

ረሱቲን።

፴፫፡

S. T. 630.

፩፡ ዕዳችን፡ ቀረ፡ ድልም፡ ተሰጠ፡
ዓመፃም፡ ጠፋ፡ ጽድቅም፡ ተገኘ።
የአምላክ፡ ሕግ፡ እንዳይረግመን፡
ክርስቶስ፡ በሞቱ፡ አዳነን።
ሰው፡ ሆይ፡ ስማ፡ እመን፡ የምስራችን።
ክርስቶስ፡ ሲሞት፡ ተገዛን፡ ሁላችን።

ደሙ፡ በመስቀል፡ ከፈሰሰ፡
ዕዳችን፡ ተደመሰሰ።

፪፡ ክርስቶስ፡ ዋጀልን፡ የፍርድ፡ ነጻነት፡
ከኃጢአትም፡ ቀምበር፡ አርነት።
ወደኔ፡ ኑ፡ ብሎ፡ ያድማል፡
አማኝም፡ ሁሉ፡ ይድናል።
ሰው፡ ሆይ፡ ስማ። . . . ።

፫፡ ልጆች፡ ከሆነ፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡
በርሱ፡ አለነ፡ የአምላክ፡ ሞገስ።
ኃይሉም፡ ከውድቀት፡ ዓድነናል።
ወደ፡ ሰማይም፡ ያደርሳል፡
ሰው፡ ሆይ፡ ስማ። . . . ።

ረሱቲን።

፴፬፡

S. T. 78.

፩፡ የዋንት፡ አምባ፡ ጥግ፡ ሁነኝ፡
ከለላህ፡ ይሠውረኝ።
ከተወጋው፡ ጐድንህም፡
የሚፈልቅ፡ ውኃና፡ ደም፡
ከክፋቴ፡ ያጥራኝ፡
ከጥፋትም፡ ያድነኝ።

፫፡ ሕግህን፡ መፈጸሙ፡
አቅቶኝ፡ ተሸነፍሁ።
ሌትም፡ ቀንም፡ አልቅሼ፡
አልጠራልኝም፡ እድፌ፡
አንተ፡ ብቻ፡ ተስፋዬ፡
ያድነኝ፡ ከከሠኔ።

፬፡ የምስጥህ፡ የለኝም፡
ጽድቅ፡ አልተገንብኝም።
አንተ፡ ብቻ፡ ጽድቅ፡ ሁነኝ፡
ጸጋህ፡ ብቻ፡ ዓድነኝ፡
ቅዱስ፡ ደምህ፡ አምላኬ፡
ይሁንልኝ፡ ሕይወቴ።

፭፡ የፍርድ፡ ዕለትም፡ ሲደርስ፡
ምድራችንም፡ ሲፈርስ፡
ዓለም፡ ካይንህ፡ ፊት፡ ሲቀልጥ፡
ጽድቅህንም፡ ስትገልጥ፡
የጥንት፡ አምፀ፡ ጥፋ፡ ሁነኝ፡
ከለላህ፡ ይሠውረኝ።

ረቡዕን።

ዐቢይ፡

S. T. 156.

፩፡ እንዴት፡ የሚገርም፡ ነው፡ አ፡ቸር፡ መድኃኔ፡
በደሞህ፡ መድኃኒት፡ ተገኘ፡ ለኔ።
ከፍርድ፡ ከቅጣትም፡ ነጻነት፡ ላገኝ፡
የመድኃኒቴ፡ ቍስል፡ ከሞት፡ ፈወሰኝ።
ታላቅ፡ ነው፡ ፍቅሩ፡
ዕሙንም፡ ምክሩ።
ጸጋውንም፡ ዘምሩ።
ይስፋ፡ ክብሩ።

፪፡ እንዴት፡ ግሩም፡ ነው፡ የሱስ፡ ተሰዋቶኛል፡
እርሱም፡ በቸርነት፡ ተቀብሎኛል።
አርነት፡ አወጣኝ፡ ከሰይጣን፡ ሥልጣን፡
ድኜም፡ ልመላለስ፡ በፊቱ፡ ብርሃን።
ታላቅ፡ ነው፡ . . . . ።

፫፡ አ፡ መድኃኔ፡ ደምህ፡ እንዴት፡ ክ፡ር፡ ነው።
ለቍስሌ፡ ሁሉ፡ መድኃኒቱ፡ ነው፡
ሥቃዬንም፡ ሁሉ፡ ይፈውሰዋል፡
እንቤንም፡ መድኃኒቴ፡ ያብስዋል።
ታላቅ፡ ነው፡ . . . . ።

፬፡ ለኔ፡ የተሰቀልኽው፡ ላመስግንህ።
አ፡ ጌታዬ፡ አምላኬም፡ ንጉሤ፡ ነህ።
ሥጋዬም፡ ሲቀበር፡ በተስፋ፡ ልረፍ፡
የማዳንህን፡ ኃይል፡ ለመመልከት፡ ልትረፍ።
ታላቅ፡ ነው፡ . . . . ።

ረሰቲን።

ፀሳኔ፡

ሮሜ፡ ፫።

Haeffn. 126.

፭፡ ያምላክ፡ ጸጋ፡ ታላቅ፡ ነው፡
ሰው፡ የሆነውን፡ ሁሉ፡ ጠራ።
ያለ፡ አድልዎም፡ ለሰው፡
በማይመሰን፡ ምሕረት፡ ራራ።
ምሕረቱም፡ ሲያድናቸው፡
ያዳም፡ ልጆች፡ እኩል፡ ናቸው።

፮፡ ሁሉ፡ ግፍ፡ አደረጉ፡
ሁሉም፡ ኃጢአትን፡ ሠረ።
አምላክን፡ ሳይፈልጉ፡
ጽድቅን፡ ሳያገኙም፡ ቀሩ።
ምኞትም፡ በባሕርያቸው፡
አንድ፡ ሳይቀር፡ አሸነፋቸው።

፫፡ ሁሉም፡ እንደወዳቂ፡
ሁሉም፡ ኃጥአን፡ እንደሆኑ፡
ሁሉ፡ ደግሞ፡ ጸደቁ፡
ሁሉም፡ በምላክ፡ ጸጋ፡ ዳኑ።
ጸጋውም፡ ብቻ፡ ጽድቅ፡ ሲሰጥም፡
ትምክሕት፡ ለማንም፡ የለም።

፬፡ በግዘት፡ ቤት፡ ታሥሮ፡
መቅሠፍት፡ የተፈረደበት፡
መጽሐፍም፡ ተምሮ፡
እውቀቱ፡ የሚደምቅለት፡
ልዩነት፡ ሳይኖር፡ ሁለቱ፡
ይድናሉ፡ በምሕረቱ።

፭፡ ጽድቅ፡ የሹት፡ ምዕመናን፡
ፍጹም፡ ላምላክ፡ የተሰጡ፡
የተዋረዱም፡ ኃጥአን፡
ወደ፡ መስቀሉ፡ ቢመጡ፡
ሳይለያዩ፡ እኒህ፡ ሁሉ፡
በምላክ፡ ጸጋ፡ ይድናሉ።

፮፡ በክፋቱ፡ አገሩን፡
በምግባሩም፡ የሚያፍር፡

ኃጢአቱን፡ አምኖ፡
ጸጋን፡ ማመን፡ የማይደፍር፡
ራሱን፡ ሊያጸድቅ፡ ሲሞክር፡
ከንቱ፡ ነው፡ የልቡ፡ ምክር።

፫፡ በሰው፡ ጽድቅና፡ ልፋት፡
ያምላክ፡ ጸጋ፡ አይሰናዳም።
የሰው፡ ሁሉ፡ ትሩፋት፡
ማንንም፡ ለዚህ፡ አይረዳም።
ሰው፡ በምሉ፡ ኃይል፡ ቢተጋም፡
ነፍሱን፡ ለማዳን፡ አይበቃም።

፬፡ የሱስ፡ ግን፡ በመስቀሉ፡
ለኛ፡ ጸጋን፡ አዘጋጀ።
ሞትን፡ በመቀበሉ፡
ሕይወት፡ ለነፍሳችን፡ ዋጀ።
ወደ፡ እርሱም፡ የሚመጣ፡
ይድናል፡ ከአምላክ፡ ቁጣ።

፭፡ በምስራቹ፡ ያመነ፡
በመድኃኒቱ፡ ይድናል።
ምሉ፡ ተስፋ፡ አለን።
መጽሐፍ፡ እንዲህ፡ ይለናል፡

ወልድ፡ ያለው፡ ሕይወት፡ አለው፡
ሕይወት፡ የለውም፡ ወልድ፡ ለሌለው።
፩ኛዮሐ፭።

የእግዝአብሔርን፡ጸጋ፡ስለ፡መቀበል።

ዝማሬ፡

S. T. 121.

፩፡ አዲስ፡ ያልተወለደ፡ ላዲስ፡ ሕይወት፡
ያምላክን፡ መንግሥት፡ አያይም።
ክርስቶስን፡ ያልያዘ፡ በልብ፡ ሃይማኖት፡
ወደ፡ ሰማይም፡ አይገባም።
ደጁም፡ ጠባብ፡ ነው፡ ተጋደል፡ ለመግባት።
ቀንም፡ አጭር፡ ነች፡ እንዳታባክናት።
ልትጥር፡ ያስፈልግሃል፡ በፍርሃት፡
እንዳይቀርብህ፡ ብዕዕናው።

፪፡ ሰምተህ፡ ከመዳን፡ ይከለክልሃል፡
ሰይጣን፡ ያ፡ ክፉ፡ ጠላትህ።
በለም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ያታልልሃል፡
እንዳትድን፡ ከጥፋትህ።
ድምጹን፡ አትስማ፡ ፍራው፡ ወዳጄ፡ ሆይ።

ከለም፡ ምንጮች፡ ራቅ፡ በዚያም፡ አትቆይ።
ንስሐ፡ ለማድረግም፡ አትዘገይ፡
የሱስ፡ በፍቅር፡ ሲጠራህ።

፫፡ በሰማይ፡ ለጻርህ፡ ለትግልህም፡
ምን፡ ያህል፡ ወረታ፡ አለህ።
ወዲያም፡ ከደረስህ፡ አይጸጽትህም፡
አክሊልህን፡ ታገኛለህ።
ስለዚህ፡ ተነሥ፡ አሁንም፡ ተዘጋጅ።
ይቀርብ ብሃል፡ የዓለሙ፡ ፈራጅ።
የሠርግ፡ ልብስ፡ ያለበሰው፡ በሰማይ፡ ደጅ፡
አስክ፡ ዘላለም፡ አይገባም።

፬፡ እውነተኛ፡ እምነት፡ በልብህ፡ ባይገኝ፡
ወደ፡ ሰማይ፡ አትደርስም።
የክርስቶስን፡ ጽድቅ፡ ልትለብስ፡ በትመኝ፡
ሕይወትንም፡ አትወርስም።
ልትድን፡ ከሆንህ፡ በእምነት፡ ብቻ፡ ነው።
የክርስቶስን፡ ጽድቅ፡ አሁን፡ ተቀበለው፡
የሱስም፡ በፍቅር፡ ሲጠራህ፡ ስማው፡
እርሱን፡ የሰማ፡ ይድናል።

፭፡ የሕይወትን፡ ዘውድ፡ እንዲጭን፡ ለመጣር፡
ዓለሙ፡ ሁሉ፡ ተጠራ።

ላንተም፡ ዘውድ፡ ተዋጀ፡ በየሱስ፡ ተግባር።
ላንተም፡ በፍቅሩ፡ ራራ።
ታላቁ፡ መሐሪ፡ ያዝንልሃል፡
እጁንም፡ በፍቅር፡ ዘርግቶልሃል።
ከእንቅልፍህም፡ ይቀሰቅስሃል፡
ብዕዕ፡ ነህ፡ ብትነቃለት።

ረስቲን።

፴፰፡

S. T. 138.

፩፡ ቀጭን፡ ሆነች፡ የሕይወት፡ ደጅ፡
ያች፡ መንገድ፡ ጠባብ፡ ናት።
ተጋደል፡ አንተ፡ የሰው፡ ልጅ፡
በዚያ፡ ለመግባት፡ በዚያ፡ ለመግባት።

፪፡ ሰማያት፡ ገና፡ አልመሉም፡
ስፍሮች፡ ገና፡ አሉ።
ደጆቹ፡ ስለ፡ የሱስ፡ ስም፡
ላንተ፡ ተከፈቱ፡ ላንተ፡ ተከፈቱ።

፫፡ በአምላክ፡ ፊት፡ ከሚቆሙ፡
ከብዙዓን፡ ጋራ፡
አሳብሮ፡ በምሕረቱ፡
አንተን፡ ሊያገባ፡ አንተን፡ ሊያገባ።

፬፡ በየሱስ፡ ልብ፡ በገነቱ፡
አለ፡ ገና፡ ስፍራ።
ይጠራኛል፡ በወንጌሉ፡
ወደ፡ ሰማይ፡ ደስታ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ደስታ።

፭፡ በዚህ፡ ኣገር፡ በጸጥታ፡
ተመችቶኝ፡ ልኖር።
ብዑዕ፡ እርሱ፡ የሚሰማ፡
የእምላክን፡ ምክር፡ የእምላክን፡ ምክር።

ሉንሂል።

፴፱፡

S. T. 449.

፩፡ በእውነት፡ ባንተ፡ ያመነው፡
ኦ፡ የሱስ፡ እርሱ፡ ብዑዕ፡ ነው።
ቤዛችን፡ አንተ፡ ሁነሃል፡
በአንተም፡ አብ፡ ይወደናል።

፪፡ የነፍሴ፡ ቤዛ፡ ለመሆን፡
በሞት፡ ሕማም፡ ያደረግኸውን፡
ያን፡ ሁሉ፡ ለኔ፡ አርገሃል፡
ባምላኬም፡ ፊት፡ ያጸድቀኛል።

፫፡ ከጸጋ፡ ሁሉ፡ የሚበልጥ፡

ከአምላክ፡ መቅሠፍት፡ እንዳመልጥ፡
ዕዳዬን፡ እንደከፈልኸው፡
በፍቅርህ፡ ስታስረዳኝ፡ ነው።

፬፡ በሞትህ፡ ኦ፡ መድኃኒቴ፡
ሕግንም፡ ፈጸምኸው፡ ለኔ።
ባንተም፡ ኦ፡ የሱስ፡ ካመንሁ፡
ምላትህን፡ ተካፈልሁ።

፭፡ ልጅነት፡ ባንተ፡ አግኝቼ፡
በድፍረት፡ ወደ፡ አባቴ፡
ልቀረብ፡ ከምድርም፡ ስለይ፡
ርስቴን፡ ልውረሰው፡ በሰማይ።

፮፡ ግን፡ ጌታ፡ ሆይ፡ ደክማ፡ ነኝ፡
በጸጋህ፡ ኃይል፡ አጠንክረኝ፡
ሰይጣን፡ እንዳያሸንፈኝ፡
ዘወትር፡ አንተ፡ ጠብቀኝ።

፯፡ የጀመርህልኝን፡ ሥራ፡
እስከ፡ ፍጻሜውም፡ ሥራ።
ወትሮም፡ በመንገድህ፡ ምራኝ፡
ወደ፡ ሰማይህም፡ ጥራኝ።

ረስጥን።

፵፡

S. T. 140.

፩፡ የሱስ፡ መድኃኒትህ፡ ልቡን፡ ከፍቶልህ፡
በቅፉ፡ ሊቀበልህ፡ ምኞቱ፡ ነው።
ምሉ፡ ደህንነትም፡ ከተገኘልህ፡
ስለምን፡ ጭንቂን፡ የምትመርጠው፡
ታላቅ፡ መሐሪው፡ አንተን፡ ይጠራል፡
ልብህን፡ ስጠኝ፡ በፍቅሩ፡ ይላል።
ስለምን፡ ጸጋው፡ በከንቱ፡ ይቀራል፡
ነፍሱንም፡ ላንተ፡ ሲል፡ ለውጥዋል።

፪፡ ጸድቅዋል፡ ዓለም፡ በጌታ፡ በየሱስ፡
የኃጢአት፡ መሥዋዕት፡ ቀርብዋል።
ቅዱሱ፡ ረከሰ፡ እኛን፡ ሊቀድስ፡
ሙቶም፡ ሁላችንን፡ አድኖናል።
ደሙ፡ ሲፈስ፡ ተደመሰሰ፡ ዕዳው፡
ኃጢአታችንም፡ ጠፍቶልናል።
ስለሥረዮች፡ ፈራጁ፡ ተቀጣ።
ታረቀ፡ አምላክ፡ ይበቃንማል።

፫፡ አሁን፡ ለኃጥአን፡ ብዕዕና፡ ተሰጠ፡
የበደላችን፡ እጥፍ፡ ሁንዋል።
አዳም፡ ሁላችንን፡ እንዳበላሸ፡

ክርስቶስ፡ ሁላችንን፡ አብዮትዋል።
ምሉ፡ አርነት፡ ያገኘቱ፡ ባሮች፡
ወደው፡ ሊገዙ፡ ይገባ፡ ይሆን፤
እኛስ፡ ይልቅ፡ ደስ፡ ብሎን፡ እንደ፡ ልጆች፡
ቸር፡ አባታችንን፡ እናመስግን።

፬፡ ፈቃር፡ መድኃኒቱ፡ ሆይ፡ ትሩፋትህ፡
ለኔ፡ ተሰጠና፡ የኔ፡ ይሁን።
ስሜ፡ ተጽፍዋል፡ በመጽሐፍህ፡
ከልቤም፡ አንሥተሃል፡ ሸክሙን።
አባትህን፡ ሳትክድ፡ ራስህንም፡
ስሜን፡ ከቀ፡ስልህ፡ አትፍቅም።
ፍቅርህን፡ ላክብረው፡ እንዲህ፡ ልበልም፡
ወጽመዱን፡ በጠስህ፡ አወጣኽኝም።

ረባጥን።

፵፩፡

S. T. 506; 157.

፩፡ የየሱስ፡ ልብ፡ ተከፈተልህ፡
በምሕረቱም፡ ይጠራሃል።
የምስኪኑ፡ ወዳጅ፡ ራራልህ፡
መድኃኒትም፡ ይሰዋሃል።

ቃሉን፡ አሁን፡ ስታደምጸው፡
ልብህን፡ አታደንዝዘው።

፪፡ አሁን፡ ይጠራሃል፡ በፍቅር፡
አሁን፡ መድኃኒታችን፡ ነው።
አንድ፡ ቀን፡ ግን፡ መጥቶ፡ በክብር፡
ሲጠራህ፡ ፈረጁች፡ ነው።
ዛሬ፡ እርሱን፡ ተቀብለህ፡
ለፍርድ፡ ሲጠራህ፡ ብፁዕ፡ ነህ።

ረስቲን።

፵፱፡

S. T. 132.

፩፡ የልብህን፡ በር፡ የሚመታ፡ ማን፡ ነው፤
ማን፡ ይጠራል፤
በደሙ፡ የገዛህ፡ መድኃኒትህ፡ ነው፡
በፍቅሩ፡ ለአንተም፡ ይራራል።

፪፡ በፈትም፡ ሲጠራህ፡ ሲፈልግህም፡
ሰምተሃል፡ ወይ፤
ለጌታህ፡ ለርኅሩኅ፡ መድኃኒትህም፡
የልብህን፡ በር፡ ከፍተሃል፡ ወይ፤

፫፡ የዓለም፡ ከንቱነት፡ የልብህን፡ ራብ፡

አያርቅም።
ወዳለምም፡ ደስታ፡ ፈቃድህ፡ ሲሳብ፡
መባበት፡ ከልብህ፡ አይለቅም።

፬፡ የዓለምን፡ ሁሉ፡ ብዕልና፡ ከብት፡
ብትወርስም፡
በምድሩ፡ ብኵ፡ ካገኘኸው፡ ሀብት፡
ሰላም፡ ወደ፡ ልብህ፡ አይደርስም።

፭፡ በሰው፡ ወዳጅነት፡ በዓለምም፡ ሽር፡
ብትመራ፡
ረድኤት፡ ስትሻ፡ ሳታገኝ፡ ብትቀር፡
ያጋልጡሃል፡ ስትጠራ።

፮፡ ግን፡ የሱስ፡ ቢሰጥህ፡ የእውነት፡ ሰላም፡
ለዘላለም፡
ከእርሱ፡ በቀር፡ ሌላ፡ ሀብት፡ አትሻም፡
አይተውህምም፡ በዚህ፡ ዓለም።

፯፡ የየሱስ፡ ወዳጅ፡ ከመሆን፡ የሚበልጥ፡
ምን፡ ይገኛል፤
የፍቅሩን፡ የጸጋውንም፡ መብለጥ፡ ሲገልጥ፡
ከእርሱ፡ በቀር፡ ምን፡ ያስመኛል፤

፰፡ ብዕዕናን፡ ሊሰጥህ፡ ለመጣው፡ ወዳጅ፡

ክፈትለት።
ለአንተም፡ ብዕዕናህን፡ ሲያዘጋጅ፡
የሰጠህን፡ ተቀበልለት።

ረሰቲን።

ማር፡

S. T. 711.

፩፡ ኑ፤ ደክሞች፡ ሁላችሁ፡
ወደ፡ ምሉ፡ ሰላም።
ሕይወት፡ የሚሰጣችሁ፡
ወረታ፡ አይሽም።
ግሩም፡ ነው፡ የምሕረተኛ፡
የፍቅሩ፡ ትሩፋት፡
የሚሰጠን፡ ለኛ፡
በጸጋው፡ ብዛት።

፪፡ የሱስን፡ እየው፡ ቆሙ፡
አሁን፡ ይጠራሃል።
ብትዘገይስ፡ ቆሙ፡
ዘመንህ፡ ያልፋል።
ፍቅሩን፡ አትናቀው፡
አሁን፡ ተቀበለው፡

ገዝቶሃልና፡ ለርሱ፡
ልብህን፡ ስጠው።

፫፡ ቸኩል፡ ወደርሱ፡ አሁን፡
አንተን፡ ይጠብቃል።
የተዘጋጀ፡ ክብሩን፡
ያቀርብልሃል።
በደ፡ ምስኪን፡ መሆንህን፡
እርሱ፡ በጣም፡ ያውቃል።
የሚያስፈልግህን፡
ወደ፡ ይሰጣል።

ተወልደ፡ ብርሃን።

ማይ፡

S. T. 143.

፩፡ የሱስ፡ ሲጠራህ፡ ወደ፡ ሰማይ፡
ቸኩል፡ ወደርሱ፡ ሳትዘገይ።
መንገዱንም፡ ያስተምርሃል፡
ፍቅሩም፡ ይታይሃል።
ምን፡ ይሆናል፡ ለሰማይ፡ መናኝ፡
ድኖ፡ ከምላክ፡ ጋራ፡ ሲገናኝ።
ምን፡ ያህል፡ ደስታ፡ አለ፡ በላይ፡
በሌቱ፡ በሰማይ።

፪፡ ዛሬም፡ በቃሉ፡ ቀርቦልሃል፡
ዛሬም፡ እረኛህ፡ ፈልጎሃል።
ሰምተሃል፡ ድምጹን፡ ወንድሜ፡ ሆይ፡
ልብህን፡ ከፈትህ፡ ወይ፤
ምን፡ ይሆናል። . . . ።

፫፡ ሳታመነታ፡ ለርሱ፡ ክፈት፡
ዛሬም፡ ተቀበል፡ ከርሱ፡ ስርየት።
ዛሬ፡ ሲሰጥህ፡ ያምላክ፡ ጸጋ፡
ልብህን፡ አትዝጋ።
ምን፡ ይሆናል። . . . ።

ረሱቲን።

ግጌ፡

S. T. 635.

፩፡ የሚመጣ፡ ሁሉ፡ የሱስ፡ ይላል፡
ሰምቶ፡ የሚመጣውንም፡ ይቀበላል።
አንድም፡ ወደ፡ ሚዳ፡ ከቶ፡ አንዳይጣል፡
ቃሉ፡ ይመሰክራል።
ወደ፡ እኔ፡ ኑ፡ ሲል፡ ይጠራናል፡
ድምጹ፡ ለሁላችንም፡ ይሰማናል።
ለጠፋው፡ ልጅ፡ አባቱ፡ ተመለስ፡ ይለዋል፡
እኛንም፡ ይጠብቃል።

፪፡ እውነተኛ፡ መንገድ፡ የሱስ፡ ሁንዋል፡
የሰማይም፡ ደጅ፡ በርሱ፡ ተከፍትዋል።
አንተም፡ ለመግባት፡ አውን፡ ይቻልሃል፡
ሳንተም፡ ተከፍቶልሃል።
ወደ፡ እኔ፡ ኑ፡ . . . ።

፫፡ የሚመጣ፡ ሁሉ፡ ጸጋ፡ ያገኛል።
የየሱስን፡ ትሩፋት፡ ይቀበላል።
ከሞት፡ ወደ፡ ሕይወትም፡ ይሻገራል፡
በመድኃኒታችን፡ ቃል።
ወደ፡ እኔ፡ ኑ፡ . . . ።

ረሱቲን።

ግጌ፡

S. T. 117.

፩፡ ያበተህ፡ እቅፍ፡ ተከፍትዋል፡
ልጄን፡ ሊቀበልህ፡
በስምህም፡ ይጠራሃል፡
በፍቅሩም፡ ፈለገህ።
እጁንም፡ ዘርግቶልሃል፡
በታላቅ፡ ምሕረት።
ለአንተም፡ ተዘጋጅትዋል፡
ስፍራ፡ በሰርጉ፡ ቤት።

፪፡ በዚህ፡ በዓለም፡ በረሐ፡
ሰላም፡ የማታገኝ፡
ከሕይወት፡ ምንጭ፡ ጥሩ፡ ውኃ፡
እንዴት፡ የማትመኝ፡
በሌላ፡ ምንጭ፡ የልብህ፡ ጥም፡
ሊጠፋ፡ አይችልም።
መድኃኒት፡ ያለ፡ የሱስ፡ ስም፡
አልተገኘልንም።

፫፡ ርስትህን፡ ሁሉ፡ በትነህ፡
መሞት፡ ያስፈራሃል።
በቤትህ፡ ግን፡ ቸር፡ አባትህ፡
ልጁን፡ ይጠብቃል።
የሰርግ፡ ልብስና፡ ቀለበት፡
አውን፡ ይቆይሃል።
በከንቱ፡ ሁሉን፡ ለመስጠት፡
አባትህ፡ ወድዋል።

፬፡ የጠፋ፡ ልጅ፡ ወዳባቱ፡
ቢሔድ፡ በንስሐ፡
በማይመረመር፡ ምሕረቱ፡
ይመርሳል፡ ፍጹሐ።
በቤቱም፡ ሁሉ፡ ግሩም፡ በዓል፡

እልልታም፡ መዝሙርም፡
በዚያ፡ ቀን፡ ይደረጋል፡
ደስታውም፡ አይተረክም።

ረስቲን።

፵፯፡

S. T. 769.

፩፡ ሕይወቴን፡ ለወጥሁልህ፡
ልገዛ፡ ነፍስህን።
ሰማይን፡ ልከፍትልህ፡
ልሰጥህ፡ ርስትህን።
ትድን፡ ዘንድ፡ ደሜ፡ ፈስዋል።
ምን፡ መልሰህልኛል፡

፪፡ ስላንተ፡ ብዕዕና፡
እኔ፡ ተሣቀይሁ።
ስላንተም፡ ብልጥግና፡
እኔ፡ ደኸየሁ።
ስላንተ፡ ሁሉንም፡ ትቼ፡
ምን፡ ሆኑ፡ ደመወዜ፡

፫፡ ከኃጢአት፡ ከሞትም፡
ላድንህ፡ መጣሁ።
በልብህ፡ ውስጥ፡ ልኖርም፡

ደጅህን፣ መታሁ።
ስጠኝ፣ አ፡ ልጄ፡ ምኞቴን፣
ልብህን፣ ደመወዜን።

ረስቲን።

፻፷፫፣

S. T. 643.

፩፣ ያ፣ ታላቅ፣ ሐኪም፣ መጥትዋል፣
መድኃኒታችን፡ የሱስ፡
ለዓለምም፡ ተሰጥትዋል፣
መዳን፡ በጌታ፡ የሱስ።
ስሙ፣ ይላቅ፡ ለተጉሐን፡
ይዘመርም፡ በሰው፡ ልማን፡
ይደነቅ፡ ለምዕመናን፣
ያ፡ ድንቅ፡ ስም፡ የሱስ፡ ክርስቶስ።

፪፣ የአምላክ፡ በግ፡ ሁኖልናል፣
መድኃኒታችን፡ የሱስ።
በመስቀልም፡ ሙቶልናል፣
ያ፡ ንጹሕ፡ ጌታ፡ የሱስ።
ስሙ፡ ይላቅ። . . . . . ።

፫፣ ዕዳችንን፡ ይሰርያል፣
መድኃኒታችን፡ የሱስ።

ወደ፡ ሰማይ፡ ይመራናል፣
ያ፡ ቸር፡ እረኛ፣ የሱስ።
ስሙ፡ ይላቅ፡ . . . . . ።

ረስቲን።

፻፷፬፣

S. T. 139.

፩፣ ወዳምላክ፡ ልብ፡ የሚያደርስ፣
አንድ፡ ቅዱስ፡ ደጅ፡ አውቃለሁ።
ከዚያም፡ ደጅ፡ ብርሃን፡ ሲሠርፅ፣
መድኃኒቴን፡ አያለሁ።
እንዴት፡ ይገርማል፡ አምላኬ፣
ያ፡ ደጅ፡ ተከፈተ፡ ለኔ።
ለኔ፣ ለኔ፣
ተከፈተ፡ ለኔ።

፪፣ ያ፡ ደጅ፡ ለማንም፡ አይዘጋም፣
ተከፈተ፡ ለሁሉ፡
ለንጉሥም፡ ለባርያም፣
ለምድር፡ ወገን፡ ሁሉ።
እንዴት፡ ይገርማል፡ . . . . . ።

፫፣ አንድ፡ ቀን፡ ግን፡ ደጁ፡ ይዘጋል።

ቆሎ፡ ለመግባት፡ ቸኩል።
የሱስ፡ አሁን፡ ይጠራሃል፡
ከጠቃውንም፡ ተቀበል።
እንዴት፡ ይገርማል፡ . . . . . ።

፬፡ አንድ፡ ቀንም፡ መስቀላችንን፡
በላይ፡ ሲያጠፋልን፡
ዘውድም፡ ሲሰጠን፡ የሱስን፡
እናመሰግናለን።
እንዴት፡ ይገርማል፡ . . . . .

ረሱቲን።

፱፡

I. C. 205.

፩፡ ተነሥቼ፡ ወዳባቴ፡ ልሔድ፡ ነኝ፡
በቀና፡ መንፈስ፡ ላድርግ፡ ኑዛዜን።
አምላኬ፡ ሆይ፡ ምሕረትህን፡ አሳየኝ፡
በጸጋ፡ ደምስስልኝ፡ ኃጢአቴን።

፪፡ እንዲህ፡ ብዬ፡ አባቴ፡ ሆይ፡ ተወልኝ፡
ባንተና፡ በሰማይም፡ በደልሁ።
ሰላም፡ ስጠኝ፡ ደስታህን፡ አውርድልኝ፡
ተቀበለኝ፡ ስል፡ እጮኻለሁ።

፫፡ ይሰማኛል፡ ኃጢአቴ፡ እንደ፡ በዛ፡
የአምላክ፡ ምሕረት፡ ገና፡ ይበልጣል።
ጥፋ፡ ልጁ፡ ልመለስ፡ ሲል፡ ቢነግ፡
ቸር፡ አባቱ፡ አቅፎ፡ ይቀበላል።

፬፡ ተነሥቼ፡ ወዳባቴ፡ ልመለስ፡
ልግጠን፡ ነኝ፡ በአባትነቱ።
ጉባኤ፡ ብዙዎን፡ ላምላክ፡ ሊወድስ፡
ሲገባ፡ ጥፋ፡ ልጅ፡ በማሕበሩ።

O. E.

፲፩፡

S. T. 242.

፩፡ እኔ፡ የሱስን፡ ለማየት፡
ከዱ፡ አይሆንልኝም።
ወይ፡ ድክም፡ የልቤ፡ እውረት፡
እርሱን፡ አያሳየኝም።
ና፡ ብርሃንህን፡ አብራልኝ፡
ሕይወትህንም፡ ስጠኝ።
ፅውር፡ ዓይኔን፡ ፈውስልኝ፡
ከጥፋትም፡ አድነኝ።

፪፡ በባርነት፡ ለተጋዙ፡
ግሩም፡ አርነት፡ ሁንዋል።

በሬት፡ መርገም፡ ለተያዙ፡
ቡራኬ፡ ተሰጥትዋል።
ክቡር፡ ደመ፡ ለነፍሳቸው፡
ሕይወት፡ ሆነ፡ ፈውስም።
የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሞተላቸው፡
እርሱ፡ ነው፡ መድኃኒትም።

፫፡ ማን፡ ነው፡ ዛሬ፡ የሚጠራ፡
ፍቅሩን፡ የሚገልጥ፡ ማን፡ ነው፡
ለሚሞትም፡ የሚራራ፡
የሚያድንስ፡ ማን፡ ነው፡
እርሱ፡ ነው፡ መድኃኒታችን፡
ስለ፡ አንተም፡ ሙትዋል።
ቅዱስ፡ ስሙን፡ የሚያምን፡
ለዘላለም፡ ይድናል።

ተወልደ፡ ብርሃን።

፺፪፡

S. T. 201.

፩፡ ሕግ፡ ፈረደብን፡
ምሕረት፡ እንለምን።
ጸጋህን፡ ለግስ፡
ፍርድን፡ ስንለብስ።

ትል፡ ነን፡ እኛ፡
የሚበን፡ ትቢያ፡
አላፊ፡ ጥላ።

፪፡ ጠግ፡ ከብዶን፡
ኃጢአት፡ ወረሰን፡
ምኞትም፡ ነዳን፡
ፈተና፡ አሳተን።
ደክሞች፡ ነን፡
አትቅሥፈን።
ተቀበለን።

፫፡ ስለ፡ ሥቃዩ፡
ስለ፡ እሾኽ፡ ዘውዱ፡
የሱስ፡ የጫነ፡
ሊያስታርቀን፡
አምላክ፡ ራራልን፡
አትፍረድብን፡
አባት፡ ሁንልን።

፬፡ በቅዱስ፡ ደሙ፡
የወጣ፡ ከጕኑ፡
እንድናለን፡
ይጠጋል፡ ቍስላችን።

የዋህ፡ እረኛ፡
የክዳውን፡ ጠራ፡
ና፡ ወደ፡ መንጋ።

፫፡ አምላክ፡ ርዳኝ፡
በየሱስ፡ ማረኝ።
ሲ.ማልደልን፡
ጸሎቱን፡ ስማልን።
እንጮኻለን፡
ደምስስ፡ ኃጢአታችን፡
አምላክ፡ እይልን።

O. E.

፶፫፡

S. T. 488.

፩፡ ከከበደ፡ ኃጢአቴ፡
ወዴት፡ ልሸሽ፡ አ፡ አምላኬ፡
ዘማም፡ እጨነቃለሁ።
ሕግህን፡ ሁሉ፡ አፍርሼ፡
ራቅም፡ ከአንተ፡ ሸሽቼ፡
ፍርድህን፡ አፈራለሁ።
ነፍሴንም፡ ሐዘን፡ ደቂሰው፡
ልቤንም፡ ጸጸት፡ ሰበረው።

አ፡ ጌታዬ፡ ራራልኝ፡
መድኃኒትም፡ ሁንልኝ።

፪፡ አ፡ የሱስ፡ ቃልህ፡ ሕይወት፡ ነው፡
ለነፍሴ፡ ጤናም፡ ጣፋጭ፡ ነው፡
ልቀበለውም፡ አሻለሁ።
ወዳለም፡ የሱስ፡ መጥቀ ል፡
ፅዳዬን፡ ከፈለ፡ ይላል፡
በእርሱም፡ እድናለሁ።
ቀማኛውን፡ የተቀበለው፡
በገነትም፡ ያሳረፈው፡
እኔንም፡ እንዲቀበል፡
ይለኛል፡ ቅዱስ፡ ወንጌል።

፫፡ አ፡ የሱስ፡ አ፡ የዳዊት፡ ልጅ፡
ወደ፡ አንተ፡ ዓይንና፡ እጅ፡
እኔ፡ እዘረጋለሁ።
የረከስሁ፡ እኔን፡ አጥራኝ፡
ከኃጢአትም፡ እድን፡ አንጻኝ።
በአንተ፡ አምናለሁ፡
የጠሩች በግም፡ ነበርሁኝ፡
በአንተ፡ ግን፡ ተገኘሁኝ።

አኑረኝ፡ ከንተ፡ ጋራ፡
አንተ፡ የምትራራ።

ክፍለ፡ አግዚአ።

ፃፀ፡
S. T. 489; - Stud. miss. 54.

፩፡ ኦ፡ አምላኬ፡
በኃጢአቴ፡
መንፈሴ፡ አዘነብኝ።
በዚች፡ ዓለም፡
አንድ፡ ሰው፡ የለም፡
በጭንቀት፡ የሚረዳኝ።

፪፡ ሩቅም፡ ብሔድ፡
ረጅም፡ መንገድ፡
እስከ፡ ዓለም፡ ዳርቻ፡
በየት፡ ላገኝ፡
ደስ፡ የሚለኝ፡
ከሐዘን፡ የሚፈታ፡

፫፡ ወደ፡ አንተ፡
ቸር፡ አምላኬ፡
እቀርባለሁ፡ አሁን።
አባት፡ ሁነኝ፡

ተዓገሠኝ።
ዘውትር፡ ሁንልኝ፡ ተገን።

፬፡ ቸሩ፡ የሱስ፡
ልሆን፡ ዕጉሥ፡
አድስ፡ ክፉ፡ ጠባዬን።
ደክማ፡ ነኝ፡
አራምደኝ፡
በደስታ፡ ወይ፡ በሐዘን።

፭፡ በንተ፡ ፈቃድ፡
በቅን፡ መንገድ፡
ልሔድ፡ እጄን፡ ያዝልኝ።
በዚች፡ ዓለም፡
ብርቱ፡ ሽክም፡
ልታገሥ፡ ኃይልን፡ ስጠኝ።

፮፡ አብና፡ ወልድ፡
በባሕርይ፡ አንድ፡
ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ጋራ፡
ስማኝ፡ አሁን፡
አዎን፡ አሜን፡
ጸሎቴን፡ ልትሰማ።

ሉንሂል።

፱፫፡

S. T. 483.

፩፡ ኦ፡ ርኅሩኅ፡ አምላክ፡ ጸጋህን፡ ስጠኝ፡
ከኃጢአትም፡ በርሱ፡ አድነኝ።
ኦ፡ የሱስ፡ መንፈስህንም፡ ላክልኝ፡
በፊትህም፡ ምሕረትህ፡ ይቁምልኝ።

፪፡ ያለም፡ ብርሃን፡ እንደ፡ ጥዋቱ፡ ከከብ፡
የምድር፡ ልጆችን፡ ወዳንተ፡ ለማቅረብ።
ከወጣህ፡ አንተን፡ እመለከታለሁ፡
በደስታም፡ ጨረሀን፡ እከተላለሁ።

፫፡ በኃጢአት፡ እንቅልፍ፡ ለማንቀላፋት፡
ሞትም፡ ልሞት፡ አልተውከኝም፡ ኦ፡ አባት።
በጸጋህ፡ ስለሰጠህ፡ ምሕረትን፡
ተቀበል፡ ልቤን፡ ገጸ፡ በረከቱን።

፬፡ መድኃኒት፡ ሆይ፡ ለእኔና፡ ለሁሉ፡
የመቅሠፍት፡ ጽዋን፡ ጠጣኸው፡ በምሉ።
እወድሃለሁ፡ ባንተም፡ አምናለሁ፡
በኃይልህም፡ ከውድቀት፡ እድናለሁ።

ረዕቲን።

፱፬፡

Mel. S. T. 300.

ኃጢአቴ ያሳገኘኛል፡
ነፍሴንም፡ ያከብዳል።
እንደ፡ በሽታ፡ ይቀፈኛል፡
ኃይሌን፡ ያደነዝዛል።
ሃመጸዬን፡ ደምስስልኝ፡
እንዳልኰንን፡ አድነኝ።
ፍጠርልኝ፡ ቅዱስ፡ አሳብ፡
ልቤን፡ ወደ፡ አንተ፡ ሳብ።

O. E.

፱፭፡

S. T. 511.

ወደ፡ ጸጋ፡ ዙፋን፡ አውን፡ እቀርባለሁ፡
አምላክ፡ አባት፡ ሆንኝ፡ በተስፋ፡ እኖራለሁ።
ኃጢአቴን፡ ተወልኝ፡
በፍቅሩ፡ ሞገሰኝ፡
ሰላሙን፡ ዐደለኝ።
አውንም፡ ደስ፡ አለኝ።

O. E.

ስለ፡ ምዕመን፡ ደስታ።

፱፫፡

S. T. 53.

፩፡ ያን፡ ክቡር፡ ዕንቁ፡ አገኘሁኝ፡
እርሱም፡ መድኃኒቴ።
አገኘው፡ ዘንድ፡ ተመኘሁኝ፡
አሁንም፡ ነው፡ ሀብቴ።

፪፡ ተነሽ፡ አ፡ ነፍሴ፡ ዘምሪ፡
ደስታሽንም፡ ግለጭ፡
ንጉሥሽንም፡ አክብሪ፡
ለርሱም፡ ምስጋና፡ ስጭ።

፫፡ ከአምላክ፡ ጋር፡ አስታረቀኝ፡
የእውነቱንም፡ ቃል፡
በመንፈሱ፡ አስታወቀኝ፡
በልቤም፡ ነግሥዋል።

፬፡ የጌቶች፡ ሁሉ፡ ጌታ፡ ነው፡
የኔም፡ አረኛ፡ ነው።
ቀንበሩንም፡ ስሸከመው፡
በእውነት፡ መልካም፡ ነው።

፭፡ ድኃ፡ ብሆንም፡ ምስኪንም፡
ብርታቴ፡ እርሱ፡ ነው።
በኃጢአት፡ ስጨነቅም፡
የኃጢአት፡ ማስተረይ፡ ነው።

፮፡ እርሱ፡ ነው፡ ጽድቄ፡ ሕይወቴም፡
ሰላሜም፡ ጤናዬም።
እርሱ፡ ነው፡ ደህንነቴም፡
ድፍረቴም፡ ተስፋዬም።

፯፡ ዕዳዬን፡ የደመሰሽው፡
አ፡ ርኅሩኅ፡ መድኃኔ፡
አንተ፡ ሁሉ፡ በሁሉው፡
ዘወትር፡ ሁን፡ ለኔ።

ረሱቲን።

፯፬፡

S. T. 86.

፩፡ አ፡ ነፍሴ፡ አሁን፡ ደስ፡ ይበልሽ።
አ፡ ልቤ፡ ሐሴት፡ አድርጊ።
በደሙ፡ የሰስ፡ እንደገዛሽ፡
የሚለውን፡ ወንጌል፡ አትርሺ።
አምላክሽ፡ እንደወደደሽ፡
ሰው፡ ሁኖ፡ አንችን፡ እንደዋጀሽ፡

በከንቱም፡ ጸጋውን፡ አንደሰጠሽ፡
ይህንን፡ ከቶ፡ አትርሺ።

፪፡ በልቤ፡ ጭንቅ፡ ብኾ፡ ቢሰማኝ፡
አንዳለሁ፡ የሱስ፡ ገዝቶኛል።
ማናቸውም፡ ነገር፡ ቢያስፈራኝ፡
የደሙ፡ ቤዛ፡ በቅትዋል።
ድኃ፡ ብሆን፡ ብኩብርም፡
ብቸገርም፡ ደስታ፡ ባገኝም፡
በሕይወት፡ ዘመኔም፡ በሞትም፡
የየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ገንዘብ፡ ነኝ።

፫፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ የሚያምን፡
ከሌላ፡ ሁሉ፡ ታደለ።
በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ደም፡ ሰላምን፡
ከአምላኩ፡ ተቀበለ።
በአባት፡ ፍቅር፡ ያየዋል፡
በመንገዱም፡ ወትሮ፡ ይመራል፤
ልጁንም፡ ወደ፡ ላይ፡ ይጠራል፤
ለዚህም፡ የሱስ፡ ገዝቶታል።

ረበጥን።

፻፡

S. T. 272.

፩፡ አርነት፡ ወጣሁኝ፡
ብየሱስ።
ከጭንቁም፡ አረፍሁኝ፡
በመድኃኒቴ።
የየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ደም፡
ጥቅሙን፡ ክብሩንም፡
ቀድሞ፡ አላወቅሁም።
አሁን፡ ታይቶኛል።

፪፡ የጸጋው፡ ምሥጢሩ፡
ተገለጠ።
አምላክ፡ በፍቅሩ፡
ልጁን፡ ለመጠ።
ፍርድ፡ ሲያስጨንቀኝ፡
ልቤም፡ ሲያውከኝ፡
በርሱ፡ ሰላም፡ አለኝ፡
በመድኃኒቴ።

፫፡ ምን፡ ያህል፡ ደስታ፡
አለኝ፡ አሁን።
ከምላኬ፡ ይቅርታ፡

ምን፡ ይበልጥ፡ ይሆን፡
ብዙ፡ ቢጐድለኝም፡
አያስፈርድብኝም።
ፍርድ፡ አይደርስብኝም፡
በመድኃኒቴ።

፬፡ እስከምሞት፡ ልመን፡
በየሱስ፡ ደም።
ይምጣ፡ የፍርድም፡ ቀን፡
አያስፈራኝም።
በየሱስ፡ ቸሮታ፡
የሰማይ፡ ደስታ፡
አለኝ፡ አለኝታ፡
በመድኃኒቴ።

ረስቲን።

ጀፅ፡

S. T. 258; 555.

፩፡ ስንት፡ ብዕዕና፡ ታደለ፡
የሱስን፡ ያገኘ።
ከርሱ፡ የተዘመደው፡
ልቡ፡ ሰላም፡ አለው።
ልናዳምጥ፡ የርሱን፡ ቃል፡

ከሁሉ፡ ይገዳል።
ከምሕረቱ፡ አንጥገብ፡
በእግሩ፡ አጠገብ።

፪፡ ምን፡ አለው፡ ጌጥ፡ ወርቅ፡ ደስታ፡
የሚበን፡ አዋራ።
ያመኑ፡ በየሱስ፡ ግን፡
ያዙ፡ እፀ፡ ሀብትን።
ጤና፡ ትርፍ፡ ወዳጅ፡ ሕይወት፡
ምንም፡ ቢጠፉበት፡
የሱስ፡ ከርሱ፡ ይኖራል፡
ገዳቱን፡ ይተክል።

፫፡ የሱስ፡ ሆንህልኝ፡ ጋሻ፡
ሰይፍ፡ መዝገብ፡ ትርፍ፡ አምባ።
በሌት፡ ሆንህ፡ ፀሓዬ፡
የማይከድ፡ ወዳጄ።
በወርድ፡ብኝ፡ ነህ፡ ተገን፡
ማጽንያ፡ በሐዘን፡
ኃይል፡ በጭንቀት፡ በድክም፡
በሞት፡ ሕይወት፡ ሰላም።

፬፡ ከኃጢአቴ፡ አዋራኝ፡

ጸድቅን፡ ፍጠርልኝ፡
አግባልኝ፡ ቅዱስ፡ ድፍረት፡
አድነኝ፡ ከውድቀት።
ሁን፡ አረኛዬ፡ ዘንጌ፡
አትራቅ፡ ከእኔ።
ከመቃብሬ፡ አንሣኝ፡
በሰማያት፡ አግባኝ።

O. E.

፶፪፡

S. T. 61.

፩፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ራሱ፡ ሆነ፡
የኔ፡ ወዳጅ።
ነፍሴንም፡ ከሞት፡ አዳነ፡
ያ፡ ቸር፡ ወዳጅ።
ልቡናው፡ በፍቅር፡ ጋለ፡
እኛን፡ ወንድሞቹ፡ አለ፡
ለኛም፡ ሲል፡ ሕይወቱን፡ ጣለ፡
ያ፡ ቸር፡ ወዳጅ።

፪፡ ሳልገናኝህ፡ ወደኸኛል፡
አ፡ ቸር፡ ወዳጅ።
በምሕረት፡ ተዛምደኸኛል፡

እንደ፡ ወዳጅ።
ከጥፋቴ፡ ስወኸኛል፡
ከመሞት፡ አድነኸኛል፡
ለልጅነት፡ መርጠኸኛል፡
አ፡ ቸር፡ ወዳጅ።

፫፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ረድኤት፡ እሻለሁ፡
ከዚሁ፡ ወዳጅ።
ሁሉንም፡ እነግራለሁ፡
ለዚሁ፡ ወዳጅ።
አንዳች፡ ነገር፡ ቢሆንብኝ፡
ልመናዬን፡ ሲሰማልኝ፡
ገርሞኛል፡ ሲያስብልኝ፡
ይህ፡ ግሩም፡ ወዳጅ።

፬፡ ይህ፡ ወዳጅ፡ በሐዘን፡ ሁሉ፡
ያጸናኛል።
እርሱም፡ ኃጢአቴን፡ ሁሉ፡
ይሰርያል።
እኔም፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ስበድል፡
መከራዬን፡ ሲያስተውል፡
በስሕተቴ፡ ሳይበቀል፡
ይምረኛል።

፫፡ እንዳይታየኝም፡ ቢደበቅ፡
አይተወኝም።
እኔን፡ ራሴን፡ ለመጠበቅ፡
አይለቀኝም።
መንገዱ፡ በይታወቀኝም፡
ሊረዳኝ፡ ሊያድነኝም፡
ነውና፡ ቢፈትነኝም፡
አላዝንም።

፮፡ ሐሳብ፡ ሁሉ፡ እጥላለሁ፡
በዚህ፡ ወዳጅ።
ሁሉን፡ እጠባበቃለሁ፡
ከዚህ፡ ወዳጅ።
አሮጌ፡ ሥጋዬን፡ መግደል፡
ነፍሴን፡ ከጥፋት፡ ማስጠለል፡
መከራዬንም፡ ለማቅለል፡
ይቻለዋል።

፯፡ አምላክ፡ የተዘመዳቸው፡
እንደ፡ ወዳጅ፡
ለዘላለም፡ ብሩክን፡ ናቸው፡
አ፡ ግሩም፡ ወዳጅ።
ሌላ፡ ዘመድ፡ ሲተዋቸው፡

ሌላ፡ ሀብት፡ ሲጠፋባቸው፡
የዘላለም፡ ሀብት፡ አላቸው፡
በዚህ፡ ወዳጅ።

ረቡዕን።

ጽዮን፡

S. T. 496.

፩፡ የማይተወኝ፡ ጥር፡ ወዳጄ፡
ጌታ፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ነው።
እኔም፡ እንዴት፡ እርሱን፡ ክጄ፡
ወዳጅነቱን፡ ልተው፡
እሰከዚህ፡ ድረስ፡ ሲወደኝ፡
እንዳችም፡ አይለየኝም።
ከርሱ፡ ጋር፡ እንድነት፡ አለኝ፡
ዛሬና፡ ዘላለምም።

፪፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ከሞተልኝ፡
ማንም፡ አይፈርድብኝም።
ክባቱም፡ ሲለምንልኝ፡
ጸጋው፡ አይቀርብኝም።
ጠበቃዬም፡ ሲሆንልኝ፡
ማን፡ ሊከሰኝ፡ ይችላል፡

በከሃሊ፣ እጁም፣ ሲይዘኝ፣
ከርሱ፣ ማን፣ ይነጥቀኛል፡

፫፡ ሕይወትና፡ ሞት፣ ከየሱስ፣
እንዳይለየኝ፣ አመንሁ።
ልቤም፣ በፍርሃት፡ ሲደቂስ፣
የሱስን፣ ተማጠንሁ።
ውርደትም፣ ቢሆን፡ ወይም፡ ክብር፣
ደስታም፣ ሆነ፡ ሐዘንም፡
በርሱ፡ ካለኝ፣ ከምላክ፡ ፍቅር፡
ከቶ፣ አያወጣኝም።

ረስቲን።

፻፲፡

S. T. 714; 163.

፩፡ ከየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ጽድቅ፣ በቀር፣
የምድንበት፡ የለኝም።
ግን፣ በርሱ፣ አምኜ፡ ልድፈር፡
የአምላክ፣ ሕግ፣ ሲከሰኝም።
ለማመን፣ ቢያስቸግርም፣
የየሱስ፣ ቃል፡ አይፋለስም።

፪፡ ሕይወት፣ ሊሰጠኝ፣ የሚችል፡
የኃጢአት፡ ይቅርታ፡ ነው።

ከፍርድም፡ የሚያስጠልል፡
ምሉ፡ ይቅርታ፡ ብቻ፡ ነው።
ይቅርታ፣ ባይኖርልኝም፣
ተስፋና፡ ሕይወት፡ የለኝም።

፫፡ የምመካበት፣ ጋሻዬ፡
የኃጢአት፡ ይቅርታ፡ ነው።
በጭንቅም፣ ሁሉ፡ ደስታዬ፡
የኃጢአት፡ ይቅርታ፡ ነው።
በየሱስ፡ ደም፡ ስርየት፡ ሳገኝ፡
እስክ፡ ዘላለም፣ ብፁዕ፡ ነኝ።

፬፡ ኡ፡ የሱስ፡ ግሩም፡ ይቅርታህን፣
በጸጋህ፡ ሁሉ፣ ቀን፣ ስጠኝ።
በልቤም፣ ውስጥ፡ ሰላምህን፡
ይቅርታህ፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ይስጠኝ።
በደምህ፡ አምባ፡ ውስጥ፡ ስኖር፡
አልፈራም፡ የጠላቴን፣ ጦር።

ረስቲን።

ስለ፡ ክርስቲያን፡ አካሔድ።

፻፫፡

S. T. 101.

፩፡ በአምላክ፡ ተመርተን፡ በቃሉ፡ ብርሃን፡
በልጁም፡ ሲጸና፡ የምሕረት፡ ኪዳን፡
ያላየነው፡ ዘመን፡ ሲብት፡ አንፍራ።
ያ፡ ቸር፡ አረኛችን፡
ሲኖር፡ በቅርብችን፡
ሲሔድ፡ በፊታችን፡
ከምን፡ አንፍራ፡

፪፡ ከጨለማ፡ ዓለም፡ ከምድር፡ ሥቃይ፡
አንድ፡ ጭፍራ፡ ተነሣ፡ ሊጓዝ፡ ወደ፡ ላይ።
የጭፍራውም፡ ገናነት፡ ተሠውርዋል፡
ግን፡ አምላክ፡ ሲቀድም፡
ሲከተል፡ ሲከብም፡
ሲያግፍ፡ ሲሸከም፡
ይጋርደዋል።

፫፡ ከንቱነቱን፡ ዓለም፡ ሲፈልግ፡ ሲሻው፡
በርኩሰትም፡ ብቻ፡ ሲሆን፡ ይስታው፡
ያን፡ ጭፍራ፡ ልከተል፡ ሲሔድ፡ ወደ፡ ላይ።

ያልታወቀውን፡ ክብር፡
ያልታሰበውን፡ ነገር፡
የተስፋውንም፡ ምድር፡
ላገኝ፡ በሰማይ።

፬፡ የደመና፡ ዓምድ፡ የእሳት፡ ግለትም፡
ውኃ፡ የሚሰጠን፡ ሕያው፡ እለትም፡
ዘወትር፡ ሊመራ፡ ይከተሉናል።
ያን፡ ቅዱስም፡ እለት፡
ብታየው፡ በእምነት፡
ለሞቱ፡ ሕይወት፡
ሊሰጥ፡ ይችላል።

፭፡ ያ፡ እለትም፡ ክርስቶስ፡ መድኃኒቴ፡ ነው።
ያነጻንም፡ ደም፡ የወጣበት፡ ውኃው።
የኃጢአታችን፡ ስርየት፡ እለን፡
በአንዱ፡ በየሱስ።
ያ፡ ጻድቅ፡ ያ፡ ቅዱስ፡
ለምስኪን፡ ለርኩስ፡
መድኃኒት፡ ሆነ።

፮፡ በሰይጣን፡ ስጨነቅ፡ ሲበዛኝ፡ ድክም፡
መድኃኒቴ፡ ሆነ፡ የልቤ፡ ሰላም።
በመስቀሉ፡ ሞተ፡ ለሁሉ፡ ኃጥአን።

ለሁሉም፡ ከሞተ፡
ሁላችንም፡ ሞትን፡
ለሁሉም፡ ከሞተ፡
ተገኘ፡ መዳን።

፭፡ በአምላኬ፡ ፊት፡ በደለኛ፡ ስሆን፡
በየሱስ፡ ብገኝ፡ ማን፡ ይከሰኝ፡ ይሆን፡
በየሱስ፡ በልጁ፡ የጸደቅሁ፡ ነኝ።
በእርሱም፡ ሲያየኝ፡
አንድ፡ ርኩሰትም፡ የለኝ፡
ሥምረቱ፡ ግን፡ አለኝ፡
በየሱስ፡ ስገኝ።

፮፡ ይህም፡ የብዕዕና፡ መያዣዬ፡ ነው።
የየሱስም፡ ጽድቅ፡ መጸናናቴ፡ ነው፡
ያነገብሁት፡ ጋሻም፡ የደፋሁት፡ ቊር።
መድኃኒቴ፡ ሳለ፡
ረድኤት፡ ዘወትር፡ አለ።
መድኃኒቴ፡ ሳለ፡
በተስፋ፡ ልኑር።

፯፡ አ፡ የሱስ፡ ያልተውኸኝ፡ እስከ፡ አሁን፡
መታመንህ፡ ብኾ፡ ተስፋችን፡ ይሁን።
ተሸከመን፡ ጋርደን፡ ከኛም፡ ዘንድ፡ ሁን።

አሜን፡ ለዘላለም፡
ምስጋና፡ ስብሐትም፡
ለአምላክ፡ ለዘጉም፡
ሳይጨረስ፡ ይሁን።

ረስቲን።

፷፭፡

S. T. 273.

፩፡ ያምላክ፡ ሕዝብ፡ የጽዮን፡ ወገን፡
ወደ፡ ላይ፡ ይራመዳል።
በለም፡ ባይገኝለት፡ ተገን፡
ከምላክ፡ ዘንድ፡ ተገኝትዋል።
የሱስ፡ ክርስቶስ፡ የገዛቸው፡
በርሱም፡ የሚያምኑ፡
እንግዶች፡ በምድር፡ ናቸው፡
በለምም፡ ተበተኑ።

፪፡ በለም፡ ሁሉ፡ ብትጠላ፡
ጥሉ፡ አያስፈራህም።
የሱስ፡ ልብህን፡ ከመላ፡
ሌላ፡ አያስፈልግም።
እርሱ፡ ብኾ፡ ምሉ፡ ተስፋ፡
ሊሆንልህ፡ ይችላል።

ሌላ፡ ምርኩዝም፡ ቢጠፋ፡
ደገፋው፡ ይጦርሃል።

፫፡ እርሱን፡ አገኝተህ፡ በምሉ፡
ሕይወትህ፡ ይበቃሃል።
አምላክ፡ ሁሉ፡ ነው፡ በሁሉ፡
መንጋውንም፡ ያስጠልላል።
ድንቢዋ፡ ቤትዋን፡ አገኘች፡
በአምላክ፡ መሠወሪያ።
ግሩም፡ አርነትም፡ ተገኘች፡
ለተጨነቀው፡ ባርያ።

፬፡ እምነትና፡ ፍቅር፡ ብቻ፡
አምላክ፡ ከኛ፡ ፈለገ።
ፍቅር፡ ነው፡ የሕግ፡ ዳርቻ፡
ትእዛዙን፡ አደረገ።
የሚያምንም፡ ይድናል።
የሱስ፡ መንፈስህ፡ ይምራን።
ፍቅርህን፡ ያስፈልገናል፡
የሱስ፡ ሆይ፡ ፍቅርህ፡ ይግዛን።

፭፡ መንፈስህ፡ በዚህ፡ መሠረት፡
ቅዱስ፡ ቤትህን፡ ይሥራ።
እያንዳችንንም፡ በምንት፡

ወደ፡ መስቀልህ፡ ይምራ።
ማሕበርህን፡ ያዳብር፡
ይግለጥለት፡ እውነቱን።
ሁሉንም፡ ሲያስተባብር፡
በሁሉ፡ አንድ፡ ልብ፡ ይሁን።

ረስጥን።

፻፷፫፡

Abnf. 63.

፩፡ ያች፡ ታናሽ፡ መንጋ፡ ብዕዕት፡ ናት፡
የክርስቶስ፡ ቤተ፡ ሰው።
ጠላትም፡ ቢያስጨንቃት፡
እረኛዋም፡ ታላቅ፡ ነው።
ከመከራ፡ ያድናታል፡
በቃሉም፡ ያበረታታል፡
ዎዳገሩም፡ ይመራታል፡
በእጁም፡ ይይዛታል።

፪፡ በጉቹንም፡ የውቃቸዋል፡
እነርሱም፡ አወቁት።
ልባቸውም፡ አዲስ፡ ሁንዋል፡
ቃሉንም፡ አመኑት።
በመንፈስ፡ ኃይልና፡ ብርሃን፡

እላለሁ፡ ፫ር፡ ወዳጄ፡ ሆይ፡
አንተማ፡ አወቅኽኝ።
ድካም፡ ቢያገላላኝም፡
በኃጢአት፡ ብጨነቅም፡
ልከተልህ፡ ልወድህም፡
ፈቃዴስ፡ ሁንሞል።

፯፡ ስ፫ር፡ ስፈራ፡ ምላሼን፡
ልሰዋ፡ ቢቸግረኝ፡
አንተስ፡ ትላለህ፡ ገንዘቤን፡
መው-ደድም፡ አይቸግረኝ።
በሞት፡ በሕይወት፡ ወደድኽኝ፡
ላንተም፡ በደምህ፡ ዋጀኽኝ።
አ፡ ፫ር፡ ወዳጄ፡ ላንተ፡ ኑኝ፡
በፈት፡ ለወደድኽኝ።

ፈጸጥኝ።

፵፰፡

Hamb. ps. 270.

፩፡ ስለ፡ ሕይወት፡ ዋና፡ ጥቅም፡
አምላኬ፡ አስተምረኝ።
ባለም፡ ያለ፡ ቢያስገርም፡
ክቡድ፡ ቀምበር፡ ሆኑብኝ።

ከፍርድ፡ ከሰይጣንም፡ ሥልጣን፡
ተቀበሉ፡ ምሉ፡ መዳን፡
የአምላክ፡ ቅዱሳን።

፫፡ እኔስ፡ አ፡ የሱስ፡ ያንት፡ አሆን፡
እኔንም፡ ታውቅ፡ ይሆን፡
ተከትዬሀ፡ እሔድ፡ ይሆን፡
ታስገባኝስ፡ ይሆን፡
አ፡ ጌታ፡ የሱስ፡ ጥያቄን፡
ስጠይቅ፡ መልስ፡ መልስህን።
በበጎች፡ መንጋ፡ ውስጥ፡ እኔን፡
ትቆጥራለህን፡

፬፡ አቤቱ፡ ልቤን፡ መርምረው፡
ላንተስ፡ ይቻልሃል።
በፍጹም፡ ያንተ፡ አድርገው፡
ስለርሱ፡ ሙተሃል።
ቸሮታህም፡ ሳይታወቀኝ፡
በሕይወትህ፡ የገዛኽኝ፡
እሞት፡ ድረስ፡ ከወደድኽኝ፡
ልወድህ፡ አስተምረኝ።

፭፡ ኋላም፡ ትወደኛለህ፡ ወይ፡
ብለህ፡ ብትጠይቀኝ፡

በፈተና፡ ወጽመደ፡ ያጠላልፈኛል፡
ሥቃይና፡ ሀብትን፡ ዘትር፡ ያመጣል።
ሁሉን፡ የሚተካ፡ ያ፡ አንዱን፡ በ፯ኝ፡
በሚደርስብኝ፡ ዕገሥ፡ ብፁዕ፡ ነኝ።

፪፡ ልታገኘው፡ ብትታገል፡
አተሻ፡ በከንቱነት።
ከለም፡ ምኞት፡ ተጠቃለል፡
ከፍ፡ በል፡ ዝቅ፡ ከለ፡ ፍጥረት።
በምላክ፡ ስትጠጋ፡ ስትታመን፡ ፍቅሩን፡
በየሱስ፡ ይሰጥሃል፡ ነዋሪ፡ ሀብቱን።
ያን፡ ዕድል፡ ያገኘ፡ በጉድለቱ፡ እንኳ፡
ዘወትር፡ ይኖራል፡ በትርፍ፡ በደስታ።

፫፡ ይህን፡ ዕድል፡ ለማግኘት፡
ማርያም፡ እየናፈቀች፡
ለመስማት፡ የጌታን፡ ትምህርት፡
ዝቅ፡ ብላ፡ ተቀመጠች።
በተነገረላት፡ ሰማያዊ፡ አውነት፡
ብርሃኑ፡ ወጣላት፡ ፍቅሩ፡ አሞታት።
ያ፡ መልክሙ፡ ዕድል፡ ሳይወሰድባት፡
ለዘላለም፡ ሕይወት፡ ተጠበቀላት።

፬፡ ቸሩ፡ የሱስ፡ ሕዙን፡ ልቤ፡

ወዳንተ፡ ይናፍቃል።
በፍቅር፡ ተባበር፡ ከኔ፡
አድርገኝ፡ ያንተ፡ አካል።
ሌሎች፡ ካንተ፡ ርቀው፡ ቢጠፉብህ፡ እንኳ፡
ዘወትር፡ ልኖርልህ፡ ፍቅሬን፡ አጽና።
በቃልህ፡ ይገኛል፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡
በጸጸት፡ በጭንቀት፡ ዘወትር፡ ረድኤት።

፭፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ሀብት፡ ከሰጠህ፡
አውን፡ ምን፡ ያጣብኛል፡
ደምህን፡ ለመሥዋዕት፡ ይዘህ፡
ወደ፡ መቅደስ፡ ገብተሃል።
ከሞት፡ ኃይል፡ አዳንህ፡ ዋጀህ፡ ከባርነት፡
የልጅነት፡ መንፈስ፡ ላክህ፡ በቸርነት።
አርነት፡ ካገኘሁ፡ በአንተ፡ የውሃት፡
ከሁን፡ ልገዛልህ፡ በቅዱስ፡ ቅናት።

፮፡ አውን፡ ሰላም፡ ደስታ፡ አለኝ፡
ተስፋዬ፡ በየሱስ፡ ነው።
ባለም፡ አቃንቶ፡ ሊመራኝ፡
መንፈሴን፡ ሊቀድሰው።
ልኖር፡ በቸርነት፡ በጽድቅ፡ በበጎነት፡
አርቅ፡ ግብዝና፡ አግባልኝ፡ ቅንነት።

በሕይወት፡ በሞትም፡ ሁንልኝ፡ ተገን።
ስብሓት፡ ለአምላክ፡ ለዘላለም። አሜን።

O. E.

፷፱፡

S. T. 442. 439.

፩፡ በዚህ፡ በእንግድነቱ፡
ልቤ፡ ለምን፡ ይፈራል፤
ያ፡ ዕሙኑ፡ መድኃኒቱ፡
መራመዴን፡ ይመራል።
የሞተው፡ ስለ፡ በጎቹ፡
በቃሉና፡ በመንፈሱ፡
ከእኛ፡ ጋር፡ ይኖራል።

፪፡ እከተላለሁ፡ ኩቴውን፡
ድምጹም፡ ይታወቀኛል።
በጎ፡ እረኛም፡ በጎቹን፡
ቁጥሮ፡ ሁሉን፡ ያውቃል።
የጠፉትን፡ ይፈልጋል፤
የደከመውን፡ ይሸከማል፤
የወደቀውን፡ ያስነሣል።

፫፡ የሕይወት፡ ሕብስት፡ አብልዶ፡

ከጸጋ፡ ምንጭ፡ ያጠጣል።
በመንፈስ፡ ኃይል፡ አበርትቶ፡
ሰላሙንም፡ ይሰጣል።
በጨለማ፡ እንኳ፡ ብሔድ፡
እርሱን፡ ተከትዬ፡ ስሔድ፡
አንድ፡ ቅዱስ፡ ድፍረት፡ አለኝ።

፬፡ በጌን፡ በኃይል፡ ከመንጋዬ፡
የሚነጥቀብኝ፡ የለም፤
ስትል፡ ኡ፡ ቸር፡ እረኛዬ፤
ና፡ ጠብቀኝ፡ ከዓለም።
ይህ፡ ዓለም፡ በክንቱነቱ፡
በእይህ፡ ከሚመረቱ፡
አይሳበኝ፡ ለዘላለም።

፭፡ ይህ፡ ሕይወት፡ እንደ፡ ሕልም፡ ያልፋል።
በረን፡ እንሔዳለን፡
ቀናችን፡ ይመሽብናል፡
ከዚህ፡ እንጓዘለን።
ሲያልቅም፡ እንግድነቱ፡
እንዳልኸን፡ ባለህበቱ፡
እኛም፡ እንሆናለን።

ረስቲን።

ሮ፡

S. T. 62.

፩፡ አንድ፡ ወዳጅ፡ በምሔድበት፡ ሁሉ፡
ከኔ፡ ጋራ፡ ይመላለሳል።
አይታይልኝም፡ ግን፡ ቅዱስ፡ ቃሉ፡
ወደ፡ ልቤ፡ ይደርስልኛል።
ያ፡ ወዳጅ፡ ስለኔ፡ ሙቶ፡ ነበር፡
ከመቃብር፡ ግን፡ ተነሥትዋል።
እረኛችን፡ ሁኖ፡ በማይነገር፡
ርኅራኄ፡ ለመንጋው፡ ያስባል።

፪፡ ሁል፡ ጊዜ፡ የሚያስፈልገኝን፡
ቸር፡ እረኛ፡ ያቀርብልኛል።
ልቤንም፡ የሚያቆስለኝን፡
ፈውሶ፡ ረድኤት፡ ይሰጠኛል።
አጭር፡ ዘመን፡ እንዲሠወርብኝ፡
እርሱ፡ ራሱ፡ ገልጦ፡ ብሎኛል፡
ግን፡ ተመልሶ፡ ሲገለጥልኝ፡
ደስታና፡ ሰላም፡ ይሆነኛል።

፫፡ ድል፡ የነሣ፡ ዕሙኑ፡ መድኃኒት፡
ቶማስ፡ ሲጠረጥር፡ አሰበው።
እንዲሰጠውም፡ ቅዱስ፡ መጸናናት፡

ቍስሎቹን፡ አመለከተው።
ቶማስ፡ ጌታን፡ አውቆ፡ አዲስ፡ ተስፋ፡
ምሉ፡ እምነትም፡ ተቀብሎ፡
ጮኸ፡ በማይነገር፡ ቅዱስ፡ ደስታ፡
ጌታዬና፡ አምላኬ፡ ብሎ።

፬፡ ለኔ፡ ደግሞ፡ የሱስ፡ ሆይ፡ ራራልኝ፡
ያንን፡ ደስታ፡ አትከልክለኝ።
አለማመኔም፡ እንዲጠፋልኝ፡
ቍስሎችህን፡ አሳስበኝ።
ቸር፡ እረኛ፡ እኔ፡ ምስኪን፡ በግህ፡
ተስፋዬ፡ በአንተ፡ ብቻ፡ ነው።
አንተንም፡ አ፡ አምላኬ፡ የማውቅህ፡
ቍስልህን፡ ስታሳየኝ፡ ነው።

፭፡ የተወጋው፡ ልብህ፡ አ፡ ቸር፡ መድኅን፡
ያስበኝ፡ በዓለም፡ በረሐ።
በምንትም፡ ልመልከት፡ ቍስልህን፡
በትካዜና፡ በፍስሐ።
ና፡ አሳርፈኝ፡ በርኅሩኅ፡ እቅፍህ፡
አድርሰኝ፡ ወደየሩሣሌም።
ድኜም፡ ፈት፡ ለፈት፡ አ፡ ጌታ፡ ልይህ፡
አ፡ መድኃኒቴ፡ አ፡ አምላኬም።

ሮይ፡

S. T. 312.

፩፡ የሱስ፡ ሆይ፡ በዚህ፡ በምድር፡
የማርፍበት፡ ዬት፡ ላግኝ፡
ወደ፡ ሰማያዊ፡ አገር፡
አምጥተህ፡ አሳርፈኝ።
እመኛለሁ፡ እመኛለሁ፡
ካንተ፡ ጋራ፡ ልገናኝ።

፪፡ የምራመድበት፡ መንገድ፡
እጅግ፡ ቀጭን፡ ሁንዋል።
ሰይጣንም፡ በብዙ፡ ወጥመድ፡
ሊያጸምደኝ፡ ይጥራል።
ጐዳናዬም፡ ጐዳናዬም፡
በሞት፡ ወንዝ፡ ይወስደኛል።

፫፡ በዚህ፡ በምፈራው፡ ሁሉ፡
አንተ፡ አደፋፍረኝ።
የተሰጠውን፡ ላለም፡ ሁሉ፡
ደምህን፡ አሳስበኝ።
ያንተ፡ መስቀል፡ ያንተ፡ መስቀል፡
ለኔ፡ ሕይወትን፡ ይስጠኝ።

፬፡ እንዲት፡ ቀን፡ ስንኳ፡ ሥጋዬን፡

ድል፡ ለመንሣት፡ አቃተኝ።
ቅዱስ፡ መንፈስህ፡ ሥራዬን፡
መርቶ፡ ምክሩን፡ ይስጠኝ።
ና፡ አ፡ የሱስ፡ ና፡ አ፡ የሱስ፡
በድካሜ፡ ኃይል፡ ሁነኝ።

፭፡ ያለም፡ ፍቅር፡ ያለም፡ ጥልም፡
ከቶ፡ እንዳይደልለኝ።
ቢገዛልኝ፡ ምሉ፡ ዓለም፡
ያለ፡ አንተ፡ ግን፡ አይብቃኝ።
አንተ፡ ብቻ፡ አንተ፡ ብቻ፡
በውነት፡ መንገድህ፡ ምራኝ።

፮፡ ወደ፡ ርኅሩኅ፡ ልብህ፡ ሳበኝ፡
በርሱ፡ ውስጥም፡ ሠውረኝ።
ሌላም፡ ሁሉ፡ ቢጠፋብኝ፡
ካንተ፡ ጋራ፡ ብፁዕ፡ ነኝ።
ካንተ፡ ጋራ፡ ካንተ፡ ጋራ፡
የሰማይ፡ ሰላም፡ አለኝ።

ረስቲን።

፫፪፡

S. T. 719.

፩፡ ያንተን፡ ሰላም፤ አ፡ የሱስ፡ አውርድልን፤
በሁከት፡ የሚያድል፡ ጸጥታን፡
በእንግድነት፡ ተስፋን፡ የሚሰጠን፤
ለገነት፡ የሚለውጥ፡ በረሐን።

፪፡ ባጭር፡ ጊዜ፡ ከአንተ፡ ዘንድ፡ መታገል፤
አይዘህ፡ ልጄ፤ ብለህ፡ ስትመክረኝ።
ባጭር፡ ጊዜ፡ መዝራትና፡ ማገልገል፡
ቀኑ፡ ለመከር፡ እስኪንጋልኝ።

፫፡ ባጭር፡ ጊዜ፡ ይገኛል፡ ሥቃይ፡ ሐዘን።
ነፍሳቸን፡ በዚህ፡ ዘትር፡ ይጸማል።
ወዲያ፡ ግን፡ ደስታና፡ ትርፍ፡ ሊቆየን፤
ከሕይወት፡ ወንዝ፡ ነፍሳችን፡ ይረክል፡

፬፡ ባጭር፡ ጊዜ፡ አንተ፡ እስክትመጣ፤
መብራቱን፡ አብርቼ፡ ልጠብቅህ።
ስትመጣ፡ ሊሆነኝ፡ ደስታ፡ እልልታ።
ሁለ፡ ጊዜ፡ ስብሓት፡ ይሁንልህ።

O. E.

፫፫፡

S. T. 117.

፩፡ ያ፡ አዲስ፡ እየሩሣሌም፡ በላይ፡ ተሠርትዋል፤
በዚያም፡ ምሉ፡ ደስታና፡ ሰላም፡ ይቆየኛል።
በዚህ፡ በምድር፡ ግን፡ ፍርሀት፡ ሁከትም፡ በዝ
|ትዋል፡
ሲሻልም፡ እንኳ፡ መከራ፡ ድካምም፡ መልት
|ዋል።

፪፡ እንዲሁ፡ ከሆነስ፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ወደየሩሣሌም፡
ብናፍቅ፡ አያስደንቅም፤ ብመኝ፡ አይገርመ
|ኝም።
መወለዴ፡ ከዚያ፡ ነው፡ ቤቴም፡ ዝምድናዬም፤
በዚህም፡ በንግድነቴ፡ ነጻነት፡ የለኝም።

፫፡ በእውነት፡ አንድ፡ የሣሌም፡ ልጅ፡ ልሆን፡
|ተወለድሁኝ።
ከሰይጣን፡ ኃይል፡ ከሕግም፡ ፍርድ፡ አርነት፡
|ወጣሁኝ።
በየሱስም፡ ለመንፈሴ፡ መዳን፡ ከገኘሁኝ፡
የአምላክ፡ ልጅ፡ በጸጋው፡ ነኝ፡ በርያም፡ አይ
|ደለሁኝ።

ፀ። ሊያድነኝ፣ በመስቀል፣ ላይ፣ በሞተው፣
|አምኜ፣
በሰጠኝ፣ ጸጋ፣ ውስጥ፣ ልኑር፣ እርሱን፣ ተ
|ማጥኜ፣
ከአብ፣ ዘንድ፣ እንደ፣ አመላጅ፣ ከቆመ፣ ስለኔ፣
በርሱ፣ ሊያየኝ፣ ጻድቅ፣ ነኝ፣ በርሱ፣ በመድኀኔ።

ፁ። ግን፣ በምግባር፣ በሕግ፣ ሥራም፣ ሊድን፣
|ለሞከረ፣
ስለርሱ፣ መደኅኑ፣ ሲሞት፣ በክንቱ፣ ነበረ።
በእምነት፣ ጻድቅ፣ እንዲድን፣ ነቢዩ፣ ነገረ።
በክርስቶስ፣ ሞት፣ ሥሉ፣ መዳን፣ ለኛ፣ ተፈ
|ጠረ።

ፂ። ስለኔ፣ ነፍሱን፣ ለውጦ፣ ፍጹም፣ በወደደኝ፣
በኔም፣ አይደል፣ በክርስቶስ፣ ግን፣ ሕያው፣
|በእምነት፣ ኑኝ።
ከእርሱም፣ ጋር፣ ተሰቅዬ፣ መኖኝ፣ በዓለም፣ ኑኝ።
የዓለምም፣ ወዳጅ፣ ልሆን፣ አሁን፣ ምን፣ ጠ
|ንቅ፣ አለኝ፣

ፃ። ወዳምላክ፣ ከተማ፣ ስደርስ፣ ከምድሩ፣ ሥ
|ቃይ፣
እረፍት፣ ሰላምም፣ ደስታም፣ ይቆየኛል፣ በላይ።

ልቅሶ፣ መጣጣር፣ ጩኸትም፣ አይገኝም፣ በ
|ሰማይ።
ሌትም፣ አይሆንም፣ ያምላክ፣ በግ፣ ነው፣ ያ
|ገሩ፣ ዐሐይ።

ፄ። በአንጨት፣ የተሰቀለውን፣ መድኃኒት፣ ካ
|የሁኝ፣
በምድር፣ የሚወደደውን፣ መሻት፣ ሰለቸሁኝ።
አንድ፣ ነገር፣ ብቻ፣ ፈልጌ፣ እርሱን፣ ተመኘ
|ሁኝ፣
ወዳንቺ፣ እየሩሳሌም፣ ለመድረስ፣ ናፈቅሁኝ።

ረሰቢኝ።

ፅፀ።

S. T. 724.

፩። ስንዳዝ፣ በደረቅ፣ አገር፣
ከዚህ፣ ከሚጠፋ፣ ዓለም፣
በዝማሬ፣ እንሻገር
ወደ፣ አዲስ፣ የሩሳሌም።
እንደ፣ ባሕር፣ ሞገድ፣ ጮኸት፣
ሰማያዊ፣ መዝሙሩ፣ ይደምቃል፣
ኃይል፣ ምስጋና፣ ክብር፣ ስግደት፣
ላምላክ፣ በግ፣ ይገባዋል።

፪፡ በዚህ፡ ታች፡ ለስደተኛ፡
ሐዘን፡ መከራም፡ ይበዛል፡
ግን፡ ለጽዮን፡ መንገደኛ፡
አክሊል፡ ተዘጋጅትዋል።
እንደ፡ ባሕር፡ . . . . . .

፫፡ እሥራኤል፡ በባቤል፡ ወንዝች፡
እያለቀሱ፡ ሲኖሩ፡
የየሩሳሌምን፡ ደጆች፡
ሁሉ፡ ቀን፡ ተዘከሩ።
እንደ፡ ባሕር፡ . . . . . .

፬፡ የሰማይ፡ ወፈሮች፡ ሁሉ፤
በዚህ፡ ታች፡ እንዳትቀሩ፡
በምላክ፡ ኃይል፡ በጽኑ፡ ቃሉ፡
ሁል፡ ጊዜ፡ ተዳፈሩ።
እንደ፡ ባሕር፡ . . . . . .

አኖ፡ ሌኖ።

ፍ፫፡

S. T. 316.

፩፡ መንገደኛ፡ መናኝ፡ ሁኛለሁ፡
ሌሊት፡ ብቻ፡ ሌሊቱን፡ በዚህ፡ ልደር።

ከአምላክ፡ ሕዝብ፡ ጋራ፡ እንዛለሁ።
እርሱም፡ ሲመራኝ፡ እከተላለሁ።
አታቁየኝ፡ እቸኩላለሁ።
ሌሊት፡ ብቻ፡ ሌሊቱን፡ በዚህ፡ ልደር።

፪፡ ፋሲክዬን፡ ልብላ፡ በፍጥነት፡
ቅዱስ፡ ደሙ፡ መድረኬንም፡ ነክትዋል።
አገሬን፡ ፈልጌ፡ ከባርነት፡
እግሬ፡ ተጫምዶ፡ ልውጣ፡ አርነት።
አምላክ፡ ጠራኝ፡ ለደህንነት።
ቅዱስ፡ ደሙ፡ ቅዱስ፡ ደሙ፡ ገዝቶኛል።

፫፡ በጉን፡ በልቼ፡ እቀምሳለሁ፡
የማገኘውን፡ የዘላለም፡ ደስታ።
የኃጢአትን፡ እርሾ፡ ትቻለሁ፡
መድኃኒቴን፡ እመለክታለሁ።
በጉን፡ በልቼ፡ እመኛለሁ፡
የማገኘውን፡ የዘላለም፡ ደስታ።

፬፡ ወደ፡ ከነዓን፡ ዓይኔ፡ ያያል፤
ለዘላለም፤ ለዘላለም፡ ብሩሕ፡ ነው።
በዚህ፡ በጨለማ፡ ሞት፡ ያስፈራል፡
ደከሚም፡ ወትሮ፡ ያስወድቀኛል።
ወደ፡ አገሬ፡ ዓይኔ፡ ያያል፡

ለዘላለም፡ ለዘላለም፡ ብሩሕ፡ ነው።

፫፡ በዚች፡ ምድር፡ እረፍት፡ አይገኝም፡
ወዲያ፡ ነው፡ ወዲያ፡ ነው፡ ምኞቴ።
በዚያ፡ ሞት፡ አያስለቅሰኝም፡
ድካም፡ አይሰማኝ፡ ጠላት፡ አይደርስም፡
ኃጢአት፡ አያስጨንቀኝም።
ወዲያ፡ ነው፡ ወዲያ፡ ነው፡ ምኞቴ።

፬፡ ቸር፡ እረኛዬ፡ አትተወኝ፡
ከኔ፡ ጋራ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ወትሮ፡ ሁን።
ወደ፡ ብዕዕናህ፡ እስክታደርሰኝ፡
ለዓይኔም፡ እስክትግለጥልኝ፡
ቸር፡ እረኛዬ፡ አትተወኝ፡
ከኔ፡ ጋራ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ወትሮ፡ ሁን።

ፈሰቲን።

ፍጌ፡

S. T. 311.

፩፡ ጢሰኛ፡ ስደተኛም፡ እንዳባቶቼ፡ ነኝ፡
ቤቱም፡ በላይ፡ ነው፡ እንጂ፡ በዚህ፡ በታች፡
አይገኝ።
በላይ፡ ግን፡ ቸር፡ አባቴ፡ ቤቱን፡ ከፍቶልኛል፡
እኔም፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ ልኖር፡ ያስመኘኛል።

ግሩም፡ ግሩም፡ ነው፡ ተስፋዬ።
ወዲያ፡ ስመለከት፡ ይግላል፡ ደስታዬ።

፪፡ ስለኔ፡ ሞትን፡ ቀምሶ፡ ከሞትም፡ ያዳነኝ፡
ያን፡ ቸር፡ ወዳጄ፡ የሱስ፡ በዚያ፡ ልገናኝ።
የደስታ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በዚህ፡ ቢኖረኝም፡
ወዲያ፡ ግን፡ ወደርሱ፡ ናፍቆት፡ አይለቀኝም።
ግሩም፡ ግሩም፡ . . . ።

፫፡ በምድር፡ ኃጢአቱ፡ ሁሉን፡ አረከሰ።
ውኃ፡ እንደሚፈስም፡ በሁሉ፡ ደረሰ።
በያስፈርድብኝ፡ እንኳ፡ ሰላም፡ ይነሣኛል፤
ወዲያ፡ ግን ስገባ፡ ፍጹም፡ ይለቀኛል።
ግሩም፡ ግሩም፡ . . . ።

፬፡ ልቄይ፡ ልታገሥ፡ ገና። አይቀርም፡ ተስፋዬ።
ሊወስደኝ፡ ወደ፡ አርሱ፡ ይመጣል፡ የሱስዬ።
አሁን፡ በእምነት፡ ብቻ፡ ያለኝን፡ ገንዘቤ፡
ልቀበለው፡ በምሉ፡ ስደርስ፡ ወዳገሬ።
ግሩም፡ ግሩም፡ . . . ።

ፈሰቲን።

ፍኒ፡

S. T. 555.

፩፡ የሱስ፡ ወደ፡ ሕይወት፡
ናፍቆት፡ ተነሣብኝ።
አይገኝም፡ ሕይወት፡ ዕረፍት፡
ዓለም፡ በሚሰጠኝ።
አሳቤን፡ የሚቀድስ፡
ልቤን፡ የሚያድስ፡
አውርድልኝ፡ መንፈስህን።
ጸጋን፡ አፍስስልኝ።

፪፡ ፈተናን፡ ለማሸነፍ፡
ክፉን፡ ድል፡ ለመንሣት፡
እኔን፡ በኃይልህ፡ ደግፍ፡
ጠብቀኝ፡ ከኃጢአት።
ከዋፋት፡ ልታድነኝ፡
ወደህ፡ የሞትክልኝ፡
በዳገት፡ ወይስ፡ በድልድል፡
ደስ፡ ብሎኝ፡ ልከተል።

፫፡ ከኃጢአት፡ ተለይቼ፡
ጸድቅ፡ ልሆንልህ፡
ቅዱስ፡ ማጽርያ፡ ለኔ፡

አቅርበህ፡ በደምህ።
በሰማይ፡ ዕድል፡ ላገኝ፡
መግባት፡ ሊሆንልኝ፡
ከመቃብር፡ ተነሣህ፡
ገብተሃል፡ በግርማህ።

፬፡ ብፁዕ፡ ለመሆን፡ ልመኝ፡
ከፍ፡ ልል፡ ከከንቱነት፡
በቸርነት፡ ጠራሽኝ፡
ለዘላለም፡ ሕይወት።
ከዚህ፡ ምድራዊ፡ ውርደት፡
ሽቅብ፡ ልመለከት፡
ወደዚያ፡ ለመግባት፡
ልደራጃ፡ በትግሃት።

፭፡ ደግሞ፡ እንዳይደልለኝ፡
ጠብቀኝ፡ ከዓለም።
ከክፉ፡ ምኞት፡ ለየኝ፡
ሕግህን፡ ልፈጽም።
በኪዳንህ፡ ልጠበቅ፡
ጸጋህን፡ አስታውቅ፡

ነፍሴን፡ በብሩክ፡ ስንብቻ፡
እስክምትጠራ።

O. E.

፫፻፮፡

S. T. 786.

፩፡ ወዳንተ፡ የሱስ፡ ሆይ፡
ልቤ፡ ይናፍቃል።
የአምላክ፡ በግ፡ ሁነህ፡
ስለኔ፡ መ·ተሃል።

፪፡ ሰላም፡ ለኔ፡ ሰጠህ፡
ተሸክመህ፡ ቅጣት።
ጠባቂዬም፡ ሁነህ፡
አወጣኸኝ፡ ከሞት።

፫፡ ለኔም፡ ባባቴ፡ ቤት፡
ስፍራ፡ አዘጋጀህ።
ዓይናችን፡ ያላየው፡
ብርሃኑም፡ አንተ፡ ነህ።

፬፡ ከዓለም፡ መሔዴ፡
በደረሰ፡ ጊዜ፡

ምራኝ፡በብርሃንህ፡
ልገባ፡ አገሬ።

ክፍለ፡ አግዚአ።

፫፻፱፡

S. T. 452.

፩፡ የሱስን፡ ያስፈልገኛል፡
በደሌን፡ ይቅር፡ ይላል፡
ጋሻም፡ ይሆንልኛል።
እርሱ፡ ብቻ፡ ያድነኛል፡
ፍቅሩም፡ ሕይወት፡ ነው፡ ለኔ።
የሱስ፡ ነው፡ መድኃኒቴ።

፪፡ ያለ፡ የሱስ፡ ተስፋም፡ የለኝ፡
ያለ፡ የሱስ፡ ምሕረትም፡
ምንም፡ አይሆንልኝም።
የሱስ፡ እምነትን፡ ከልሰጠኝ፡
አላገኝም፡ ለፍቼ።
የሱስ፡ ነው፡ መድኃኒቴ።

፫፡ ስለዚህ፡ ወዳንተ፡ የሱስ፡
እመጣለሁ፡ ለምኜ፡
ጸጋህን፡ ተማጥኜ።

እውነተኛውን፡ ሕይወት፡ ለኩስ፡
በተሰበረው፡ ልቤ።
አንተ፡ ነህ፡ መድኃኒቴ።

ረሱቲን።

፹፡

S. T. 207.

፩፡ አምላክ፡ ሆይ፡ የነፍሴን፡
ጕድለት፡ አስረዳኝ።
ጸጋን፡ እንዳገኝ።
ያን፡ ጠናማ፡ ጭንቀት፡
የመንፈስ፡ ድኅነት፡
አትውሰድብኝ።

፪፡ ያለም፡ መንገደኛ፡
እንደ፡ ችጋረኛ፡
ራሱን፡ በመከደ፡
ወደ፡ ክርስቶስ፡ ጸጋ፡
በምነት፡ እንዲጠጋ፡
ነው፡ ያምላክ፡ ፈቃድ።

፫፡ ለመዳንህ፡ ተግተህ፡
በምግባር፡ ተመክተህ፡

ጸድቅ፡ ከመባል፡
እንዳንድ፡ ምስኪን፡ ርኩስ፡
ብትድን፡ በየሱስ፡
ይህ፡ ይሻልሃል።

፬፡ የሱስ፡ ያዳናቸው፡
ምስኪኖች፡ ቀራጮች፡
አመሰገኑት።
ፈሪሳውያን፡ ግን፡
እንደ፡ ዓለም፡ መድኅን፡
አልተቀበሉት።

፭፡ ጽድቅን፡ በመፈለግ፡
ተስፋዬን፡ ከማድረግ፡
አምላክ፡ ያድነኝ።
ነገር፡ ግን፡ አ፡ የሱስ፡
ጸድቅና፡ ቅዱስ፡
አንተ፡ አድርገኝ።

ረሱቲን።

፹፩፡

S. T. 439.

፩፡ አ፡ የስሱ፡ የሕይወት፡ ውኃ፡
የጸጋ፡ ምንጭ፡ ሆንህልኝ።

ልቤ፡ የለመነውን፡ ስማ፡
በጸጋም፡ ፈጽመልኝ።
ታላቅ፡ ፍቅርህ፡ ግሩም፡ ስምህም፡
የከፈትህልኝ፡ እቅፍህም፡
ለነፍሴ፡ ድፍረት፡ ሰጠ።

፪፡ አ፡ የሱስ፡ ወደ፡ መስቀልህ፡
እጄን፡ እዘረጋለሁ።
ዓይኔንም፡ ወደ፡ ምሕረትህ፡
በተስፋ፡ አነሣለሁ።
የእውቀት፡ ዛፍ፡ ያፈራውን፡ ፍሬ፡
በመስቀል፡ ዛፍ፡ አ፡ መድኃኔ፡
ከለቀምኸው፡ ጠፋልኝ።

፫፡ ተመስገን፡ ቸር፡ መድኃኒቴ፡
ፍርዴን፡ ተሸከምህልኝ።
በማይመረመር፡ ርኅራኄ፡
ሞቴን፡ ተቀበልህልኝ።
ያጠፋውትን፡ ከፈልኸው፡
ሰማይን፡ ለኔ፡ ከፈትኸው፡
ስምህን፡ እንዳከብር።

፬፡ ዓይኔም፡ ሲዘጋ፡ አካሌም፡
ወደ፡ መሬት፡ ሲመለስ፡
ከመከራ፡ ከትካዜም፡
ድኜ፡ አንተን፡ ልወድስ።
ለአብ፡ ለወልድ፡ ለመንፈስም፡
ያሁን፡ ምስጋና፡ ውዳሴም፡
እስከ፡ ዘላለም። አሜን።

ረስኪን።

፻፴፪፡

S. T. 500.

፩፡ እወድሃለሁ፡ የሱስ፡ ሆይ፡
ወዴኔ፡ ና፡ ከኔም፡ ዘንድ፡ ቆይ፡
ከኔም፡ ተጣበርልኝ።
በዓለም፡ ሁሉ፡ ፈተና፡
ሥቃይም፡ ብዙ፡ አለና፡
አንተ፡ ሰላም፡ ሁንልኝ።
ነፍሴም፡ ሥጋዬም፡ በሚመር፡
ሥቃይ፡ ቢያልቅም፡ ይህ፡ ሳይቀር፡
ለልቤ፡ ተስፋ፡ ሰጠኸኝ።
አደራህን፡ ተቀበልኸኝ።
አ፡ የሱስ፡ አ፡ መድኃኒቴ፡
መድኃኒቴ፡
አንተ፡ ነህ፡ መጸናኛቴ።

፪፡ ምድራዊ፡ ድንኳኔ፡ ሲፈርስ፡
ወዳንተ፡ ነፍሴን፡ ሊያደርስ፡
መልአክህን፡ ላክልኝ።
ድኩም፡ ሥጋዬም፡ በሰላም፡
ይረፍ፡ ከምድሩ፡ ድካም፡
ድምጽህ፡ እስኪያስነሣኝ።
ስነሣም፡ ልይህ፡ ዓይን፡ ለዓይን፡
ከአንተም፡ ዘንድ፡ አዲሱን፡ ወይን፡
ልጠጣ፡ በብዕዕናህም፡
ልወድስህ፡ ላመስግንም።
መድኃኒቴ፡ ተቀበለኝ፡
ተቀበለኝ፡
ብኖር፡ ብሞትም፡ ያንተ፡ ነኝ።

ረሰቲን።

፹፫፡

S. T. 688.

፩፡ እጨነቃለሁኝ፡
በችግር፡ ኑሮዬ።
ደስታህን፡ ፍቅርህን፡
በላዬ፡ አፍስሰው።
ቆሙ፡ እርዳኝ፡ በፍቅር፡

ቀኑ፡ ሳይደርስብኝ፡
ክቡር፡ ጸጋህ፡ ለከንቱ፡
እንደልቀበለው።

፪፡ ተስፋዬ፡ ምሉ፡ ነው፡
በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም።
አይጨክንብኝም፡
የደከምሁኝ፡ ልጁን።
የከበደ፡ ዕዳዬን፡
ተሸከመው፡ በመስቀል።
ስለዚህ፡ እኖራለሁ፡
በይቅርታው፡ ጸላ።

፫፡ እንዴት፡ ልሆን፡ ይሆን፡
እርሱን፡ ስተው፡ ጊዜ፡
በዓለም፡ ፈጪለማ፡
እቸገራለሁኝ።
ወዴት፡ ግን፡ ይመጣል፡
ብርሃን፡ ሕይወትም፡ ይዘ፡
ወደ፡ ሰማይ፡ ለመምራት፡
ለማውጣት፡ ከሥቃይ።

ተወልደ፡ ብርሃን።

ዝ፱።

S. T. 219.

፩ ጌታ፡ ፍቅርህን፡ የሚነግረኝ፡
ድምጽህን፡ አሰማለሁ።
ያንተ፡ ገንዘብ፡ ነኝ፡ አንተም፡ ጠብቀኝ፡
ጸጋህን፡ አመኛለሁ።
ወደ፡ አንተ፡ የሰዱ፡ አቅርበኝ፡
ሳበኝ፡ ወደ፡ መስቀልህ።
በተወጋውም፡ ጐድንህ፡ ወትሮ፡ ሠውረኝ።
ሳበኝ፡ ወደ፡ መስቀልህ።

፪ ላገለግልህ፡ አምላክ፡ ቀድሰኝ፡
በምላክዊ፡ ኃይልም፡ ና።
ታላቅ፡ ፍቅርህም፡ ጸጋህን፡ ይስጠኝ፡
ካንተ፡ ዘንድ፡ ወትሮ፡ ልጽና።
ወደ፡ አንተ፡ . . . ።

፫ አ፡ መድኃኒቴ፡ ካንተ፡ ጋር፡ ስገኝ፡
በግርህ፡ ተንበርክኬ፡
ፈተሀንም፡ ሳይ፡ እኔ፡ ብዙ፡ ነኝ፡
ካንተ፡ ዘንድ፡ አ፡ አምላኬ።
ወደ፡ አንተ።

፬ ግን፡ የሞትን፡ በሕር፡ ተሻግሬ፡

ፍቅርህ፡ ለኔ፡ ግልጥ፡ ሲሆን፡
አዲስ፡ መዝሙሩን፡ ላንተ፡ ዘምሬ፡
የሚሆነኝ፡ ምን፡ ይሆን፡
ወደ፡ አንተ።

ረስቲኝ።

ዝ፳።

S. T. 95.

፩ ያልደረስሁበት፡ አክሊል፡ አለኝ።
አ፡ አምላኬ፡ አሳስብኝ።
በምድርም፡ እንዳይጠፋብኝ፡
ስታክት፡ ና፡ አስጠንቅቀኝ።

፪ ያልደረስሁበት፡ ርስትም፡ አለኝ።
እንዳላባክነው፡ እርዳኝ።
በወጽመዱም፡ እንዳያጸምደኝ፡
ከሰይጣን፡ ተንኰል፡ ጠብቀኝ።

፫ አ፡ ጌታዬ፡ አ፡ የሞትሀልኝ፡
በቅዱስ፡ እጅህ፡ ደግፈኝ።
ወደ፡ ሰማይም፡ ስታደርሰኝ፡
ያን፡ ቅዱስ፡ አክሊሉን፡ ስጠኝ።

ረስቲኝ።

ቁጥር

፩፡ ቀር፡ ፬፡ ጅሀ። S. T. 380.

፩፡ ሁሉም፡ ሩጠው፡ አክሊል፡ አንድ፡ ያገኛል።
ወንድሜ፡ እንደታገኘው፡ ጣር።
ፈት፡ የገቡት፡ ወደ፡ አምላክ፡ ጸዳል፡
ይመለከታሉ፡ ያንተን፡ ጸር።
ስትሮጥም፡ ዓይንህ፡ አይገላመጥ፡
የከንቱነት፡ ደስታ፡ አትመኝ።
መንፈስ፡ ቅዱስም፡ የሚለውን፡ አድምጥ፡
ቅዱስ፡ አክሊሉን፡ እንድታገኝ።

፪፡ የሚጠፋውን፡ አክሊል፡ ለማግኘት፡
የሚመኝ፡ በጣም፡ ይጋደላል።
አንተም፡ ለዘላለም፡ ደህንነት፡
ዓለምን፡ መከድ፡ ይገባሃል።
የዚህ፡ ዓለም፡ ጥቅም፡ ምን፡ ይረባል፤
አንድ፡ ጠስ፡ ይሸሻል፡ ደስታው።
የሱስ፡ የሚሰጠው፡ ግን፡ ይቆያል፡
በርሱ፡ የሚያምን፡ ብፁዕ፡ ነው።

፫፡ የሱስ፡ ላንተ፡ መስቀሉን፡ ሲሸከም፡
ቅዱስ፡ አክሊሉን፡ ዋጅቶልሃል።
በርሱ፡ የሾህ፡ ዘውድ፡ ስለተጫነም፡

የብፅዕና፡ ዘውድ፡ ይቆይሃል።
የሰማይን፡ ርስት፡ እንዳታስክን፡
እንዳታጣ፡ ቅዱስ፡ አክሊሉን።
በመድኃኒታችን፡ ግን፡ ስታምን፡
እስከ፡ ሞት፡ ድረስ፡ የጸናህ፡ ሁን።
ረሱቲ።

ቁጥር

S. T. 761.

፩፡ በመላ፡ ዓለም፡ ጭንቀት፡ ይበዛል፡
በሽታና፡ ድካም፡ መልቶበታል።
ጦር፡ መረረን፡ ኃጢአት፡ ይገፋል፡
ፈተና፡ ቀርቦ፡ ይሸምቃል።

፪፡ በዬት፡ ይገኛል፡ ሕይወት፡ ለሞቱ፡
መድኅን፡ ለሕሙም፡ ኃይል፡ ለዛሉ፡
ምግብ፡ ለተራቡ፡ ደስታ፡ ለባቡ፡
ድፍረት፡ ለፈሩ፡ ለደከሙ፤

፫፡ ወንጌልን፡ ስሙ፡ የሱስ፡ ሲጠራ፤
ሁሉ፡ ወደኔ፡ አሁን፡ ይምጣ።
ራብተኛ፡ ይዋገብ፡ ጥማተኛ፡ ይርካ፡
ሕዙን፡ ይቀበል፡ ቅዱስ፡ ደስታ።

፬፡ እርሱ፡ ሞተልን፡ አስታረቀን፡

አፍስሶ፡ ደሙን፡ ሊዋጀኝ።
ጽድቅን፡ አመጣ፡ ሰላም፡ አስገኘ።
ጸጋን፡ ይሰጣል፡ ለታመነ።

፫፡ ጤናና፡ ሕይወት፡ የሚፈስበት፡
ያደርገናል፡ አዲስ፡ ፍጥረት፡
ይሰድረናል ፍቅር፡ ቸርነት።
የሱስ፡ አግባልን፡ ጽኑ፡ እምነት።

O. E.

፹፰፡

I. C. 180.

፩፡ ሐዘን፡ ወይም፡ ደስታ፡ የሚደርሰኝ፡
ማን፡ ያውቃል፤
መድኃኒታችን፡ ከኛ፡ ዘንድ፡ ከሆነ፡
ይበቃናል።
በየዋህ፡ ድምጽህ፡ ያርፋል፡ ነፍሳችን።
ሰላምና፡ ደስታ፡ በጭንቀት፡ አለን።

፪፡ ሕማማት፡ ሁሉ፡ በአንተ፡ ስንአምን፡
ይበርዳል።
ኃይል፡ በድካም፡ ረድኤት፡ በመከራችን፡
ይሆነናል።

ጭንቀት፡ የሞላ፡ ይህ፡ ምድራዊ፡ ሕይወት፡
ከአንተ፡ ዘንድ፡ ይሆነናል፡ ገነት።

፫፡ ምድር፡ ሲበራ፡ ኃጢአት፡ ስለ፡ በዛ፡
ይጨልማል።
ከንተ፡ ከዳን፡ ስለዚህ፡ ፊትህ፡ ከኛ፡
ይሠወራል።
ወደ፡ ምሕረትህ፡ እንማጠናለን፡
በርኅሩኅ፡ ብብትህ፡ አሳርፈን።

፬፡ አ፡ ቸሩ፡ የሱስ፡ በሕይወት፡ በሞትም፡
ረዳችን፡ ሁን።
አሰልፈን፡ ከክፋት፡ ስንገዋም፡
ስጠን፡ ድሉን።
ሁን፡ ከኛ፡ ዘንድ፡ ቀናችን፡ ሲመሽብን፡
ብርሃን፡ ሁንልን፡ ደስታን፡ ዐድለን።

O. E.

፹፱፡

ዮሐ፡ ፰፡ ፲፯። ሮሜ፡ ፰፡ ፲፯። S. T. 380.

፩፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወንድም፡ ከሆነልኝ፡
ከርሱም፡ ጋራ፡ የምወርስ፡ ብሆን፡
ሐዘን፡ ሁሉ፡ ከኔ፡ ይራቅልኝ፡

የምጨነቅስ፣ በምን፣ ይሆን፣
አምላካችን፣ ወንድሜ፣ ሆነልኝ።
ነገሩ፣ እንዴት፣ ይገርመኛል፣
ለአእምሮዬም፣ በይታይልኝ፣
ቃሉ፣ ፈጽሞ፣ ያስረዳኛል።

፫፣ እርሱ፣ አምላኬና፣ አምላካችሁ፣
አባቴም፣ የናንተ፣ አባት፣ ነው፣
የኔ፣ ወንድሞች፣ እናንተ፣ ናችሁ፣
ሲል፣ ተስፋችን፣ በርሱ፣ ምሉ፣ ነው።
እንደ፣ ምኞቴ፣ እንኳ፣ በይሰማኝ፣
ከቶ፣ የርሱ፣ ቃል፣ አይፋለስም።
ነፍሴ፣ ሆይ፣ ይህንን፣ ቃል፣ ስታገኝ፣
ምነው፣ በርሱ፣ ደስ፣ አላለሽም፣

፫፣ በሰው፣ ሐሳብ፣ ከቶ፣ የማይመዘን፣
ግሩም፣ የሆነ፣ ወንድምነት፣ ነው።
የሱስ፣ ክርስቶስ፣ በሚወርሰው፣ መጠን፣
ርስቱም፣ ከርሱ፣ ጋራ፣ እኩል፣ ነው።
በመሞቱ፣ የተከፈተልኝ፣
መንግሥቱም፣ ይቄየኛል፣ በላይ።

አምላኬ፣ ሕዋሳቴን፣ አብራልኝ፣
ርስቴንም፣ ለእምነቴ፣ አሳይ።

ረስቲን።

፯፣

S. T. 259.

፩፣ ደስ፣ ይበለኝ፣ ሐዘን፣ ይራቀልኝ፣
እግዚአብሔር፣ ይወደኛል።
አምላካችን፣ አባት፣ ከሆነልኝ፣
ስለ፣ ልጁ፣ እርሱ፣ ያስባል።
በየደቂቃው፣ የደረሰኝን፣
አባቴ፣ በፍቅሩ፣ ልክታል፣
ለየቀኑም፣ የሚጠቅመኝን፣
ደስታም፣ ሐዘንም፣ ያከፍላል።

፪፣ ጨኸቱን፣ ሊሰማ፣ አይሰለችም፣
ሽክሜንም፣ ያነሣልኛል።
በድካሜ፣ ከኔ፣ ዘንድ፣ አይለይም፣
ስሙም፣ መከር፣ ኃያል፣ ይባላል።
ክበር፣ ገንዘቡ፣ እንዳይጠፋበት፣
እርሱ፣ ራሱ፣ ይጠነቀቃል።
እንደ፣ ቀኑም፣ ኃይሉ፣ ሊሆንለት፣
ልጁን፣ ጸጋው፣ ያበረታዋል።

፫፡ አምላኬ፡ እንዲህ፡ ስታስብልኝ፡
እኔስ፡ ሐሳቤን፡ ልተው፡ እርዳኝ።
እምነቴን፡ ከቃልህ፡ ጨምርልኝ፡
በጅህም፡ ወዳገሬ፡ ምራኝ።
ደስ፡ ሲለኝ፡ ስጨነቅም፡ በሐዘን፡
አንተ፡ ሁሉን፡ እንደሰጠኸኝ፡
ተስፋህን፡ ተቀብዬ፡ ለማመን፡
ጌታ፡ ሆይ፡ አንተ፡ አስተምረኝ።

ረስቲን።

፯፩፡

S. T. 506; 505.

፩፡ አ፡ ነፍሴ፡ ላምላክሽ፡ ተሰጪ፡
ተስፋሽም፡ እርሱን፡ አድርጊ።
በትካዜም፡ ስትበሳጪ፡
ረድኤትን፡ ከርሱ፡ ፈልጊ።
አምላክን፡ የሚታመነው፡
ቤቱን፡ አያሠራም፡ ባሸዋው።

፪፡ የማጸናናት፡ ወቅት፡ ይመርጣል፡
ጥቅምህንም፡ ያስባል።
የምትለምነውን፡ ይሰጣል፡
ቁዘማህም፡ ይሰማዋል።
ባልታሰበም፡ ጊዜ፡ ረድኤት፡
ይሰጥሃል፡ በምሕረት።

፫፡ ችግርህ፡ እንኳ፡ ቢበረታ፡
አምላክ፡ የጣለህ፡ አይምሰልህ።
ሐዘን፡ ይለውጣል፡ በደስታ፡
ከሐዘን፡ ደስታ፡ ሲሻልህ።
ሁሉ፡ ጊዜም፡ ይወድሃል፡
መዳንህንም፡ ያስባል።

፬፡ ታላላቆቹን፡ ገዝቶ፡ ለማድረግ፡
ለአምላካችን፡ ቀላል፡ ነው።
መሳኪኖቹንም፡ ማበልጠግ፡
ለርሱ፡ የማያስቸግር፡ ነው።
ልዑል፡ አምላክ፡ በምክሩ፡
ያስገርማል፡ መንክር፡ ግብሩ።

ረስቲን።

፯፪፡

S. T. 121.

፩፡ ስትጨነቅ፡ ሳለህ፡ ጥራ፡ የሱስን፡
እርሱ፡ የአንተም፡ ረዳት፡ ነው።

ያለህን፡ ድካም፡ ግለጥለት፡ አሁን፡
ችግርህንም፡ ንገረው።
በኃይሉ፡ ብርታት፡ ልትበረታ፡ ነህ፡
ግን፡ በአንተ፡ ኃይል፡ መተሃል፡ ፈጽመህ።
ስለዚህ፡ ቸኩል፡ ወደ፡ የሱስም፡ ሽሽ፡
የጸጋ፡ ኃይሉን፡ ልበሰው።

፪፡ አምላክሽን፡ ጭንቅህን፡ ሁሉ፡ ያያል፡
ጩኸትህንም፡ ይሰማል።
የሚያድስ፡ ኃይልም፡ ይሰድልሃል፡
በእምነት፡ ብቻ፡ ተቀበል።
አንተን፡ ይወዳል፡ አንተን፡ ይረዳልም።
ነፍስህ፡ እንዲሞት፡ ከቶ፡ አልወደደም።
ስለዚህ፡ የሱስን፡ ለመሞት፡ ላከው፡
በሞቱም፡ ሁሉን፡ አዳነ።

፫፡ መከራህንም፡ እስኪሸር፡ ቢዘገይ፡
በጭንቀት፡ ስትጮስቀኝ፡
ወደ፡ ላይ፡ አሻቅበህ፡ የሱስን፡ እይ፡
ጨለማህንም፡ ያርቃል።
ተስፋህ፡ አድርገው፡ ለሁሉ፡ ዘመንህ።
እርሱ፡ ኃይልህ፡ ነው፡ ከሞትህ፡ ያዳነህ።

ብርሃኑን፡ ይመራል፡ በልብህ፡ ገብቶ፡
ዕውረትህንም፡ ያበራል።

ተወልደ፡ ብርሃን።

፯፫፡

S. T. 8.

፩፡ የአምላኬን፡ ውለታ፡ ሁሉ፡
ልቄጥረው፡ ያቅተኛል።
ከላይ፡ እንደወረደው፡ ጠሉ፡
በሁሉ፡ ተረፍርፍዋል።
የአምላኬን፡ ወለታ፡ ሁሉ፡
ልቄጥረው፡ ያቅተኛል።

፪፡ ሳይሰየም፡ ሳይመዘን፡ ይቀራል፡
የፍቅሩ፡ የጸጋውም፡ ብዛት።
በጨለማ፡ ውስጥ፡ ግን፡ ያበራል፡
በሌትም፡ ይሰጣል፡ ንጋት።
ሳይሰየም፡ ሳይመዘን፡ ይቀራል፡
የፍቅሩ፡ የጸጋውም፡ ብዛት።

፫፡ ልመዝነው፡ ከቶ፡ ባይቻለኝ፡
ይልቅ፡ ላመሰግነው፡ ነኝ።
የውለታው፡ ትሩፋት፡ ከለኝ፡

የፍቅሩ፡ ብርታት፡ ታወቀኝ።
ልመገነውም፡ ከቶ፡ ባይቻለኝ፡
ይልቅ፡ ላመሰግነው፡ ነኝ።

ረዐተ።

፻፲፡

S. T. 217.

፩፡ በልብህ፡ ያለውን፡ ትከዜህን፡ ጣል፡
በተስፋም፡ ተቀበል፡ የየሱስን፡ ቃል።
በጣም፡ ብትጨነቅ፡ በዚህ፡ በመሬት፡
ከለይ፡ ተጠባበቅ፡ የጌታን፡ ረድኤት።

፪፡ ድካምህን፡ ሁሉ፡ ለየሱስ፡ ንገር፡
ያዳምጥሃል፡ አትመረር።
ሐዘንህም፡ ሁሉ፡ በርሱ፡ እስኪሻር፡
አምላክን፡ በእምነት፡ መጠበቅ፡ ተማር።

፫፡ ከአንተ፡ ይልቅ፡ የተቸገሩትም፡
እንዳሉ፡ ለማሰብ፡ ይገባሃልም።
ለርሳቸውም፡ ረድኤት፡ ልትሰዋ፡ ብትግር፡
በእርግጥ፡ ይቀላል፡ የራስህ፡ ችግር።

ረዐተ።

፻፲፩፡

S. T. 600.

፩፡ ሐዘንተኛን፡ ያጸናናው፡
የመድኃኒታችን፡ ስም፡
ያንን፡ ቅዱስ፡ ስም፡ የጠራው፡
ይረዳል፡ ይድናልም።
ቅዱስ፡ ስም፡ ብፁዕ፡ ስም፡
የዘላለም፡ ተስፋ፡ ነው።

፪፡ ብርቱ፡ ጋሻም፡ ይሁንለት፡
ኃጢአት፡ ሲፈትነው።
ልመናውም፡ ይፈጸምለት፡
ከየሱስ፡ የለመነው።
ቅዱስ፡ ስም፡ . . . ።

፫፡ ያ፡ ክቡር፡ የየሱስ፡ ስምም፡
ብዕዕናን፡ ይሰጠናል።
ሕይወት፡ ደስታም፡ ሰላምም፡
ከዚህ፡ ስም፡ አግኝተናል።
ቅዱስ፡ ስም፡ . . . ።

፬፡ ወደ፡ ሰማያዊ፡ አገር፡
አድኖ፡ ሲያደርሰን፡
ያንን፡ ስም፡ ለአምላክ፡ ክብር፡

እንዘምር፡ አክብረን።
ቅዱስ፡ ስም፡ . . . ።

ረሱቲን።

የጸሎትና፡ የምስጋና፡ መዝሙራት።

፻፲፡

S. T. 623.

፩፡ የሱስ፡ ሆይ፡ አትለፍብኝ፡
ጸሎቴን፡ ስማ።
ሕዝብህ፡ ጸጋህን፡ ሲያገኝ፡
እኔንም፡ እርዳ።
የሱስ፡ ክርስቶስ፡ እኔንም፡ ስማኝ፡
ሕዝብህ፡ ጸጋህን፡ ሲያገኝ፡
አትለፍብኝ።

፪፡ የሱስ፡ ሆይ፡ ወደ፡ ዙፋንህ፡
አሁን፡ ቀረብሁ።
አምናለሁ፡ በሥልጣንህ፡
ልብስህን፡ ነካሁ።
የሱስ፡ ክርስቶስ፡ . . . . . ።

፫፡ ስለ፡ ምሕረትህ፡ ብቻ፡
ጸጋህን፡ ስጠኝ።

ልቤንም፡ በደምህ፡ ሂጸጽ፡
ረጭተህ፡ አንጻኝ።
የሱስ፡ ክርስቶስ፡ . . . . . ።

፬፡ ተስፋ፡ ያለ፡ አንተ፡ ፍቅር፡
አይገኝልኝም።
በሰማይና፡ በምድር፡
ሌላ፡ የለኝም።
የሱስ፡ ክርስቶስ፡ . . . . . ።

ረሱቲን።

፻፸፫፡

S. T. 273.

፩፡ አንተን፡ የሱስ፡ ሆይ፡ እሻለሁ፡
እኔ፡ ጥፋተኛ፡ ነኝ።
ያለ፡ አንተም፡ እጠፋለሁ፡
ያለ፡ አንት፡ የሞትሁም፡ ነኝ።
ቅዱስ፡ ክቡር፡ ደምህ፡ ብቻ፡
ሊያጠራኝ፡ ይችላል።
ያንተ፡ ጽድቅ፡ ያንተም፡ ይቅርታ፡
እኔንም፡ ያጸድቀኛል።

፪፡ አንተን፡ የሱስ፡ ሆይ፡ እሻለሁ፡
እኔ፡ ራሴ፡ ዕውር፡ ነኝ።

ወትሮ፡ እንከራተታለሁ፡
መንገዱንም፡ አላገኝ።
ና፡ በእውነትህ፡ ብርሃንም፡
እጅን፡ ይዘህ፡ ምራኝ።
ባንተ፡ ጽድቅ፡ በንተ፡ ሥልጣንም፡
ወደ፡ መንግሥትህ፡ አግባኝ።

፫፡ አንተን፡ የሱስ፡ ሆይ፡ እሻለሁ፡
በዚህ፡ ስደተኛ፡ ነኝ።
ርስት፡ በላይ፡ ተቀብያለሁ።
አንተ፡ ራስህ፡ ሰጠኸኝ።
ወደዚያም፡ እጓዛለሁ፡
መንገዴም፡ ሸካራ፡ ነው።
የሱስ፡ ሆይ፡ አንተን፡ እሻለሁ።
ኃይልህ፡ ብቻ፡ ኃይሌ፡ ነው።

፬፡ አንተን፡ የሱስ፡ ሆይ፡ እሻለሁ፡
በደለኛን፡ የሚችል።
አንድ፡ ወዳጅ፡ እፈልጋለሁ፡
ክፉውንም፡ የማይጥል።
አንተም፡ ሰርክ፡ ትወደኛለህ፡
አንተ፡ አትጥለኝም፡

ጉድለቴንም፡ ታውቃለህ፡
ፍቅርህ፡ ግን፡ አይተወኝም።

፭፡ አንተን፡ የሱስ፡ ሆይ፡ እሻለሁ፡
በፈቃድህም፡ ምራኝ።
መንፈስህንም፡ እሻለሁ፡
እርሱን፡ የሱስ፡ ሆይ፡ ምላኝ።
እርሱ፡ ትልቅ፡ ኃጢአቴን፡
ሁሉ፡ ቀን፡ ያሳስበኝ፡
እርሱም፡ የስርየት፡ ብዛትን፡
ባንተ፡ ቃል፡ ያስተምረኝ።

፮፡ በምድራዊ፡ ሕይወት፡ ሳለሁ፡
ሲያልቅብኝም፡ ቀኔ፡
አንተን፡ የሱስ፡ ሆይ፡ እሻለሁ፡
እንድድን፡ ከከሩኔ።
አንድ፡ እርምጃ፡ ለመራመድ፡
ያለ፡ አንተ፡ አልችልም።
ከኔ፡ ጋር፡ ግን፡ ብትዛመድ፡
አንዳችም፡ አይጐድለኝም።

፯፡ አንተን፡ የሱስ፡ ሆይ፡ እሻለሁ፡
አንተ፡ ብቻ፡ ሀብቴ፡ ነህ።
አንተንም፡ አንድ፡ ቀን፡ አያለሁ፡

በአብ፡ ቀኝ፡ ተቀምጠሀ።
ወደ፡ ጽዮንም፡ ተራራ፡
አድነህ፡ ስታደርሰኝ፡
ደምህ፡ ከገዛቸው፡ ጋራ፡
ክብርህን፡ ልዘምር፡ ነኝ።

ረሱቲን።

፻፷፫፡

S. T. 203.

፩፡ መድኃኒቴ፡ ወዴት፡ ና፤
የሕይወቴን፡ መንገድ፡ አብራ።
ሲነጋልኝ፡ ሲመሽብኝም፡
አ፡ ቸር፡ የሱስ፡ ወዴት፡ ና።

፪፡ ወዳንተ፡ ቅርብ፡ አስከትለኝ፡
እንዳልሰናከል፡ ደግፈኝ።
በደስታና፡ በለዘን፡ ጊዜ፡
ወዳንተ፡ ቅርብ፡ አስከትለኝ።

N. N.

፻፸፡

S. T. 786.

፩፡ ቸሩ፡ መድኃኒቴ፡
የመጣ፡ በፍቅሩ፡

በዓለምም፡ ውርደት፡
ከጥንታዊ፡ ክብሩ።

፪፡ ፍቅሩም፡ አደረሰው፡
በመከራና፡ ሞት።
ሕይወቴን፡ ለማዳን፡
ተሸከመ፡ ቅጣት።

፫፡ አቤቱ፡ ፍቅርህን፡
ግለጠው፡ በላዬ።
ብርሃንህን፡ ስጠኝ፡
በጨለመ፡ ልቤ።

፬፡ በጨለማ፡ ዓለም፡
ለታመረ፡ ነፍሱ፡
የጸጋ፡ አርነት፡
ግለጠው፡ በራሱ።

ተወልደ፡ ብርሃን።

፻፸፩፡

S. T. 493.

፩፡ አ፡ የሱስ፡ ከኔ፡ ተባበር፤
የሚጐዳውን፡ አባርር፡

ወዳንተ፡ ተማጥኜ።
የሱስ፡ ሆይ፡ ሰርክ፡ ሁን ከኔ።

፪፡ የሱስ፡ ከኔ፡ ዘንድ፡ ከሆንህ፡
ነፍሴን፡ በጸጋህ፡ ከጦርህ፡
አንድ፡ አይጐድልም፡ ለኔ።
የሱስ፡ ሆይ፡ ሰርክ፡ ሁን፡ ከኔ።

፫፡ ከዚህች፡ ዓለም፡ ስሰናበት፡
በሰማይ፡ አግባኝ፡ በምሕረት፡
ላቅርብልህ፡ ውዳሴ።
የሱስ፡ ሆይ፡ ሰርክ፡ ሁን፡ ከኔ።

O. È.

፻፩፡

S. T. 441.

፩፡ ኦ፡ መንፈስ፡ ሕይወትን፡ ላገኝ፡
ነፍሴን፡ በእውነት፡ ምራ።
በሰጠኸን፡ ቅዱስ፡ ቃል፡
ብርሃን፡ በልቤ፡ አብራ።
በአንተ፡ ኃይልና፡ ፍቅር፡
ተደግፌ፡ ያንተን፡ ምክር፡
በንብረቴ፡ ላመስግን።

N. N.

፻፪፡

S. T. 492.

፩፡ የሱስ፡ ሆይ፡ የልቤ፡ ተስፋ፡
ነፍሴን፡ ደስ፡ የምታሰኝ፡
በረከትን፡ ለኔ፡ አስፋ፡
ከቃልህ፡ ብርሃን፡ ስጠኝ።
ና፡ ወደኔ፡ የሱስ፡ ሆይ፡
ከኔ፡ ዘንድ፡ ዘወትር፡ ቆይ።

፪፡ በቅዱስ፡ ስምህ፡ አጅምር፡
ዕለት፡ ዕለት፡ ስራዬን።
ምረቃን፡ በላዩ፡ ጨምር፡
እስክፈጽም፡ ዕድሜዬን።
ና፡ ወደኔ፡ . . . ።

፫፡ ያፈን፡ ቃል፡ የልቤን፡ አሳብ፡
በምሕረትህ፡ እይልኝ።
የማይጠፋ፡ ሀብት፡ ልሰብስብ፡
ለመማር፡ ሰርክ፡ ቀስቅሰኝ።
ና፡ ወደኔ፡ . . . ።

፬፡ ለመተኛት፡ ሲመሽብኝ፡
ጠብቀኝ፡ ቸሩ፡ ጌታ።

አትራቅ፡ ቀን፡ ሲነጋልኝ።
የሱስ፡ ሁን፡ ከኔ፡ ጋራ።
ና፡ ወደኔ፡ . . . ።

ሉንጂል።

ያቮ፡

S. T. 201.

፩፡ አሙቀ፡ አ፡ የሱስ፡ የልቤን፡ ፍቅር፡
እርዳኝ፡ ልጋደል፡ ለአንተ፡ ክብር።
የወንጌል፡ መልእክት፡ ይስፋ፡ በምድር፡
መንግሥትህ፡ ይልማ።

፪፡ የቀና፡ እምነት፡ ስጠኝ፡ ልጋደል፡
ደግሞም፡ ልታገሥ፡ ኃይልህን፡ ወድል።
ድልን፡ ዕረፍትን፡ እርዳኝ፡ ልቀበል፡
ሩጫን፡ ስፈጽም።

N. N.

ያዐ፡

S. T. 273.

፩፡ የሱስ፡ ልቤን፡ ውሰድልኝ፡
አንተ፡ ተከባክበኝ።
ጉድለት፡ ሁሉ፡ ቢኖርብኝ፡

ለዘላለም፡ ያንተ፡ ነኝ።
ሕይወትና፡ ኃይል፡ አጣለሁ፡
እወድቃለሁ፡ ሁሉ፡ ቀን።
በንተ፡ ብቻ፡ ተጥያለሁ፡
ከእናቴ፡ ማሕፀን።

፪፡ እኔ፡ አንድ፡ ምስኪን፡ ድኃ፡ ነኝ፡
አንተ፡ ሀብታም፡ ጌታ፡ ነህ።
አንተም፡ ከመሞት፡ አዳንኸኝ፡
መቅሠፍቴን፡ ተሸክመሀ።
ኃጢአቱም፡ ቢያስፈራኝ፡
ዓይኔን፡ ወደ፡ አንተ፡ ሳብ።
አንተ፡ ከርሱ፡ ልታጠራኝ፡
አፍስሰሃል፡ የደም፡ ላብ።

፫፡ የሱስ፡ ሆይ፡ የሠራሀልኝ፡
ለዘላለም፡ በቂ፡ ነው።
ሕግህም፡ እንዳይፈርድብኝ፡
አንተ፡ ራስህ፡ ፈጸምኸው።
አንተ፡ ስትነግረኝም፡
አምኜ፡ ልቀበለው።

ሌላ፡ አያስፈልገኝም።
ጸጋህን፡ ላመስግነው።

ረሰቲን።

የ፭፡

S. T. 448.

፩፡ ስማልኝ፡ የሱስ፡ ጸሎቴ፡
አድርግ፡ መቅደስህን፡ በውስጤ።
አግባ፡ ሰላምን፡ በልቤ።
አ፡ የሱስ፡ አትራቅ፡ ከኔ።

፪፡ የዋህ፡ አባት፡ ሁነህ፡ ምራኝ፡
ሲጨልም፡ ብርሃን፡ ሁንልኝ።
አንተን፡ በሁሉ፡ ደስ፡ ላሰኝ፡
የመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ኃይል፡ ስጠኝ።

፫፡ ልጁን፡ ለላክ፡ ለኃጥአን፡
ላደረገኝ፡ ብፁዓን፡
ቁጭ፡ ላለ፡ በሰማይ፡ ዙፋን፡
ይሁን፡ ግርማ፡ ክብረት፡ ሥልጣን።

O. E.

የ፯፡

S. T. 444.

፩፡ አ፡ የሱስ፡ አምላኬ፡
ለቃልህ፡ ታዝዜ፡
ወዳንተ፡ እቀርባለሁ።
ጸጋህንም፡ እሻለሁ።
በደምህ፡ ሕሊናዬ፡
ይረጭ፡ ከኃጢአቴ።

፪፡ ዘላለም፡ ያንተ፡ ነኝ፡
የሚል፡ እምነት፡ ስጠኝ።
ከአንተም፡ ከሚለየኝ፡
ልርቅ፡ ረድኤት፡ ሁንልኝ።
ሞትም፡ በማይደርስብኝ፡
በመንግሥትህ፡ አኑረኝ።

ረሰቲን።

የ፯፡

S. T. 201.

፩፡ ና፡ ጌታ፡ የሱስ፡ ልቤን፡ አሙቀው።
የክብር፡ ንጉሥ፡ ጣያትን፡ አርቀው።
በውሥጤም፡ ንግሥ፡ ኃጢአቴን፡ ፋቀው።
ና፡ ጌታ፡ የሱስ።

፪፡ አ፡ ቸር፡ ወዳጄ፡ መንፈሴን፡ ጐብኘው።
አንተ፡ ነህ፡ ረጂ፡ ደስ፡ የምታሰኘው።
ጸጋህን፡ ከእጅህ፡ አውን፡ እንዳገኘው፡
ና፡ ጌታ፡ የሱስ።

፫፡ ና፡ ደስ፡ አሰኝኝ፡ በሐዘን፡ ሁሉ።
ፍርሃት፡ ሲይዘኝ፡ ጭንቀትም፡ ምሉ፡
ና፡ ጌታ፡ አድነኝ፡ ከሚጐዳኝ፡ ሁሉ።
ና፡ ጌታ፡ የሱስ።

፬፡ የሱስ፡ ሲመጣ፡ በማይወሰን፡ ክብር፡
ልቡ፡ የነጻ፡ ቢያገኝ፡ ድንቅ፡ ነገር፡
በቶሎ፡ ይምጣ፡ ይቅረብ፡ በፍቅር።
ና፡ ጌታ፡ የሱስ።

ሉንሂል።

፻፸፡

S. T. 95.

፩፡ አ፡ አባት፡ አ፡ መድኃኒታችን፡
በጸጋህ፡ ኃይል፡ ወደኛ፡ ና።
ፍቅርህም፡ በመከከላችን፡
የመንፈስህን፡ ብርሃን፡ ያብራ።

፪፡ አ፡ የሱስ፡ ና፡ ወደ፡ ሁላችን፡

ና፡ በፍቅርህ፡ አሙቀን።
በአንተም፡ እንዲሆን፡ ተስፋችን፡
ምሕረትህን፡ አስታውቀን።

፫፡ ይጥፋ፡ የሚያታልል፡ ተስፋ፡
ሰነፉም፡ ምንጭ፡ ይድረቅ፡ አውን።
መዳን፡ የማይሰጥ፡ ጥማም፡ ይጥፋ፡
አምባችን፡ አንተ፡ ብቻ፡ ሁን።

፬፡ ውዳሴ፡ ክብር፡ ኃይል፡ ምስጋና፡
ለአንተ፡ ብቻ፡ ይገባል።
በቃልህም፡ እንድንጸና፡
ተስፋችን፡ አንተ፡ ሁነሃል።

ረቡኒ።

፻፸፩፡

S. T. 350.

፩፡ ጸጋህን፡ ስጠኝ፡
በጅህም፡ ምራኝ፡
አ፡ ቸር፡ ሰማያዊ፡ አባት።
እንዳይደልለኝ፡
ክለም፡ ጠብቀኝ፡
አገሬ፡ እስክገባባት።

የመድኃኒታችን፡ አካል፡ እንድሆን፡
በውነት፡ በርሱ፡ የምገኝም፡ እንድሆን፡
ጸጋህን፡ ስጠኝ።
በጅህም፡ ምራኝ፡
አ፡ ቸር፡ ሰማያዊ፡ አባት።

፪፡ እምነት፡ ፈጥረህ፡
ኃይልም፡ ጨምረህ፡
ና፡ የፈቀድኸውን፡ እዘዘኝ።
አዘህ፡ መክረህ፡
አቅም፡ ፈጥረህ፡
ለመታዘዝም፡ አገዘኝ።
ልቤም፡ አንተን፡ አምላክ፡ ብቻ፡ በመፍራት፡
ልትኖር፡ በጸጋህ፡ ወትሮ፡ ጠብቃት።
እምነት፡ ለኩሰህ፡
ኃይልም፡ ለግሠህ፡
ና፡ የፈቀድኸውን፡ እዘዘኝ።

ረስቲን።

የፒ፡

S. T. 323.

፩፡ አምላኬ፡ ፈትህን፡ አትሠውርብኝ።
ድምጼን፡ ስማልኝ፡ ቀረብ፡ አጽናናኝ።

አንተ፡ የታመንህ፡ የነፍሴ፡ መድኃኒት፡ ሆይ፡
አትመጣም፡ ወይ፡ አትመጣም፡ ወይ፡

፪፡ እንግዳ፡ ብቻ፡ በምድር፡ ነኝና፡
ገና፡ አላየሁም፡ ያንተን፡ ብዕዕና።
አንተ፡ የታመንህ፡ - - - ።

፫፡ በዚህ፡ በእንግዳ፡ አገርም፡ ሳለሁ፡
ወደ፡ ሰማይህ፡ በናፍቆት፡ አያለሁ።
አንተ፡ የታመንህ፡ . . . ።

፬፡ እስክትመጣም፡ በልቤ፡ ውስጥ፡ ንገሥ፡
ሐዘኔን፡ አቅልለህ፡ ደስታዬን፡ ቀድስ።
አንተ፡ የታመንህ፡ . . . ።

፭፡ አንተንም፡ ብቻ፡ አቤቱ፡ ልፈራ፡
ልቤ፡ በመንፈስህ፡ ወትሮ፡ ይመራ።
አንተ፡ የታመንህ፡ . . . ።

፮፡ የምትሰጠኝ፡ ዘውድ፡ እንዳይቀርብኝ፡
አምላኬ፡ ሃይማኖትን፡ ጨምርልኝ።
አንተ፡ የታመንህ፡ . . . ።

ረስቲን።

የ፲፩፡

S. T. 188.

፩፡ መንጋህን፡ ስታሰማራ፡
ለሚስትም፡ ስትራራ፡
አስበኝ።
በዚህ፡ ዓለም፡ ስንከራተት፡
ሐሳቤን፡ ዎዳንተ፡ ጐትት፡
ጠብቀኝ።

፪፡ በተወጋው፡ ጐድንህ፡ ብቻ፡
ባንተ፡ በጎች፡ መከማቻ፡
ሠውረኝ።
ቸር፡ እረኛ፡ ክፈትልኝ፡
እኔ፡ ደግሞ፡ ያንተ፡ በግ፡ ነኝ፡
ያንተ፡ ነኝ።

ረሰቲኝ።

የ፲፫፡

S. T. 495.

፩፡ የሱስ፡ ሆይ፡ ምራኝ፡
በቃልህ፡ ግዛኝ።
ተንቅሎ፡ ሲቀር፡ ይህ፡ ድንኳን፡

የ፲፪፡

S. T. 207.

፩፡ የሱስ፡ ባንተ፡ ድኜ፡
ገንዘብህም፡ ሁኜ፡
ባንተ፡ ጸድቅ፡ ነኝ።
ግን፡ በዓለም፡ ነገር፡
ልቤ፡ እንዳይታሠር፡
አንተ፡ ጠብቀኝ።

፪፡ ክፉው፡ ጠላቴ፡
ወጽመደ፡ ለጥፋቴ፡
ዘርግቶብኛል።
በኔ፡ ሲቀናብኝ፡
ሀብቴን፡ ሊነጥቀብኝ፡
ሰርክ፡ ይሸምቃል።

፫፡ ስለዚህ፡ ወደኛ፡
አንተ፡ ቸር፡ እረኛ፡
ናና፡ ጠብቀን፡
ታናሽ፡ መንጋህንም፡
ጋርደ፡ አድነንም፡
ተከባከበን።

ረሰቲኝ።

ወደ፡ ሰማያዊ፡ ከንአን፡
የሱስ፡ ሆይ፡ ምራን።
በሰማይ፡ አግባን።

O. E.

የፐፀ፡

S. T. 434.

፩፡ ባርከን፡ ጠብቀን፡
በፈትህ፡ ብርሃን፡ አብራልን፡
ሰላምህን፡ ላክልን።
በዚህ፡ ስምህን፡ እናክብር፡
በሰማይ፡ ግን፡ በቅዱስ፡ ከንፈር፡
ልናመሰግን፡ በክብር፡
ከቅዱስ፡ ኪሩቤል፡
ከክቡር፡ ሱራፌል።
ሦኅአና፡ ልዑል፡ ቅዱስ፡
ጠቅላይ፡ ንጉሥ፡
በኃይል፡ በግርማ፡ ለሚነግሥ።

O. E.

የፐሮ፡

S. T. 511.

፩፡ ለአምላክ፡ ዘምሩ፡
በእርሱ፡ ደስ፡ ይበለን።
በታላቅ፡ ፍቅሩ፡
ግሩም፡ ውለታ፡ ሠራልን።
ከእናት፡ ማሕፀን፡
በምሕረት፡ አስካውን፡
ወትሮ፡ ሲጠብቀን፡
ሠራልን፡ መልካሙን።

፪፡ የጸጋ፡ አምላክን፡
ወትሮ፡ እንድንፈራ፡
መንፈሱንም፡ ይስጠን፡
በእርሱም፡ እንመራ።
የምሕረት፡ አምላክም፡
ይስጠን፡ ምሕረቱን።
እስከ፡ ዘላለምም፡
ከእኛ፡ ጋር፡ ይሁን።

፫፡ ሰርክ፡ እናመስግነው፡
አ፡ አብ፡ አ፡ ወልድ፡ አ፡ መንፈስ።
ዘላለም፡ አምላክ፡ ነው፡

አ፡ አንተ፡ ሥሉስ፡ ቅዱስ።
ለቅዱስ፡ ሥላሴ፡
ለሦሥቱ፡ አካላት፡
እናቅርብ፡ ውዳሴ፡
እናቅርብም፡ ስብሐት።

ረሰቲን።

፻፲፮፡

S. T. 794.

፩፡ አምላክን፡ አክብሩ፡
ዕሙን፡ ነው፡ ምክሩ፡
ይሰሩ፡ ክብሩ።
በኃይሉ፡ ነግሥዋል፡
ጸጋን፡ ለግሰልናል።
እንዴት፡ ያስደንቃል፡
ታላቅ፡ ፍቅሩ።

፪፡ ተዋረደ፡ ለሰው፡
ጽዋውም፡ መረረው፡
ሲቀበለው።
መድኃኒቱም፡ ሲሞት፡
መላእክት፡ አደነቁት፡

መሰቀሉም፡ ሕይወት፡
ሊሰጠን፡ ነው።

፫፡ ምሕረቱ፡ ታላቅ፡ ነው።
ሊያመሰግነው፡
አይበቃም፡ ሰው።
አንድ፡ ቀን፡ ግን፡ በሰማይ፡
ግርማውን፡ በግልጥ፡ ስናይ፡
ምስጋናው፡ የቀላይ፡
ምሳሌ፡ ነው።

፬፡ ግን፡ በዚህ፡ ታች፡ አውን፡
ጀምሩ፡ አዲሱን፡
ድንቅ፡ መዝሙሩን።
ያምላክ፡ ነው፡ መንግሥትም፡
ኃይል፡ ገናንነትም፡
እስከ፡ ዘላለምም፡
ለርሱ፡ ይሁን።

ረሰቲን።

፻፲፯፡

S. T. 418.

፩፡ አ፡ መድኃኒታችን፡ አ፡ የክብር፡ ንጉሥ፡
አ፡ ፈጣሪ፡ ጠባቂያችንም፡

ዘመን፡ ሲለዋወጥ፡ አንተ፡ ሥሉስ፡ ቅዱስ፡
ለዘላለም፡ አትለወጥም።
ስምህን፡
ላመስግን።
ነፍስ፡ ያላቸው፡ ሁሉ፡
ክብርህን፡ ይዘምራሉ።

፪፡ አ፡ የቤሰልሀልን፡ ርኅሩኅ፡ ንጉሣችን፡
ስለ፡ በጎችህ፡ የተሰቀልኽው።
አንተ፡ ትሰጣለህ፡ ኃይል፡ በድካማችን።
ምስጋናችንን፡ ተቀበለው።
አ፡ መድኅን፡
ተመስገን።
ውዳሴ፡ ስብሐትም፡
ይሁንልህ፡ ለዘላለም።

ረስቲን።

S. T. 2.

፩፡ ኑ፡ አላንት፡ ሰዎች፡
ጌታን፡ እናመስግን፡
አብራችሁም፡ ልጆች፡

አመስግኑ፡ ፍቅሩን፡
አክብሩ፡ ጸጋውን።

፪፡ ሰማይና፡ ምድር፡
በግርማ፡ ሲመላ፡
የሰማይ፡ ክብር፡
ትቶ፡ በትሕትና፡
ስለኛ፡ ተገዛ።

፫፡ ያን፡ ደዌያችን፡
እርሱ፡ ተሸከመ፡
ኃጢአትን፡ ሞትን፡
ለኛ፡ አሸነፈ፡
ሰላሙን፡ ሰጠን።

፬፡ እኛን፡ ሊበጀን፡
ንጹሑ፡ ቄሰለ።
ለርሱ፡ ሊዋጀን፡
እጅግ፡ ተጋደለ፡
በመስቀሉ፡ ሞተ።

፭፡ ሊያዘጋጀን፡
ሙሽራው፡ ልንሆን፡
ሞገስ፡ ሊሰጠን፡

በስሙ፡ ስናምን፡
ጽድቁን፡ ተላብሰን።

፯፡ በቃል፡ በሥራ፡
የሱስን፡ ለማክበር፡
በሞቀ፡ ደስታ፡
ስለ፡ አምላክ፡ ፍቅር፡
በመዝሙር፡ እናክብር።

ሉንሂል።

የፐፀ፡

S. T. 418. Hamb. Ps. 18.

፩፡ አ፡ ግሩም፡ ጠቅላይ፡ ጌታ፡
ሁሉን፡ የሚገዛ፡
ለእንተ፡ ይሁን፡ ምስጋና።
አትፍረድብን፡
ምሕረት፡ አድርግልን፡
ቅዱስ፡ መንገድህን፡ አሳየን።
ሁሉ፡ ቀን፡
አምላክን፡
ከመላእክቱ፡ ማሕበር፡
በደስታ፡ እናክብር።

፪፡ ለፈጣሪ፡ ክብረት፡
እልል፡ በል፡ አ፡ ፍጥረት፡
በልዩ፡ ድምጽ፡ ዘምርለት።
በእሳት፡ የጋልሽ፡
ብርሃን፡ የመላብሽ፡
አንቺ፡ አብራ፡ ለፈጣሪሽ።
አእላፎች፡
ከከቦች፡
ጨረቃም፡ ይዘምሩ፡
ሥልጣኑን፡ ያሳዩ።

፫፡ ነፍሴ፡ ሆይ፡ ለጌታ፡
አቅርቢ፡ ምስጋና፡
ቤቱን፡ ገብተሽ፡ በእልልታ።
ይስገዱለት፡ ሁሉ፡
ለክብሩ፡ ይኑሩ፡
በቅናት፡ ግዛቱን፡ ያስፉ።
በለም፡ ላይ፡
በሰማይ፡
በዘላለም፡ ዘመን፡
ይመስገን፡ ጌታችን።

O. E.

የሯ፡

S. T. 512. 466. Heffn. 264.

፩፡ ልመናን፡ ስለ፡ ሰማልኝ፡
አምላክን፡ ልወድስ፡ ነኝ።
ረጆች፡ ሁሉ፡ ሲርቁብኝ፡
አምላክ፡ ኃይል፡ ረድኤት፡ ሆነኝ።
ክፉን፡ ሁሉ፡ ሊያሸንፍ፡
ሕዝቡን፡ በሰልፉ፡ ሊደግፍ።

፪፡ በጤና፡ ወይ፡ በሞት፡ ጊዜ፡
አለኝ፡ ተስፋ፡ ባምላኬ።
እርሱ፡ ረድቶኛል፡ በጭንቄ፡
አሁን፡ ደስ፡ ይላል፡ ልቤ።
ስለዚህ፡ እርሱን፡ ላመስግን፡
ለማገልገሉ፡ ልፈጥን።

፫፡ ልዑል፡ አምላክ፡ ሁን፡ ኃይላችን፡
ሕዝብህን፡ ከሞት፡ አድን።
ማሕበርህን፡ በዓለም፡ አግነን፡
ጠብቅ፡ ግዛ፡ ርስትህን።
ተከባክበን፡ በምድር፡
አልቀን፡ በሰማይ፡ ክብር፡

O. E.

የሰፅ፡

S. T. 513. Heffn. 268.

፩፡ ሕዝቦች፡ ሆይ፡ ደስ፡ ይበላችሁ።
አምላክን፡ አመስግኑ።
የቆማችሁ፡ በኪዳኑ፡
በአንድነት፡ ቅረቡ።
ቅረቡ፡ በእልልታ፡
ዘምሩ፡ ለቸር፡ ጌታ።

፪፡ እርሱ፡ ነው፡ የፈጠረን፡
ልጆቹን፡ የጠራን፡
የጠፉትንም፡ ያዳነ፡
እስካሁን፡ ያቆመን።
እርሱ፡ በሰማይ፡ ደስታ፡
አደራጀልን፡ ስፍራ።

፫፡ ዘምሩለት፡ በበሮቹ፡
ወድሱት፡ በመቅደሱ።
ከገር፡ ሁሉ፡ ተከማቹ፡
ላባታችን፡ ስገዱ።
ርኅሩኅ፡ ሁኖ፡ ይጸናል፡
እስከ፡ ሞት፡ ይመራናል።

O. E.

፻፸፱፡

S. T. 514. Heffn. 271.

፩፡ ላምላክ፡ በሰማይ፡ ቀኙ፡
ሕዝቦች፡ ሁሉ፡ ይስገዱ።
ድምጽ፡ ያለበት፡ ነፍስ፡ ሁሉ፡
ያመስግን፡ በመቅደሱ።

፪፡ በእጁ፡ የፈጠረው፡
እጅግ፡ ግሩምና፡ መልክም፡ ነው።
ከዘላለም፡ ያሳየው፡
ተገልጠልን፡ ግርማው።

፫፡ ከአምላክ፡ ላስታረቀን፡
ከጥፋት፡ ለነጠቀን፡
እንዳባት፡ ላሞገሰን፡
እንዘምር፡ ሁሉ፡ ቀን።

፬፡ ፍጥረቱ፡ በመላዋ፡
ስብሓት፡ ታቅርብ፡ ለጌታ።
ነፍሴም፡ ደግሞ፡ በደስታ፡
ታመስግን፡ ሃሌሉያ።

O. E.

ስለ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ በዓላት።

፻፸፫፡

S. T. 551.

፩፡ መንገድ፡ አብያ፡ ለጌታ፡
ጠማማውም፡ ይቅና።
ይመጣል፡ ወደ፡ እኛ፡
የእሥራኤል፡ ዋና።
የጽድቅም፡ ገጢ፡ ይሆናል፡
ሥልጣኖቹን፡ ይጨብጣል።
ከአብ፡ የመጣልን፡
እርሱን፡ እናመስግን።

፪፡ ነዋሪ፡ ንጉሥ፡ ነው፡
ወደኛ፡ የመጣ።
ልብስን፡ እናንጥፈው፡
ተፈጸመ፡ ተስፋ።
ቃሉ፡ እውነት፡ ነውና፡
ዘምሩ፡ ሆሣእና።
ከአብ . . . . . ።

፫፡ ደጅህን፡ ክፈትለት፡
ንጉሥህንም፡ አግባ።

ሊሰጥ፡ ለሕዝብ፡ ድኅንነት፡
ለዓለሙ፡ ተስፋ።
በምድር፡ ዙርያ፡ ሁሉ፡
እንዲሁ፡ ብለው፡ ሊቀኙ፡
ከአብ፡ . . . . ።

፬፡ የሩሳሌም፡ ተጣሰ፡
መቅደሱም፡ ተፈታ።
ያ፡ ክህነቱ፡ ተሻረ፡
ሉሉ፡ ዘውዱ፡ ጠፋ።
የጌታ፡ መንግሥት፡ ግና፡
በዓለሙ፡ ሊገዛ።
ከአብ፡ . . . . ።

ገብረ፡ ክርስቶስ።

የ፹፬፡

S. T 444.

፩፡ ነብያት፡ ያዩልን፡ ቀን፡
አሁን፡ ጮሕ፡ ወጣልን።
አምላክ፡ ከወረደልን፡
በፍቅሩ፡ ደስ፡ ይበለን።
ሠዓአና፡ ስግደት፡ ክብረት፡
አሁን፡ እናቅርብለት።

፪፡ ዘውድ፡ አልተቀዳጀም፡
እንደርሱ፡ ግን፡ የለም።
ጌጡ፡ አይታይ፡ ለዓለም፡
ሞትን፡ ግን፡ ሊያወድም።
ሠዓአና፡ . . . . ።

፫፡ ሳለ፡ ጠቅላይ፡ ንጉሥ፡
ሆነ፡ ትሑት፡ ዕጉሥ።
በርኅራኄ፡ ነው፡ ውዱስ፡
በፍርዱም፡ ጻድቅ፡ ቅዱስ።
ሠዓአና፡ . . . . ።

፬፡ ይህን፡ ንጉሥ፡ ጥራ፡
ወደ፡ ልብህ፡ አግባ።
ከንተ፡ ኪዳን፡ ሊጋቡ፡
ቤትህ፡ ደስታን፡ ሊመላ።
ሠዓአና፡ . . . . ።

O. E.

የ፹፭፡

S. T. 20.

ሠዓአና፡ ለዳዊት፡ ልጅ፡
የተባረክ፡ እርሱ፡ ነው።

ብሩክ፡ ይሁን፡ የዳዊድ፡ ልጅ፡
የሚመጣ፡ በእግዚአብሔር፡ ስም፡
ሆሣዕና፡ በአርያም፡
ሆሣዕና፡ ሆሣዕና።
ብሩክ፡ ይሁን፡ የዳዊት፡ ልጅ፡
የሚመጣ፡ በእግዚአብሔር፡ ስም።

ሉንሂል።

፻፹፮፡

S. T. 446.

፩፡ አ፡ ግሩም፡ ጊዜ፡ አ፡ ብሩክ፡ ሰዓት፡
ለቅዱሳን፡ ለነቢያት፡
የታየው፡ ቀን፡ መጣልን።
አሁንም፡ እንደ፡ አብ፡ ሥምረት፡
የአምላካችን፡ ምሕረት፡
ወደኛ፡ ወረደልን።
የሱስ፡
ክርስቶስ፡
ሰው፡ ሆነልን።
እናመስግን፡
በአንድነት፡
እንወድሰው፡ በእምነት።

፪፡ እንዳብ፡ በፍጹም፡ አምላክ፡ ነው፡
እንደኛም፡ ሆነ፡ ፍጹም፡ ሰው፡
ወዳምላክ፡ ሊያቀርበን።
የጠፋችን፡ ይፈልጋል፡
ሰላሙንም፡ ይሰጠናል፡
መድኃኒትም፡ ሆነልን።
ጥፋን፡
ልጁን፡
እንዲያድን፡
ያብ፡ ፈቃድን፡
ለመፈጸም፡
ወልድ፡ ተገለጠ፡ በዓለም።

፫፡ በመከራችን፡ አልቅሶ፡
ጭንቃችንን፡ አስታውሶ፡
በመንፈሱ፡ ሊጠረን፡
የአብንም፡ ፈቃድ፡ ሊገልጥ፡
ከጭንቅም፡ ሁሉ፡ የሚበልጥ፡
ሞሉ፡ ረድኤት፡ ሊሆነን፡
በሞት፡
ሕይወት፡
ሊዋጅልን፡

የሞት፡ ጸርን፡
ታግሦልን፡
ይከፍትልናል፡ ሰማይን።

፬፡ ሊያድነኑ፡ መጥተዋል፡
የጸጋም፡ ጅምበር፡ ወጥተዋል፡
ከቶ፡ የማይተወኑ።
እርሱን፡ እንድንከተለው፡
በእውነት፡ እረኛችን፡ ነው፡
ገንዘቡም፡ እኛ፡ ነን።
በርሱም፡
ፍጹም፡
ተስፋ፡ አለን፡
እንዲሰጠን፡
ግሩም፡ ብዕዕና።
ለርሱ፡ ነው፡ የሰው፡ ምስጋና።

ረሱቲን።

ያዕቆብ፡

S. T. 448.

፩፡ ለደስታ፡ ቀን፡ ሆነ፡ ንጋት፡
ላለም፡ የምስራች፡ ሆነላት።

መሢህ፡ እንደ፡ ተወለደ፡
ለእረኞች፡ ተገለጠ።

፪፡ በደንብሮች፡ በጎች፡ መሀል፡
በጎ፡ እረኛ፡ ገብቶአል።
የከዱትንም፡ ይጠራል፡
ሰባሮችን፡ ይጠግናል።

፫፡ ትሑት፡ ሩኅሩኅ፡ ሁኖ፡ መጣ፡
እስከ፡ ሞት፡ መስቀል፡ ሊገዛ፡
ከሞት፡ በደሙ፡ ሊዋጀን፡
ዘላለም፡ ሕይወት፡ ሊሰጠን።

፬፡ ለጋ፡ ተክል፡ የመሰለች፡
ታላቅ፡ ዛፍ፡ ሁና፡ ጀበበች።
የማሕበር፡ ጫፎች፡ ባለሙ፡
ለደከሙ፡ ያጠጣሉ።

፭፡ ዝናብ፡ ምድርን፡ እንዳራሰች፡
ቃሉ፡ ሊሰጥ፡ ደስታ፡ ልማት።
ጽድቅን፡ ሰላምን፡ ያመጣል፡
ፍሬ፡ ለዘላለም፡ ያፈራል።

፮፡ ሰማይና፡ ምድር፡ ያልፋል፡
የየሱስ፡ ቃል፡ ግን፡ ይኖራል።

ሁሉ፡ ለርሱ፡ ሊሰግዱ፡
ቋንቋች፡ ስሙን፡ ሊያመሉ።

፯፡ በየሱስ፡ ኃይል፡ ኦ፡ ክርስቲያን፡
ተነሡና፡ ሁኑ፡ ብርሃን።
የታገለ፡ ድል፡ ይነሣል፡
የታገሠ፡ ይከብራል፡

፰፡ ለቸር፡ አምላክ፡ ይሁን፡ ስብሐት፡
ስላሳየን፡ ፍቅር፡ የውሃት።
በምሕረቱ፡ ስላዳነን፡
እስከ፡ ዘላለም፡ ይመስገን።

O. E.

የ፹፱ኛ፡

Haeffn. 60.

፩፡ ሕፃን፡ ተወለደ፡ በዚህ፡ ሌት።
ያን፡ ቅዱስ፡ ሕፃኑን፡ እናክብር።
በእርሱ፡ ላይ፡ አለ፡ የአብ፡ ሥምረት፡
በእርሱም፡ ትምሕርቱ፡ ይዳብር።
ይኸ፡ ሕፃን፡ ባይወለድም፡
በጠፋነ፡ ሁላችንም፡
አሁን፡ ግን፡ ሕይወት፡ አለን።

፩፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ተመስገን።
በአንተ፡ ተስፋ፡ አግኝተን፡
ላንተ፡ እንሰግዳለን።

፪፡ እረኞች፡ መንጋቸውን፡ ሲጠብቁ፡
በሌሊት፡ በሜዳ፡ ሲቆዩ፡
በሰሙት፡ ነገር፡ ተደነቁ፡
የአምላክን፡ ክብርም፡ አዩ።
መልአክ፡ እንዲህ፡ ሲል፡ ዘመረ፡
መድኅን፡ ዛሬ፡ ተወለደ፡
እርሱም፡ በዳዊት፡ አገር፡
ጌታችን፡ ነው፡ በርሱም፡ ሥልጣን፡
የአምላክ፡ የግርማው፡ ብርሃን፡
ተገለጠ፡ በምድር፡

፫፡ መላእክትም፡ ደግሞ፡ በታላቅ፡ ቃል፡
አምላክን፡ ይወድሱ፡ ጀመር፡
በቅዱሳን፡ በሰማይ፡ ጸዳል፡
ዘላለሙ፡ እንደሚዘመር።
ለአምላክ፡ ውዳሴ፡ ይሁን፡
በምድርም፡ ሰላም፡ ይሁን፡
በጎም፡ ፈቃድ፡ አይተወን።
ኦ፡ ርኅሩኅ፡ አምላክ፡ ተመስገን።

ከልጅህ፡ ጋር፡ ከሰጠኸን፡
ከጸጋህ፡ አትለየን።

ረስቲን።

፻፸፱፡

S. T. 514.

፩፡ ያብ፡ ሥምረት፡ ተገለጠች፡
ንጽሕየት፡ ድንግል፡ ወለደች።
ያምላክ፡ ልጅ፡ ተወልዶዋል፡
በእጹብ፡ ያስደንቃል።

፪፡ ግሩም፡ ተአምራት፡ አይተናል።
ባምላክ፡ መንፈስ፡ ሁንዋል።
የዘላለም፡ ያምላክ፡ ቃል፡
እንደ፡ ሰው፡ ተወልዶዋል።

፫፡ ሳይደርስበት፡ ኃጢአት፡
የሰውን፡ ሁሉ፡ ኃጢአት፡
የሚሸር፡ ተወለደ፡
ከሥጋም፡ ተዋሐደ።

፬፡ ፍጹም፡ አምላክ፡ ፍጹም፡ ሰው፡
በመሆኑ፡ መድኅን፡ ነው።
በሥቃይና፡ ሕማም፡
አግኝቶልናል፡ ሰላም።

፭፡ ጥንት፡ ከአብም፡ ወጥትዋል፡
ወደ፡ አብም፡ አርግዋል።
በቀኙም፡ ተቀምጥዋል፡
ሁሉም፡ ይገዛለታል።

፮፡ ሞትን፡ በምላኪ፡ ኃይል፡
ለዘላለም፡ ሽርዋል።
ድል፡ በብርቱ፡ ውጊያ፡
ነሥትዋል፡ ሃሌሉያ።

፯፡ አምላክን፡ በአርያም፡
እናመስግን፡ በሰላም።
እኛን፡ መንፈሱም፡ ይምራ፡
ምድሪቱም፡ ጽድቅ፡ ታፍራ።

ረስቲን።

፻፸፪፡

S. T. 55.

፩፡ ሕፃን፡ ተወልዶልናል፡ ልጅም፡ ተሰጠን።
ከአምላክ፡ በደም፡ በሥጋም፡ ተገናኘን።
ከሰው፡ ዘር፡ ከሴቶቹ፡ እናቱን፡ መርጠ፡
በውርደት፡ ተወለደ፡ ፍቅሩን፡ ገልጠ።

፪፡ ፈጣሪ፡ ከፍጥረቱ፡ ጋራ፡ ተዛምዶ፡

ከኃጢአተኞችም፡ ቅዱስ፡ ተጣምዶ፡
አብ፡ ወልድን፡ ከላከ፡ ሊሆን፡ ዘመዳችን፡
ምሕረቱን፡ ላሳየን፡ ይረግ፡ ምስጋናችን።

፫፡ በውድቀቱ፡ አዳም፡ ላወረሰን፡ ሁሉ፡
መድኃኒት፡ ተገኝ፡ በበረት፡ በጕሉ።
ስርየት፡ ልናገኝ፡ ስለ፡ ኃጢአታችን፡
የዓለም፡ ፈራጅ፡ ሁንዋል፡ ወንድማችን።

፬፡ የታሠሩን፡ ሁሉ፡ አወጣ፡ አርነት፡
ከሞት፡ ከቅጣትም፡ አበጀ፡ ነጻነት።
ጠላቶቹን፡ ሁሉ፡ በኃይል፡ ድል፡ ይነሣል፡
ለኃጢአተኞች፡ ይቅርታን፡ ይለግሣል።

፭፡ በበረት፡ በጕሉ፡ የተኛ፡ ሕፃኑ፡
ሰው፡እርሱን ሊወድስ፡ አይበቃውም፡ ልሣኑ።
በውርደቱ፡ ክብሩ፡ ተደብቆ፡ ባይታይም፡
መዳንን፡ ብዕዕናን፡ ግን፡ ዋጀ፡ ለዓለም።

፮፡ ይህንን፡ ብዕዕናም፡ በቃሉ፡ ይሰጣል፡
በቃሉም፡ የጸጋ፡ ፈቃዱን፡ ይገልጣል።
ስጥወታውንም፡ ለግሶ፡ ለሁሉ፡ ሲሰጠው፡
ልባችንን፡ አጽንተን፡ ቸል፡ እንበለው።

፯፡ ይልቅ፡ ልንቀበለው፡ እንሥግድለት፡

እንዲህም፡ ስንል፡ እንዘምር፡ በእምነት፡
በምድር፡ ተወልደህ፡ መዳን፡ የሆንህልን፡
አ፡ ቸር፡ ወንድማችን፡ አ፡ አምላክ፡ ተመስገን።

ረስቲን።

ያ፴፩፡

S. T. 443.

፩፡ በቤተ፡ ልሔም፡ በረት፡
ግሩም፡ ነገር፡ አይተናል።
የአምላካችን፡ ምሕረት፡
አሁን፡ ጎብኝቶናል።
በዳዊት፡ አገር፡ መድኅን፡
ዛሬ፡ ተወለደልን፡
እርሱም፡ ክርስቶስ፡ ጌታ።

፪፡ በበረት፡ ውስጥ፡ የተኛ፡
ሕፃን፡ ጌታችን፡ ነው።
ተወለደ፡ እንደኛ፡
እንዳብ፡ ግን፡ አምላክ፡ ነው።
ለእርሱም፡ ይሰግዳሉ፡
የምድር፡ አሕዛብ፡ ሁሉ።
መድኃኒታችን፡ ነው።

፫፡ እኛም፡ እንደ፡ መልአኩ፡
አሁን፡ እናመስግን።
አንድ፡ ልጁን፡ በመላኩ፡
አምላክ፡ ሁሉን፡ ሰጠን፤
ለአምላካችን፡ ክብር፡
ሰላም፡ በዚህ፡ በምድር፡
ለሰውም፡ በጎ፡ ፈቃድ።

ረሰቲን።

የዐቢይ፡

S. T. 448.

፩፡ የሩሳሌም፡ አልል፡ በዪ።
የጽዮን፡ ልጅም፡ ዘምሪ።
ንጉሥሽ፡ ይመጣልና፡
በምድር፡ ሁሉ፡ ሊገዛ።

፪፡ ጸጋና፡ ጽድቅን፡ ሊሰጠን፡
ከአባቱ፡ ተላከልን።
ይሰጣልም፡ ለሰው፡ ሰላም፡
ከኃጢአት፡ ሁሉ፡ በማዳን።

፫፡ ምስራች፡ የነገረ፡ መልአክ፡
ተልከልናል፡ ከአምላክ።

በርሱ፡ ያገኘነው፡ ተስፋ፡
ይሰጠናል፡ ታላቅ፡ ደስታ።

፬፡ ስብሐት፡ ለአምላክ፡ በአርያም፡
በዓለምም፡ ይሁን፡ ሰላም።
ታላቅ፡ ጸጋ፡ ላመጣልን፡
በምሉ፡ ልብ፡ እናመስግን።

N. N.

የዐቢይ፡

S. T. 579.

፩፡ የልደት፡ ቀን፡ ሲመጣ፡
የቤት፡ ልሄም፡ ሕፃን፡
በበረት፡ ላይ፡ የተኛ፡
ይሰጠናል፡ ብርሃን።

፪፡ በመውረድህ፡ ወደኛ፡
ፍቅርህ፡ ተገለጠ።
በኃጢአት፡ ዘመናችን፡
እንዳናሳልፈው።

፫፡ የሱስ፡ ያስፈልገኛል፡
የሕፃናት፡ ወዳጅ፡

በእኔ፡ እንዳታዝን፡
ልከተልህ፡ እርዳኝ።

N. N.

የዐፀዬ፡

S. T. 27.

፩፡ የማይነገር፡ ነው፡ የማይታሰብ፡ ነው፡
ታላቅ፡ ደስታ፡ የልደት፡ ቀን፡
አቀርቡ፡ ክብር፡ በሁሉ፡ ምድር።
ያምላክን፡ ፍቅር፡ እናመስገን።

፪፡ መሢህ፡ መጣልን፡ ሕዝቡን፡ ሊያድን፡
ከርስቶስ፡ ጌታ፡ ከእሴይ፡ ስር።
ዕርቅን፡ አመጣ፡ ተገኘ፡ ነጻ፡
ሐሴትን፡ አድርጊ፡ ነፍሴ፡ ሆይ።

፫፡ አምላክ፡ ይመስገን፡ ስለሚሰጠን፡
ጸጋ፡ ሁሉ፡ በቸር፡ ልጁ።
ወንድም፡ ሆነልን፡ ደጅ፡ ከፈተልን፡
ልጆች፡ ሲለን፡ ሰዎች፡ ሁሉ።

N. N.

የዐፀዬ፡

S. T. 450.

፩፡ ሕፃን፡ ተወልዶዋል፡ በቤትልሄም፡ ቤትል
| ሄም።
ደስ፡ ይበልሽ፡ የሩሳሌም።
ሃሌሉያ፡ ሃሌሉያ።

፪፡ እናቱ፡ ማርያም፡ ንጽሕይት፡ ድንግል፡ ናት፡
| ድንግል፡ ናት።
አባቱም፡ አብ፡ በሰማያት።
ሃሌሉያ፡ ሃሌሉያ።

፫፡ በበረት፡ ውሥጥ፡ ሕፃኑን፡ አኖሩ፡ አኖሩ።
መላእክትም፡ ለርሱ፡ ዘመሩ።
ሃሌሉያ፡ ሃሌሉያ።

፬፡ ሰብዓ፡ ሰገልም፡ መጥተው፡ ሠዉለት፡ ሠ
| ዉለት።
ወርቅና፡ ዕጣን፡ ከርቤም፡ ሰጡት።
ሃሌሉያ፡ ሃሌሉያ።

፭፡ መድኃኒት፡ ያ፡ ሕፃን፡ ሁኖልናል፡ ሁንዋል፡
ጭንቃችንም፡ ተሸርዋል።
ሃሌሉያ፡ ሃሌሉያ።

፯ የአምላክ ልጅ በፍቅሩ መጣልን መጣ
ልን።
በእርሱም ደስ ይበለን።
ሃሌሉያ ሃሌሉያ።

፰ አወረደልን ከአብ ሥምረቱን ሥምረ
ቱን።
በደስታ እናያለን ፊቱን።
ሃሌሉያ ሃሌሉያ።

፱ መላእክት ስለርሱ እንደዘመሩ ዘመሩ
እላንተም ምስጋናውን አውሩ
ሃሌሉያ ሃሌሉያ።

፲ ለቸሩ አምላክ ይሁን ክብር ክብር
ሰላምም በኛ በምድር።
ሃሌሉያ ሃሌሉያ።

ገብረ ክርስቶስ

የዐቢይ

S. T. 21.

፩ የልደት ማታ እንዴት ያበራል
መብራት ሲለኰስ በልብና ቤት።
የመላእክት መዝሙር አሁን ይሰማል

ከጥንቱ ጀምሮ ይደመላል።
ለአምላክ ይሁን ምስጋና በምድርም ሰ
ላም
ለሰው በጎ ፈቃድ ይሁን ሲሉ ዘመሩ።
የልደት ማታ እንዴት ያበራል
መብራት ሲለኰስ በልብና ቤት።

፪ አምላክ ለምድር የሰጠው ስጦታ
ለኃጢአተኞች መዳን ይሆናል።
ዐሐይ በዓለም እንደሚወጣ
ጨለማን የሱስ አሸንፍዋል።
ሕዝብ በጨለማ የሔደ በሞት አገርም
በጽላም የኖረ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ።
አምላክ ለምድር የሰጠው ስጦታ
ለኃጢአተኞች መዳን ይሆናል።

፫ በየሱስ ክርስቶስ ነው የተሰጠ
ዕርቅና ጽድቅ ሕይወትና ሰላም።
መድኃኒታችን የወይን ዛፍ ሆነ
የሕይወት ፍሬ ከርሱ አገኘነ።
አንድ ወንድ ልጅ ተሰጠን ሕፃን ተወ
ልድዋል
አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል።

በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ነው፡ የተሰጠ፡
ዕርቅና፡ ጽድቅ፡ ሕይወትና፡ ሰላም።

ጥአ።

፪፻፸፯፡

S. T. 141.

፩፡ የደስታ፡ ሌት፡ የሰላም፡ ሌት፡
ጸዳልሽ፡ ያበራል።
ጥሩ፡ ብርሃንሽ፡ አረኞች፡ አዩ፡
ወደ፡ መድኃኒት፡ ገስገሱ።
ሕዛኑን፡ አገኙ፡ ሕዛኑን፡ አገኙ።

፪፡ ቅዱስ፡ ጊዜ፡ ታላቅ፡ ጊዜ፡
ነብያት፡ የነገሩ።
በዓለም፡ ጨለማ፡ ወጣ፡ ብርሃን፡
ክብር፡ ለአምላክ፡ በሰዎች፡ ማዳን፡
በምድር፡ ሁሉ፡ ሰላም፡ በምድር፡ ሁሉ፡ ለላም።

፫፡ የደስታ፡ ሌት፡ የሰላም፡ ሌት፡
የማዳን፡ ጊዜ፡ ንጋት።
ታላቅ፡ መልካም፡ የምስራች፡ ቀን፡
ክርስቶስ፡ ተወልዶዋል፡ በቤተ፡ ልሄም፡

የሱስ፡ የሰላም፡ ንጉሥ፡ የሱስ፡ የሰላም፡
ንጉሥ።

ቢግሪድ፡

፪፻፸፰፡

S. T. 492.

፩፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስለ፡ እኛ፡
መከራ፡ ተቀበለ።
እርሱም፡ እንደ፡ በደለኛ፡
በንጨት፡ ላይ፡ ተሰቀለ።
ቤዛ፡ እርሱ፡ ሁንዋል፡
በኛም፡ ፈንታ፡ መትዋል።

፪፡ በሕማማቱ፡ በሞቱም፡
ምሕረት፡ ተዋጅቶልናል።
በትንሣኤውም፡ በሕይወቱም፡
ጽድቅም፡ ተገኝቶልናል።
በዕርገቱም፡ ወደ፡ ላይ፡
ስፍራ፡ ስጠን፡ በሰማይ።

፫፡ በመድኃኒታችን፡ መስቀል፡
የሚያምን፡ ምስጉን፡ ነው።
የሱስ፡ ክርስቶስን፡ መቀበል፡

የዘላለም፡ ሕይወት፡ ነው።
የመድኃኒታችን፡ ሞት፡
ለኛ፡ ነው፡ ብፁዕ፡ ሕይወት።

ረሰቲን።

የ፴፱፡

S. T. 553.

፩፡ ኑ፡ ሁላችን፡ እንመልከት፡
የጌታችንን፡ ሥቃይ።
ኃጢአትን፡ ሲያስወግድ፡
መከራውን፡ እንወያይ።
የመድኃኒቱን፡ ሕመም፡
የሚመስል፡ አልነበረም።

፪፡ ቅዱስ፡ አካሉን፡ ችንካሩ፡
ገትሮ፡ አቈሰለ።
የሾህ፡ ዘውድ፡ ነው፡ በግምባሩ፡
መቅሠፍትም፡ ተቀበለ።
የመድኃኒቱን፡ ሕመም፡
የሚመስል፡ አልነበረም።

፫፡ በመጨረሻም፡ በመስቀል፡
እጅግ፡ ከተሣቀየ፡

አሁን፡ መንፈሴን፡ ተቀበል፡
ሲል፡ ላበቱ፡ ጸለየ።
የመድኃኒቱን፡ ሕመም፡
የሚመስል፡ አልነበረም፡

፬፡ ያምላክ፡ መቅደስ፡ መንጦላዕት፡
ያን፡ ጊዜ፡ ተበጠሰ።
የማስታረቅ፡ መሥዋዕት፡
ፊጽሞ፡ ተጨረሰ።
የመድኃኒቱን፡ ሕመም፡
የሚመስል፡ አልነበረም።

፭፡ ሰው፡ ሆይ፡ ስለ፡ ኃጢአትህ፡
የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሙትዋል።
እስከ፡ መስቀል፡ ሞት፡ ዋፋትህ፡
መድኅኑን፡ አድርስዋል።
የየሱስን፡ ፍቅርም፡
የሚመስል፡ አልነበረም።

ረሰቲን።

የ፴፯፡

S. T. 456.

፩፡ የመስቀል፡ ውርደት፡ ስድብም፡
ተሸከምህልን፡ ጌታ።

የጠራትን፡ ለማዳንም፡
ሞትህልን፡ በጎልጎታ።
አ፡ ፍቅር፡ ግሩም፡
አ፡ ቅዱስ፡ ደም፡
ስለኛ፡ የተሰጠ።

፪፡ የመስቀል፡ ሽክም፡ ከባድ፡ ነው፡
የኛ፡ ዕዳ፡ ሲጨመር።
ምስጋና፡ ከማይሰጥህ፡ ሰው፡
እኛ፡ እንዳንደመር።
አስታውሰን፡
መ-ቅ፡ ፍቅርህን፡
ልባችን፡ የሚሰብር።

፫፡ የመስቀል፡ መንገድ፡ መረጥህ፡
ትተህ፡ ያባትህ፡ ግርማ።
ልታስረዳን፡ ታላቅ፡ ፍቅርህ፡
ተዋረድህ፡ ስለኛ።
ይታማሣል፡
ያሸንፋል፡
አ፡ ጌታ፡ ያንተ፡ ፍቅር።

፬፡ በመስቀልህ፡ ሥቃይ፡ ጌታ፡
ኃጢአት፡ ያስወገድህልን።

እኛ፡ ድል፡ ነሥተን፡ በደስታ፡
ቤትህን፡ መግባት፡ አስችለን።
ባንተ፡ እምነት፡
ለነፍስ፡ ዕረፍት፡
አሁን፡ በዳግህ፡ አለን።

N. N.

፻፸፩፡

S. T. 458.

፩፡ ከምላክ፡ የራቅነውን፡ ኃጥአን፡
ልጆቹ፡ እንዲያደርግ፡
በንጹሕ፡ ደመ፡ ገዛን፡
ያ፡ ቅዱስ፡ የአምላክ፡ በግ።
በልብህ፡ ሥቃያችንን፡
ተሸክመህ፡ ልባችንን፡
አዳንህ፡ አ፡ ጌታ፡ የሱስ።

፪፡ ብርቱ፡ የሚያስደንቅ፡
ሥቃይ፡ ሲያስፈራራህ፡
መንፈስህም፡ ሲጨነቅ፡
በጸርህ፡ ለኛ፡ ራራህ።
ጭንቃችንን፡ ብታስብም፡

ሕማሙን፡ አልተሰቀቅሀም።
ተመስገን፡ ጌታ፡ የሱስ።

፫፡ እኛ፡ እንድንባረክ፡
ተጫነ፡ በንተ፡ መርገም።
ጻርህ፡ እንዴት፡ ይተረክ፡
መስቀሉን፡ ስትሸከም፤
የመቅሠፍት፡ ጽዋ፡ ጠዋተህ፡
ስለኛ፡ ነፍስህን፡ ሰዋተህ፡
አዳንኸን፡ ጌታ፡ የሱስ።

፬፡ የሱራፌልን፡ ጭፍሮች፡
ሁሉን፡ መዋረት፡ ሲቻልህ፡
የአርያምም፡ ኃይሎች፡
ሲታዘዙ፡ ለቃለህ፡
በምድራችን፡ ታሥረህ፡
እሞት፡ ድረስም፡ ታዝዘህ፡
ሞትህልን፡ ጌታ፡ የሱስ።

፭፡ ግን፡ ምሕረት፡ ያላሳየህ፡
አምላክ፡ ለእኔ፡ ራራ።
ልቤም፡ ስለ፡ ሥቃይህ፡
ይሆናል፡ ከንተ፡ ጋራ።
ልቤን፡ እሰጥሃለሁኝ፡

ለአንተም፡ እሆናለሁኝ፡
ለአንተ፡ ጌታ፡ የሱስ።

ረስቲን።

፪፻፸፪፡

S. T. 473.

፩፡ የሱስ፡ ሆይ፡ ያንተ፡ ሕማማት፡
ያንተ፡ ቍስልና፡ ሞት፡
ይሰጠኛል፡ ማጸናናት፡
በሚደርስብኝ፡ ጭንቀት።
ሥጋዬ፡ ቢፈትነኝ፡
ሕማምህን፡ አሳስበኝ።
ጕዳት፡ እንዳይወርድብኝ፡
ሥጋዊ፡ ምኞት፡ አጥቃልኝ።

፪፡ ክፉ፡ ሥጋ፡ ወደ፡ ፍትወት፡
ቢያስመንኝ፡ ለውድቀት፡
ቍስልህን፡ ግን፡ ስመለከት፤
ሊሆነኝ፡ አዲስ፡ ድፍረት።
ሰይጣንም፡ ቢፈትነኝ፡
የጸጋህን፡ ኃይል፡ ሳገኝ፡
በቶሎ፡ እስኪሸሽልኝ፡
ለማሸነፍ፡ ልታበቃኝ።

፫፣ የሱስ፡ ሆይ፡ የልቤ፡ ጌታ፡
በውስጤ፡ ከኖርህልኝ፡
ጭንቅ፡ ምንም፡ እንኳ፡ ቢበዛ፡
ከሰላምህ፡ አይለየኝ።
ዋጀኸኝ፡ ለአንተ፡ ነኝ፡
ምን፡ አለ፡ የጐደልኝ።
ሁሉ፡ ካንተ፡ ጋራ፡ ሳለኝ፡
ብፅዕናን፡ አታስቀርብኝ።

ሉንደል።

፻፸፫፡

S. T.714; 457.

፩፡ ፍርዳችንን፡ የወሰድኸው፡
መስቀልን፡ የተሸከምኸው፡
ከሞትም፡ ኃይል፡ ያወጣኸን፡
አ፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ አድምጸን።
አ፡ የሞትህልን፡ አድነን።
ስማልን፡ ጸሎታችንን።

፪፡ ታላቅ፡ ሥራህ፡ ተፈጸመ፡
ፍርድ፡ ምሕረቱን፡ አተመ።
የፍርድ፡ አምላክ፡ ለኃጢአት፡
ከሰጠ፡ በቂውን፡ ቅጣት፡

መሐሪ፡ አምላክ፡ ልጆቹ፡
አደረገን፡ በምሕረቱ።

፫፡ ግን፡ የሱስ፡ ሆይ፡ ካልረዳኸን፡
እንዴት፡ ደከሞች፡ እኛ፡ ነን።
ልጅነታችን፡ በቀላል፡
ከእኛ፡ ይጠፋብናል።
ያምላክ፡ ልጆች፡ ያደረግኸን፡
አ፡ የሱስ፡ አንተ፡ ጠብቀን፡

፬፡ አትራቅብን፡ የሱስ፡ ሆይ፡
ሁሉ፡ ጊዜ፡ ከኛ፡ ዘንድ፡ ቆይ።
በፈተና፡ አበርትተህ፡
በትግልም፡ አጠንክረህ፡
በሕይወቱም፡ በሞቱም፡ ጸር፡
በደምህ፡ ኃይል፡ ሁን ከኛ፡ ጋር።

ረስቲን።

፻፸፬፡

S. T. 454.

፩፡ የሱስ፡ ሆይ፡ ጤና፡ ሰላምም፡
ልትሰጠኝ፡ ሙተሃል።
በማይነገረው፡ ሕማምም፡

ነፍሴን፡ ከሞት፡ ገዝተሃል።
ከጥፋት፡ አሁን፡ ድኛለሁ፡
ሕይወትንም፡ እወርሳለሁ።
ይሁንልህ፡ ውዳሴ፡
ጌታ፡ የሱስ፡ አምላኬ።

፪፡ ስለመረረ፡ ሕማምህ፡
ልቤ፡ ያመሰግናል።
በሥቃይህ፡ በድካምህ፡
ሕይወት፡ ተገኝቶልኛል።
ልትሰርይ፡ የኔን፡ በደል፡
ሞትን፡ ቀምሰሃል፡ በመስቀል።
ይሁንልህ፡ ውዳሴ፡
ጌታ፡ የሱስ፡ አምላኬ።

ረስቲን።

የማጌ፡

S. T. 458.

፩· አ፡ ያምላክ፡ በግ፡ ስለኛ፡
በመስቀል፡ ላይ፡ ተሠዋህ።
አ፡ አንተ፡ ተዕግሥተኛ፡
አ፡ አንተ፡ ርኅሩኅ፡ የዋህ፡

ፍርዳችንን፡ ተሸከምኸው።
የሞትን፡ ኃይል፡ አሸነፍኸው።
ሰላም፡ ስጠን፡ አ፡ የሱስ።

ረስቲን።

የማጌ፡

S. T. 500.

፩፡ ከአምላክ፡ ፍርድ፡ ልታድነን፡
በመስቀል፡ ሞት፡ የገዛኸን፡
አ፡ መድኀኔ፡ አ፡ አምላክ፡
መርገሚን፡ የሚደመስስ፡
ደምህ፡ በእኔ፡ ላይ፡ ይፍሰስ፡
እኔን፡ ርጉም፡ ይባርክ።
ያ፡ ቅዱስ፡ ደምም፡ ኃይል፡ ይስጠኝ፡
ከፈተናም፡ ይጠብቀኝ፡
በእንብ፡ ዱሐም፡ ስሔድ፡ ይምራኝ፡
በሞት፡ በሕይወትም፡ ይርዳኝ።
ጉዞዬንም፡ ከጨረስሁ፡
ከደረስሁ፡
በፍቁር፡ እቅፍህ፡ ውስጥ፡ ያግባኝ።

ረስቲን።

፪ኛ፡

S. T. 396.

፩፡ ያምላክ፡ በግ፡ በመስቀል፡ ላይ፡
የተቀበለው፡ ሥቃይ፡
በምነት፡ ስመለከተው፡
ሕይወትና፡ ጤና፡ ነው።

፪፡ ያን፡ ጊዜ፡ የፈሰሰው፡
ቅዱሱ፡ የልጁ፡ ደም፡
ባምላክ፡ ፍርድ፡ አጸደቀኝ፡
ከክፋቴም፡ አጠበኝ።

፫፡ ወንበደሙ፡ የጸለየው፡
ጸሎት፡ ልመናዬም፡ ነው።
አስበኝ፡ በመንግሥትህ፡
ስል፡ የጸጋ፡ መልስ፡ ሰጠህ።

፬፡ የሱስ፡ ባምላክ፡ ተዋለህ፡
በንጨት፡ ላይ፡ ተለሰቀለህ፡
እኔ፡ ካምላክ፡ እንዳልጣል፡
ፍጹም፡ ተስፋ፡ ሰጥተሃል።

፭፡ አብ፡ አሁን፡ ነው፡ አባቴ፡
እኔም፡ በመድኃኒቴ፡

የሚወደኝ፡ ልጁ፡ ነኝ፡
በቅፉም፡ ውስጥ፡ ተቀበለኝ።

ረሱቲን።

፫ኛ፡

S. T. 449: 459.

፩፡ ያፈሰስህልን፡ ደምህን፡
አ፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ተመስገን።
ከሰይጣን፡ ተንኰልና፡ ኃይል፡
በሞትህ፡ አድነኸናል።

፪፡ አ፡ ፍጹም፡ አምላክ፡ ፍጹም፡ ሰው፡
ና፡ ጸሎታችንን፡ ስማው።
የታሠርነበት፡ ወጽመዳን፡
በኃይልህ፡ በጥሰው፡ አሁን።

፫፡ ከኀጢአትም፡ ጠብቀን፡
መስቀል፡ ሲከብድም፡ ደግፈን፡
ጭንቅም፡ እንዳያሸንፈን፡
ቅዱስ፡ ረድኤትህን፡ ስጠን።

፬፡ አ፡ የሱስ፡ ወንድማችን፡ ነህ፡
በሁሉም፡ ረድኤታችን፡ ነህ፡

ከመከራችን፡ አድነን፡
ካንተም፡ ዘንድ፡ ሕይወትን፡ ስጠን።
ረቡዒን።

፪፻፶፱፡

S. T. 300.

፩፡ የሰ፡ በመስቀል፡ ሞተልን።
እንማጥን፡ በፍቅሩ።
አምላክ፡ ሁሉ፡ ዓመፃችን፡
ተወልን፡ ስለ፡ ስሙ።
አምላክ፡ ሆይ፡ አባት፡ ሁንልን፡
ጸጋህን፡ ለጽድቅ፡ ስጠን።
አመላችን፡ ለውጥልን፡
ቀድስ፡ ሕይወታችንን።

O. E.

፪፻፷፡

S. T. 584.

፩፡ አልረሳውም፡ ያንን፡ ጊዜ፡
በጌቴሴማኔ።
በጣርህ፡ ደም፡ ሲያልብህ፡
ስለኔ፡ አምላኬ።

አልረሳውም፡ አልረሳውም፡
ክቶ፡ አልረሳውም፡
የብርቱ፡ ጣርህን፡ ጊዜ፡
በጌቴሴማኔ።

፪፡ ብዚያ፡ ሥፍራ፡ ባታክልቱ፡
በልቤ፡ አየሁህ።
ቤዛ፡ ሁነህ፡ የፍርድ፡ መዓት፡
እንደ፡ ተቀበልህ።
አልረሳውም፡ አልረሳውም፡ . . ።

፫፡ ወዳጆችህ፡ ሁሉ፡ ካዱህ፡
አልራራልህም፡ አብ።
ያ፡ ብርቱ፡ ችግርህ፡ ጊዜ፡
አይመዘንም፡ በሰብ።
አልረሳውም፡ አልረሳውም፡ . . . ።

፬፡ ፍቅሬ፡ ቢበርድብኝ፡ ላንተ፡
ክብሩ፡ መድኃኒቴ።
ሕማማትህን፡ አሳስበኝ፡
አሳየኝ፡ ቍስልህን።
እንዳልረሳው፡ እንዳልረሳው፡
ይህን፡ እንዳልረሳው፡

የብርቱ፡ ጣርህን፡ ጊዜ፡
በጌቴሴማኔ።

፫፡ ስለኔ፡ ነው፡ ስለኔ፡ ነው፡
ደምህ፡ የፈሰሰ።
እንዳመሰግንህ፡ ጌታ፡
ከፈትልኝ፡ አፌን።
እንዳልረሳው፡ እንዳልረሳው፡ . . . ።

ሲግሬድ።

፪፻፩፡

S. T. 31.

፩፡ ወደ፡ ቅዱስ፡ ቍስሉ፡
ነፍሴ፡ ሆይ፡ ዕረጊ፡
ወደ፡ ረድኤ፡ መስቀሉ፡
እምነሽ፡ ተጠጊ።
ያምላክ፡ ልጅ፡ እረኛሽም፡
ሞተ፡ ለበጎቹ።
ዕዳን፡ ሁሉ፡ ከፈለም፡
ስለ፡ ወንድሞቹ።

፪፡ ከጥፋት፡ ሊያድነን፡
ወርቅም፡ ብርም፡ ሆነ፡
ከምላክ፡ ፍርድ፡ ሊጋርደን፡
የማይበቃ፡ ሆነ።
ነገር፡ ግን፡ የአምላክ፡ ልጅ፡
መሥዋዕት፡ ሆነ፡
እኛንም፡ ከሰይጣን፡ እጅ፡
በሕማም፡ አዳነ።

፫፡ በሕማሙም፡ ከመንሁ፡
በርሱ፡ እድናለሁ።
ጽድቁን፡ ከተቀበልሁ፡
ጻድቅ፡ እሆናለሁ።
ንጹሕ፡ ደሙን፡ አፍስሶ፡
ያምላክ፡ በግ፡ ሞተልኝ።
ኃጢአቴን፡ ደምስሶ፡
ቅዱስ፡ እርድ፡ ሆነልኝ።

፬፡ ደሙም፡ ስላጸደቀኝ፡
አብ፡ ይቀበለኛል።
የልጁም፡ ሙሽራ፡ ነኝ፡
በርሱም፡ ደስ፡ ይለኛል።
ከኔ፡ ጋር፡ ተባበረ፡
ያለም፡ ፍትወት፡ ይጥፋ።

የሱስ፡ በኔ፡ ካደረ፡
የርሱ፡ ነኝ፡ በተስፋ።

፫፡ ቅዱሳኑቹ፡ ለሰማይ፡
ብሩክን፡ ደጆች፡ ናቸው።
ችጋረኞች፡ ወደ፡ ላይ፡
ክፉት፡ በር፡ አላቸው።
ለሚታመመው፡ ድኃ፡
ጠበሉ፡ መነጨ።
ቅዱስ፡ የሕይወት፡ ውኃ፡
በርሱ፡ ላይ፡ ተረጨ።

፬፡ ወደ፡ ቅዱስ፡ ቅኑስ፡
ነፍሴ፡ ሆይ፡ ዕረጊ።
ጤናሽ፡ ነው፡ በመስቀሉ፡
ከርሱ፡ አትራቂ።
በዚህ፡ ቅዱስ፡ አምባ፡ ላይ፡
ሕይወት፡ ታገኛለሽ።
ከፍርሃትና፡ ሥቃይ፡
በርሱ፡ ትድኛለሽ።

ያሣፍ፡

Haeffn. 103

፩፡ ጌታ፡ ከሞት፡ ተነሥትዋል፡
መቃብር፡ አሁን፡ በረ።
የሞትን፡ ኃይል፡ አሸንፍዋል፡
ሕይወትንም፡ አሰፋ።
ከመቃብር፡ ይወጣል፡
በባንዴራው፡ ተጽፍዋል፡
ትንሣኤ፡ ነኝ፡ ሕይወትም።
ሃሌሉያ።

፪፡ ወደ፡ ሕይወት፡ አካሔዴን፡
በርሱ፡ ተስፋ፡ ላቀና።
ልነግሥ፡ ነኝ፡ በደይን፡ ቀን፡
ልኖር፡ ለርሱ፡ ምስጋና፡
በማይጠፋብኝ፡ ሕይወት፡
ክንቱነት፡ የማይነካበት፡
በኃጢአት፡ የማይረክስ።
ሃሌሉያ።

፫፡ ሞት፡ ሆይ፡ ዬታለ፡ ያንተ፡ ሾህ፡
ማሸነፍህ፡ ዬታለ፡
የሱስ፡ ፍጹም፡ ከሸነፈህ፡

የሚጐዳኝ፡ ማን፡ አለ፤
ለዘላለም፡ የርሱ፡ ነኝ።
ይላል፤ እኔ፡ ወዳለሁኝ፡
አላንትም፡ ልትሆኑ።
ሃሌሉያ።

ሉጣሄል። — O. E.

ደግሞ፡

S. T. 463.

፩፡ በአፋችሁም፡
በልባችሁም፡
ክርስቶስን፡ አመሰግኑ።
ስለ፡ እኛ፡
መዶ፡ ተኛ፡
ሶስት፡ ቀን፡ በመቃብሩ።
ከመቃብር፡
ባምላክ፡ ክብር፡
ለተነሣው፡ ዘምሩ።

፪፡ ስለዳችን፡
ተቀጣልን፤
ጽድቁንም፡ አወረሰን።
ያ፡ ረኃችን፡

ከጭንቃችን፡
ለዘላለም፡ አዳነን።
በሞት፡ ፈንታ፡
ሕይወት፡ በንታ፡
ለኛም፡ ሕይወት፡ ሰጠችን።

፫፡ እኛን፡ ምሮ፡
ሞትን፡ ሽሮ፡
ሰይጣንን፡ ቀጠቀጠ።
ኃይልም፡ ሁሉ፡
በለም፡ ምሉ፡
ለወልድ፡ ብቻ፡ ተሰጠ።
በብርሃኑ፡
ስንኖአኑ፡
ምሕረትም፡ ተገለጠ።

፬፡ ለአብ፡ ክብር፡
በዚህ፡ ምድር፡
የሰው፡ ውዳሴ፡ ይሁን።
ላንዱ፡ ልጁም፡
እንደዚህም፡
እናመስግን፡ ምሕረቱን።
ለቸር፡ ውዱስ፡

መንፈስ፡ ቅዱስ፡
እናሳርግ፡ ውዳሴውን።

ረስቲን።

፪፻፶፡

S. T. 461-

፩፡ ክርስቶስ፡ ሕያው፡ ሆነ፡ መቃብር፡ በራ፡
መድኃኒት፡ ተገኘ፡ ትንቢትም፡ መላ።
ግርማን፡ ተጐናጽፎ፡ ከሞት፡ ወጥተዋል።
ከጠላት፡ ተዋጋ፡ ድል፡ ግን፡ ነሥተዋል፡
ያ፡ ማሕተም፡ ተፈታ፡ ድንጋይ፡ ለቀቀ።
ጠባቂው፡ ፈርቶ፡ ፈጥኖ፡ ሸሸ፡
ሲኦልም፡ ተገዛ።
ሃሌሉያ።

፪፡ ከጨለማ፡ ጋራ፡ ብርሃን፡ ሲዋጋ፡
ብርሃን፡ ለዘላለም፡ ሸሮ፡ ድል፡ ነሣ፡
ያ፡ ሞት፡ ተደበየ፡ ድል፡ ነሣ፡ ሕይወት፡
ተስፋችን፡ በረታ፡ ለማበት፡ እምነት።
እላንት፡ ሐዘንተኞች፡ ከልብ፡ ተቀኙ።
ከሞት፡ አዳነኑ፡ በየውሃቱ፡
ሊኖር፡ ክኖ፡ ጋራ፡
ሃሌሉያ።

፫፡ ሰማይ፡ ከምድራችን፡ አሁን፡ ታርቀዋል።
መቃብር፡ የደስታ፡ መንገድ፡ ሆንዋል።
እንባን፡ ያቀረራችሁ፡ በመስቀል፡ ትይዩ፡
ጠላቶች፡ ቢቆጩ፡ ሐሴት፡ አድርጉ።
የጠፉትን፡ ወዶ፡ በጎ፡ እረኛ፡
ገና፡ ይጠራል፡ ከርሱ፡ የከዳ።
ይመለስ፡ ለመንጋ።
ሃሌሉያ።

፬፡ ቤት፡ ክርስቲያን፡ ጸናች፡ ነፋሳት፡ ይምጡ፡
በብርሃኑ፡ ፍጥነት፡ ሰፋ፡ ትምህርቱ።
በዓለሙ፡ ወጡ፡ መልክተኞቹ፡
ሞት፡ እንኳ፡ ሳይፈሩ፡ ወንጌል፡ ሲሰብኩ።
ስለኛ፡ ለሞተ፡ ነጻ፡ ላወጣን፡
ምስክር፡ ሊሰጡ፡ ሰውን፡ ለማዳን፡
ሊጣሩ፡ በደስታ።
ሃሌሉያ።

፭፡ ለምን፡ አልቅሳችሁ፡ እላንት፡ ምአመናን።
ስንት፡ አጭር፡ ነው፡ ዘመን፡ ሞት፡ እስኪጠራን።
መሬት፡ እንደ፡ እናት፡ ልታቅፋችሁ፡
እንደ፡ ሕያው፡ ዘር፡ ግን፡ ቆሎ፡ ትወጡ።
የዘራው፡ ይመጣል፡ በመከር፡ ጌዜ፡

ክርዳድን፡ ይለያል ከጥሩ፡ ፍሬ፡
ስንዴን፡ ሊያገባ።
ሃሌሉያ።

O. E.

፪፻፷።

S. T. 448. 449.

፩፡ የደስታ፡ ዘመን፡ ሁንዋል፤
ክርስቶስ፡ አሁን፡ ድል፡ ነሥትዋል።
ሲነግም፡ ከመቃብሩ፡
ታየልን፡ አምላክነቱ።

፪፡ ከመቅሠፍቱ፡ ሊያድነን፡
በሞተ፡ በሰስተኛው፡ ቀን፡
ተነሥቶ፡ ደግሞ፡ አንዲያርግ፡
ተጽፎ፡ ነበር፡ በምላክ፡ ሕግ።

፫፡ ቢጠብቁም፡ መቃብሩን፡
ወጣበት፡ ጥሶ፡ ድንጋዩን።
የሕይወት፡ ንጉሥም፡ ቢሞት፡
አልቀረም፡ በሲያል፡ ግዘት።

፬፡ ሲያል፡ አሁን፡ ተሸነፈ፤
የሞትም፡ ገጋር፡ ተቀሠፈ፡

ሃሌሉያ። ተነሥትዋል፡
ጌታችን፡ እንደ፡ ተስፋው፡ ቃል።

፭፡ ከሞት፡ ሥልጣን፡ ያወጣኸን፤
አ፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፤ ተመስገን።
ጸድቃን፡ በሚነሡበት፡ ቀን፡
የሕይወት፡ ትንሣኤ፡ ስጠን።

ረሱቲ።

፪፻፷፩።

S. T. 443.

፩፡ ድል፡ ነሥተሃል፡ አ፡ የሱስ፡
እርዳችን፡ አንተ፡ ነህ።
ላንተ፡ ለሕይወት፡ ንጉሥ፡
ምስጋና፡ እንስጥሀ።
የሞትን፡ ኃይል፡ ከሰበርህ፡
ለእኛ፡ ሕይወት፡ ፈጠርህ፡
በቅዱስ፡ ትንሣኤህ።

፪፡ መሬቱ፡ ቤትህ፡ ነበር፡
ለኛም፡ ይከፈታል።
እኛንም፡ ከመቃብር፡
ድምጽህ፡ ያስነሣናል።
አንተንም፡ በሕይወቱ፡

የወደደሁ በሞቱ፡
በእቅፍሁ ውሥጥ ያርፋል።

፫፡ ኃለኛውም ቀን ሲነጋ፡
በግርማሁ ስትታይ፡
ዙፋንህ ሲዘረጋ፡
ለፍርድ በአሕዛብ ላይ፡
መለከቱም ሲሰማ፡
ሕይወቱ እንደለማ፡
ድምጽህ ያስታውቃል።

ረስቲን።

የግጌ፡

S. T. 467.

፩፡ አያለሁ፡ የሱስ፡ ዕርገትህን፡
ስታርግ ከምድራችን።
እኔ ግን እንደ እንግዳ፡
ልኖር በውርደት ገና።
ሐዘን፡ ድካም ተከተለኝ፡
ገና ካባቴ ቤት ሩቅ ነኝ።

፪፡ ያን ክቡር አገር በእምነት፡
አሁንም ልመለከት።
ከኃጢአቴ ተፈትቼ፡

ልከብር በጌታዬ፡
ልኖር ከብፁዓን ጋራ፡
በሕያው አምላክ ከተማ።

፫፡ በወዲያ የለም ሌሊት፡
ጫለማ፡ ሐዘን ጭንቀት።
በዚያ አለ መዝገቤ፡
በዚያም ይሁን ልቤ።
ከየሱስ ይሩረኝ ሕብረት፡
ጸጋ ይስጠኝ ልኖርለት።

፬፡ ወደ ሰማይ እንደ ወጣ፡
ሊመለስ ወደ እኛ።
ለሥራዬ እንድቀና፡
በጸሎት እንድተጋ፡
እስኪመጣ ባልታሰበው፡
ዕለት ዕለት ልጠብቀው።

፭፡ ትጉ ሎሌ በሚሠራ፡
ብፁዕ ነው ስትመጣ።
ተስፋ ሰጠህ እንደሚወርስ፡
ያን ሰማያዊ መንግሥት።
ልታድለው ክብረት ደስታ፡
በልዑል አባትህ ግርማ። ሎንሂል።—O. E.